# የግብርና ዘርፍ የ2013 ዓመታዊ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

**አዲስ አበባ**

**ነሃሴ 2013 ዓ.ም**

# ማውጫ

**ይዘት......................................................................................................................ገጽ**

1. ድርሞ (Executive Summary) .......................................................... 1
2. መግቢያ ........................................................................................ 4
3. በቁልፍ የውጤት አመልካቾች መሰረት የፊዚካል ዕቅድ አፈፃፀም ..................... 4
3.1 ገበያ ተኮር የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ........................................ 4
3.2 ገበያ ተኮር የእንስሳትና ዓሳ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ............................ 17
3.3 የግብርና ግብዓት አቅርቦትና ምርት ግብይት ............................................ 24
3.4 ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ............................................ 30
3.5 የግብርና ምርምር ......................................................................... 44
3.6 ህብረት ስራ ማህበራት ..................................................................... 51
3.7 ግብርና ትራንስፎርሜሽን ................................................................... 52
3.8 ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ......................................................................... 55
4. የፕሮግራም በጀት ........................................................................... 65
5. የኦዲት ግኝት ................................................................................ 66
6. ተቋማዊ ለውጥና የአገልግሎት አሰጣጥ ..................................................... 67
7. ልዩ ድጋፍ ክልሎች የተከናወኑ ተግባራት ................................................... 68
8. ለክልሎች የተሰጠ አቅም ግንባታ ......................................................... 69
9. የዋና ዋና ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ............................................................ 70
10. በአፈፃፀም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ............. 79
11. ማጠቃለያ ................................................................................... 80
12. የግርጌ ማስታወሻ ........................................................................... 81
13. አባሪ 1፡ የግብርና ዘርፍ የቁልፍ አመልካቾች የ2013 ዓመታዊ አፈጻጸም ................ 82

## 1. ድርሞ (Executive Summary)

ይህ ሪፖርት የዘርፍን ዓመታዊ ሪፖርት አፈፃፀም የሚያሳይ ሲሆን በዓመቱ የተቀመጡ ዒላማዎችን በእያንዳንዱ የውጤት መስኮች በዝርዝር የአፈፃፀም መረጃዎችን በማሰባሰብና ትንተና በማካሄድ ዘርፉ ያለበትን የአፈፃፀም ደረጃ በሚያሳይ መልኩ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

የ2013 በጀት አመት ዓመታዊ ዕቅድ የ10 ዓመቱን መሪ ዕቅድ ርዕይ የሆነውን በ2022 የተሸጋገረ ግብርና ለመፍጠር ግብርናን ምርታማና ተወዳዳሪ በማድረግ የአርሶና አርብቶ አደሩን ገቢ ማሳደግና ከድህነት ማላቀቅ፣ እንዲሁም ሀገሪዊ ምግብና ስርዓተ ምግብ ፍልጎት ያሟላ፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓትና ለወጪ ንግድ በቂ ምርት ያቀረበ፣ ወደ እሴት ጭመራ የተራመደ ግብርና ለማየት የተቀመጡ የውጤት ማዕቀፍና ውጤቶችን ለማሳካት የሚያስችሉ የትግበራ መስኮችን መተግበር የጀመረበት አመት ነው፡፡

የሰብል ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ሀገራዊ የምግብና የኢንዱስትሪ ፍላጎትን የማርካትና የውጭ ምርቶችን አቅርቦት በመጨመር የውጪ ምንዛሪ ግኝትን ለማሳደግ በዕቅድ ተይዞ የተሰራ ሲሆን በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ የተገኘ ሰብል ምርት 640 ሚሊዮን ኩንታል የአቅዳችን 112 በመቶ የተሳካ ሲሆን ከአነስተኛ አርሶ አደር 621 ሚሊየን ኩንታል (110%) ሲመረት ከዚህ ውስጥ በግብርና አስተዳደራዊ ጥቅል መረጃ መሰረት 96.3 ሚሊዮን ኩንታል ከበልግ የተገኘ ሲሆን ከመካከለኛና ሰፋፊ የባለሀብት እርሻ ደግሞ 19 ሚሊየን ኩንታል (141%) ማምረት ተችሏል፡፡. የበልግ የምርት ትመና የማዕከላዊ ስታቲሰቲክስ መረጃ ሲለቀቅ የሚስተካከል ይሆናል፡፡

በበጋ እርሻ 350 ሺህ ሄ/ር በማልማት 12.25 ሚሊዮን/ኩ/ል ምርት ለማምረት እቅድ ተይዞ፤ በበጋ እርሻ (በመስኖና በበልግ) የሰንዴ ልማት 396 ሺህ ሄ/ር በማልማት 15 ሚሊየን ኩ/ል ምርት እንደሚገኝ ተገምቷል፡፡

የሆርቲካልቸር ምርቶች የወጪ ንግድ በ2013 በጀት አመት በአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት 425,337 ቶን ምርት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 309,857 ቶን (73%)ምርትን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ተችሏል፡፡ ካላፈው በጀት አመት ክንውን አኳያ ሲታይ የ7 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ 6.15 ሚሊ. ኩንታል ለማምረት ታቅዶ 6.73 ሚ ኩንታል (109%) ለማምረት ተችሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ 5.85 ሚሊ. ኩንታል በአነስተኛ አርሶአደሮች የተመረተ ነው፡፡

የቡና የወጪ ንግድ በ2013 በጀት 330,000 ቶን ምርት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 263,000 ቶን (79.6%) ምርትን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ተችሏል፡፡

በ2013 በጀት ዓመት 4,827 ሚ/ሊ ሊትር ወተት ለማምረት የታቀደ ሲሆን በዓመቱ መጨረሻ ወር ላይ 7,225 ሚ/ሊ ሊትር ወተት ለማምረት ተችሏል፤ አፈጻጸሙም 149.6% መድረስ ችሏል፡፡ ከዳልጋ ከብት ላም ወተት ምርት 3,978 ሚ/ሊ ሊ/ር ወተት ለማምረት ታቅዶ 4,692 ሚ/ሊ ወተት የተመረተ ሲሆን አፈጻጸሙም 117.9% ልደርስ ችሏል፡፡ የፍየል ወተት ምርትን ከቆላው ስነ ምህዳር በያዝነዉ በጀት ዓመት 0.099 ሚሊየን ሊ/ር ለማድረስ የታቀደ ሲሆን እስከ 2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ወር 0.099 ሚ/ን ሊ/ር የተመረተ ስሆን አፈጻጸሙም 100% ልደርስ ችሏል፡፡ የግመል ወተት ምርት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ 710 ሚሊየን ሊ/ር ለማድረስ ታቅዶ 2,434 ሚ/ሊ ሊትር የተመረተ ስሆን የ2013 አፈጻጸም 342% ልደርስ ችሏል

ከዳልጋ ከብት፣ ከበግ፣ ከፍየልና ከግመል 345 ሺህ ቶን ስጋ ለማምረት ታቅዶ 348.8 ሺህ ቶን (100%) ማምረት ተችሏል፡፡ ከዳልጋ ከብት፣ ከበግና ከፍየል የቆዳና ሌጦ ምርት 15.96 ታቅዶ 15.15 ሚሊየን ሲከናወን አፈጻጸሙም 95.04% ነው፡፡

የዶሮ ሥጋና እንቁላል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በተያዘ እቅድ 51.5 ሺህ ቶን የዶሮ ሥጋ ለማምረት ታቅዶ 70 (+100%) ሺህ ቶን ስጋ ተመርቷል፡፡ በተመሳሳይ 3,047.5 ሚሊየን እንቁላል ለማምረት ታቅዶ 2,771.13 ሚሊየን እንቁላል የተመረተ ሲሆን ይህም የእቅዱን 90.9% ማከናወን ተችሏል፡፡

በሀገር-አቀፍ ደረጃ የተፋሰስና የአረንጓዴ አሻራ ድህረ ተከላ ሥራዎችን አስመልክቶ በ2012 በጀት ዓመት በክረምት ወራት ለተተከሉ ችግኞች የድህረ ተካለ ወቅት ከተተከሉት 5.9 ቢሊዮን ችግኞች ውስጥ ለ5.35 ቢሊዮን ችግኞች በ1,347,118.87 ሄ/ር መሬት ላይ 18,478,974 አርሶ አደሮችን በማሳተፍ የአረም፣ የኩትኳቶና ውሃ የማጠጣት ስራ ለማከናወን ተችሏል፡፡ ለ2013 ተከላ በተለያዩ ችግኝ ጣቢያዎች 7.46 ቢሊዮን ችግኞች የተዘጋጁ ሲሆኑ ከዚህም ውስጥ 3.708 ቢሊዮን የዛፍ፣ 0.0579 ቢ/ን የቀርከሀ፣ 2.105 ቢ/ን ዘርፈ-ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው ዕፅዋት፣ 0.486 ቢ/ን የፍራፍሬ፣1.1.1 ቢ/ን የእንስሳት መኖ እንዲሁም 0.0027 ቢ/ን የውበት ዛፍ ችግኞች ናቸው፡፡ ከተዘጋጁት 7.46 ቢሊዮን ችግኞች ውስጥ 6 ቢሊዮን ችግኞች በአገር ውስጥ የሚተከሉ ሲሆን 1 ቢሊዮን ችግኞች ደግሞ ለጎረቤት አገራት የሚሰጥና የሚተከል ይሆናል፡፡

300,000 ሄ/ር የተጎዱና የተራቆቱ አካባቢዎችን በመከለል ከንክኪ ነጻ ለማድረግ ታቅዶ 215,469.9 ሄ/ር (71.82%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በበጀት ዓመቱ 2.5 ሚሊዮን ሄ/ር መሬት በተለያዩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ቴክኖሎጂዎች ለመሸፈን ታቅዶ 2.39 ሚሊዮን ሄ/ር (95.6%) መሬት ላይ መስራት ተችሏል፡፡

በ2012 የተደረሰበትን 790 ሺህ ሄ/ር መነሻ በማድረግ በ2013 ተጨማሪ 26,200 ሄ/ር በማሳካት 816,200 ሄ/ር ለማድረስ ግብ የተጣለ 26,000 ሄ/ር መሬት አዲስ የመስኖ መሬት ዝግጁ ለማድረግ ታቅዶ 56,540 ሄ/ር (215%)መሬት ለመስኖ ዝግጁ የተደረገ ሲሆን አፈፃፀሙ ከፍ ያለው የውሃ መሳቢያ ፓምፖች በስፋት በግዢ ለአ/አደር ስለተሰራጩ ነው፡፡ በተጨማሪም ከዕቅድ ውጭ በባህላዊ አሠራር የማህበረሰብ የውሃ አማራጭ 27,882 ሄ/ር መሬት ለመሥኖ ዝግጁ መሆኑን ከክልሎች በቀረበው መረጃ ለመለየት ተችሏል፡፡

የሚኒስቴር መ/ቤቱን አደረጃጀት ለማሻሻል የተጀመረው የሰው ኃይል የሪፎርም ስራ ተጠናቆ የየሥራ መደቡ የሥራ መዘርዝር ተዘጋጅቷል፡፡ አደረጃጀቱ እንደጸደቀ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡ የፖሊሲ ሪፎርም የማሻሻያ ሥራ የፖሊሲ አቅጣጫዎቸ ተዘጋጅቶ ለከፍተኛ አመራ ቀርቦና በአስተያየት ዳብሮ ለማፀደቅ ቀርቧል፡፡ በተዘጋጀው ረቂቅ መሰረትም የተለያየ ሙያ ያላቸው ግብረ ሃይል ተቋቁሞ ሲስተሚክ ኢንተርቬንሽን ፕላን ተዘጋጅቶ ፈፃሚ አካል ተለይቶ ወደ ተግባር ለመግበት በጀት በማፈላለግ ላይ ይገኛል፡፡ የስራ አካባቢን ምቹ ከማድረግ አኳያ አንድ ህንፃ የማሻሻያ ስራው ተጠናቆ ሥራ የጀመረ ሲሆን ሁለተኛው ሕንጻ በመጠናቀቅ ላይ ሲገኝ የቤተመጽሃፍት ግንባታ ከ45 በመቶ በላይ እንሁም የአዳራሽ ግንባታ ከ70 በመቶ በላይ ሲጠናቀቅ የግቢ አስፋልት ስራ ተጠናቆ ግሪኒንግ ብቻ ይቀራል፡፡

የግብርናን መረጃ ዲጂታይዝ ከማድረግ አኳያ የግብርና አስተዳደራዊ መረጃን ለማዘመን በየክልሉ ለተመረጡ 12 የሙከራ ትግበራ ወረዳዎች ሶፍትዌር የተጫነባቸው 1,984 ታብሌቶች በመጠቀም በመረጃ አስተዳደር ስርዓቱ ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ የሙከራ ትግበራውን ለማስፋት ይቻል ዘንድ ለክልል ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና እንዲሰጥ ከተደረገ በኋላ 32,947 ታብሌቶች ለየክልሎች እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡ ለ11 የክልል ኃላፊዎች እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው 57 የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት የትውውቅ ስልጠና፣ ለ51 የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጅ እና የዕቅድ ዝግጅት ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና እና 360 የዞን፣ የወረዳና የቀበሌ ልማት ጣቢያ ሰራተኞች ስልጠና እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ በትግበራ ሙከራ ወረዳዎች የተጀመረው ስልጠና እንደተጠናቀቀ የመረጃ ማስገባት ስራው የሚጀመር ይሆናል፡፡

ለክልሎች የተሰጠ ድጋፍን በሚመለከት ንዑስ ዘርፉ ለክልሎች የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት፣ በመስክ የክትትልና ድጋፍ ስራዎችን በማከናወን፣ የማቴሪያልና የገንዘብ ድጋፎችን በማድረግ፣ የጋራ የምክክር መድረኮችን በማካሄድ ክልሎችን ለመደገፍ ሰፊ ጥረት ተደርጓል፡፡

## 2. መግቢያ

የ2013 በጀት ዓመት የዘርፉ ዕቅድ በግብርና ሚኒስቴር ውስጥ የሚገኙ ሰራተኞች እና ክልሎች እንዲወያዩበትና በዕቅዱ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲይዙ ተደርጎ ወደ ትግበራ የተገባ ሲሆን የዘርፍ አፈፃፀም በተቀመጡ ዒላማዎችን በእያንዳንዱ የውጤት መስኮች በዝርዝር የአፈፃፀም መረጃዎችን በማሰባሰብና ትንተና በማካሄድ ዘርፉ ያለበትን የአፈፃፀም ደረጃ በሚያሳይ መልኩ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

በዚህም መሰረት የዋና ዋና ስራዎች አፈፃፀም ሪፖርት ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን በፕላንና ልማት ኮሚሽን የሪፖርት አቀራረብ መመሪያ መሰረት የፊዚካል ስራዎች አፈፃፀምን፣ የፕሮግራም በጀት አፈፃፀም፣ የኦዲት ግኝት፣ የተቋማዊ ለውጥና አገልግሎት አሰጣጥ፣ ለክልሎች የተሰጠ የአቅም ግንባታ እንዲሁም ተግዳሮቶችና በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች አካቶ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

## 3. በቁልፍ የውጤት አመልካቾች መሰረት የፊዚካል ዕቅድ አፈፃፀም

### 3.1 ገበያ ተኮር የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግ

የሰብል ምርትና ምርታማትን ለማሳደግ የምንከተለው የአመራረት ስርዓት በአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች እና በመካከለኛና ሰፋፊ የባለሀብት እርሻዎች ሲሆን የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች ሶስት የምርት ወቅት (መኸር፣ በልግና መስኖ) እና የመካከለኛና ሰፋፊ የባለሀብት እርሻዎች መሰረት አድርጎ የሚለማ ነው፡፡ በዕቅድ አፈጻጸም የተካተቱ ሰብሎች ሆርቲካልቸር፣ አዝርዕት፣ ቡና ሻይና ቅመማ ቅመምን ይይዛል፡፡
በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ የተገኘ ሰብል ምርት 640 ሚሊዮን ኩንታል የአቅዳችን 112 በመቶ ከአነስተኛ አርሶ አደር 621 ሚሊየን ኩንታል ሲመረት ከዚህ ውስጥ በግብርና አስተዳደራዊ ጥቅል መረጃ መሰረት 96.3 ሚሊዮን ኩንታል ከበልግ የተገኘ ሲሆን ከመካከለኛና ሰፋፊ የባለሀብት እርሻ ደግሞ 19 ሚሊየን ኩንታል የተመረተ ነው. የበልግ የምርት ትመና የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ መረጃ ሲለቀቅ የሚስተካከል ይሆናል፡፡

#### 3.1.1 የአነስተኛ ይዞታ እህል ልማት

የሰብል ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ሀገራዊ የምግብና የኢንዱስትሪ ፍላጎትን የማርካትና የውጭ ምርቶችን አቅርቦት በመጨመር የውጪ ምንዛሪ ግኝትን ለማሳደግ በአነስተኛ አርሶ አደሮች በ2011/12 ምርት ዘመን የነበረውን የበልግና መኸር ምርት ማስጠበቅና ለማካካሻ የሰፋፊ መሬትና የቆላማ አካባቢዎች እርሻዎች ለማስፋፋት ታቅዶ ተከናውኗል፡፡
በአነስተኛ አ/አደሮች በመኸር 12.85 ሚሊዮን ሄ/ር በማልማት 357 ሚሊ/ኩ/ል ምርት፤ በበልግ 1.93 ሚሊዮን ሄ/ር በማልማት 47.7 ሚሊ. ኩ/ል ምርት ማምረት፤ በበጋ እርሻ 350 ሺህ ሄ/ር በማልማት 12.25 ሚሊዮን/ኩ/ል ምርት ለማምረት እቅድ ተይዞ፤ በአነስተኛ አርሶ አደር በመኸር 13 ሚሊዮን ሄ/ር መሬት በማልማት 342 ሚሊ. ኩ/ል (2012/13 ማስኤ ሪፖርት) ተገኝቷል ይህ ምርት መጠን ከባለፈው

ምርት ዘመን ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር መጠነኛ (2 በመቶ) ጭማሪ ታይቷል። በበልግ ግብርና ሚ/ር ድህረ ምርት ግምገማ መረጃ መሰረት 2.01 ሚሊዮን ሄ/ር በማልማት 24.6 ሚሊ. ኩ/ል ምርት መገኘቱን ያሳያል። በቢጋ እርሻ (በመስኖና በበልግ) የሰንዴ ልማት 396 ሺ. ሄ/ር በማልማት 15 ሚሊየን ኩ/ል ምርት እንደሚገኝ ተገምቷል።

**የብርዕና አገዳ ሰብሎች ምርት** 302 ሚሊዮን ኩንታል የተገመተ ሲሆን 88 በመቶ የእህል ምርትን ይይዛል። ይህ ምርት ከባለፈው ምርት ዘመን ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር መጠነኛ (1.8 በመቶ) ጭማሪ አሳይቷል። ለዚህ ጭማሪ አስተዋፅኦ ካደረጉት ሰብሎች ውስጥ ሩዝ (57 በመቶ)፣ በቆሎ (9.7 በመቶ) እና ስንዴ (8.8 በመቶ) ናቸው። በተቃራኒም አጃ (33.3 በመቶ) ፣ ማሽላ (14.2) እና ጤፍ (3.9 በመቶ) የመሬት ሽፋን መቀነስ ተመዝግቧል።

**የጥራጥሬ ሰብሎች ምርት** 32 ሚሊዮን ኩንታል የተገመተ ሲሆን ከባለፈው ምርት ዘመን ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ6.5 በመቶ ምርት ቅናሽ አሳይቷል። ለዚህም የአኩሪ አተር (66 በመቶ) ፣ ነጭ ሽምብራ (37.8 በመቶ) እና አብሽ (34.7 በመቶ) ምርት ጭማሪ በሌላ በኩል የግብጦ (18.7 በመቶ) ፣ ማሾ (7.6 በመቶ) እና ጓያ (7.3 በመቶ) ምርት መቀነስ በማሳየታቸው ነው።

**የቅባት እህል ሰብሎች ምርት** 7.8 ሚሊየን ኩንታል የተገመተ ሲሆን ከባለፈው ምርት ዘመን ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ7.7 በመቶ ምርት ቅናሽ አሳይቷል። ለዚህ አስተዋፅኦ ያደረጉት ጎመን ዘር (70 በመቶ) ፣ ሱፍ (55.2 በመቶ) እና ኑግ (28.4 በመቶ) የምርት መቀነስ በማሳየታቸው። በአንፃሩ አቾሎኒ የ31 በመቶ ምርት መጨመር እንዲሁም ከፍተኛ የምርት ድርሻ ያለው ሰሊጥ ምርት ለውጥ አላሳየም።

የአብዛኛው የእህል ሰብሎች ምርታማነት ከባለፈው አመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር ጭማሪ አሳይቷል። ለምሳሌ የብርዕና አገዳ ሰብሎች ውስጥ ሩዝ የ6.1 በመቶ (ከ29.64 ወደ 31.45 ኩል/ሄር) ፣ ስንዴ የ2.54 በመቶ (29.71 ወደ 30.46 ኩል/ሄር) እና ጤፍ የ1.71 በመቶ (18.5 ወደ 18.82 ኩል/ሄር) ጭማሪ አሳይተዋል። በአንፃሩ አጃ የ8.37 በመቶ (ከ21.5 ወደ 19.7 ኩል/ሄር)፣ ማሽላ የ6.6 በመቶ (28.8 ወደ 26.9 ኩል/ሄር) እና በቆሎ የ1.41 በመቶ (42.39 ወደ 41.79 ኩል/ሄር) ምርታመነት መቀነስ አሳይተዋል። ከጥራጥሬ ሰብሎች ውስጥ አኩሪ አተር የ8.13 በመቶ (ከ23.03 ወደ 24.9 ኩል/ሄር) እና ቀይ ቦለቂ የ4.88 በመቶ (ከ16.8 ወደ 17.62 በመቶ) የምርታማነት ጭማሪ አስመዝግቧል። በሌላ መልኩ አብዛኞቹ የቅባት እህሎች ምርታማነት መቀነስ ያስመዘገቡ ሲሆን ሱፍ የ18.4 በመቶ (12.66 ወደ 10.33 ኩ/ል በሄር) እና ጎመን ዘር የ12.9 በመቶ (18.24 ወደ 15.88 ኩ/ል በሄር) ምርታማነት መቀነስ ከተመዘገበባቸው ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በአንፃሩ ኦቾሎኒ የ1.5 በመቶ (ከ17.8 ወደ 18.07) እና ሰሊጥ የ0.5 በመቶ (7.00 ወደ 7.04 ኩ/ል በሄ/ር) ምርታማነት ጭማሪ ያስመዘገቡ ናቸው። ከላይ የምርት

መቀነስ የታየባቸው ሰብሎች ከቅርብ ጊዜ ወድህ በበሽታና በተባይ ክስተት ምክንያት አርሶ አደሩ ወደ ሌሎች ሰብሎች ማምረት በመሸጋገሩ ነው፡፡

### 3.1.2 የመካከለኛ እና ሰፋፊ እርሻ ሰብል ልማት

በ2012/13 ምርት ዘመን ምርት ዘመን በሰፋፊ እርሻ 13.56 ሚሊዮን ኩ/ል የሚደርስ ምርት ለማምረት ታቅዷል፡፡ ዕቅዱን ለማሳካት በፌዴራል ደረጃ ዘርፉን ሊደግፉ የሚችሉ የፌደራል እና የክልል ባለድርሻ አካላት የምክክር መድረክ በማካሄድ ግንዛቤ የመፍጠር፣ በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሀብቶች አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ የተቻለ ሲሆን፣ ከክልል ግብርና ቢሮዎች ጋር በመተባበር በመስክ ደረጃ ለእርሻ ኩባንያዎች ድጋፍ በመስጠት በመሬት ልማትና በምርት አሰባሰብ ወቅት የሚጋጥሙ ችግሮች ለመፍታት ድጋፍ ተደርጓል፡፡

በዚህ መሰረት በ2012/13 ምርት ዘመን በሰፋፊ እርሻ በተለያዩ ጊዚያዊና ቋሚ ሰብሎች 19.15 ሚልዮን ኩ/ል (አፈፃፀሙ +100%) ምርት መገኘቱን ከማዕከላዊ ስታቲክስ ኤጀንሲ ከተገኘው መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከተገኘው ምርት ውስጥ የእህል ሰብል 14.13 ሚሊየን ኩ/ል፣ አትክልት 880,123 ኩ/ል፣ ስራስር 379,592 እና ሌሎች ሰብሎች 175.6 ኩንታል ይሸፍናሉ፡፡

### 3.1.3 አነስተኛ ሆርቲካልቸር ልማት

### የበልግና መኸር አትክልት ፍራፍሬና ስራ ስር ልማት

በበልግ 46.64 ሚ/ን ኩ/ል ታቅዶ 70.75 (151.7 %) ምርት መሰብሰብ ተችሏል፡፡ የመኸር ልማትን በተመለከተ ይሰበሰባል ተብሎ ከታቀደው 43.22 ሚ/ን ኩ/ል ታቅዶ በማእከላዊ ስታቲሰቲክስ መረጃ መሰረት 78.97 ሚ/ን ኩ/ል (182%) ምርት መሰብሰብ ተችሏል፡፡

በዚሁ በመኸር ወቅት ልማት ከተገኘው መረጃ 147,214 ኩ/ል ኤን.ፒ.ኤስ፣ 51,162 ኩ/ል ዩሪያ በድምሩ 198,376 ኩ/ል ማዳበሪያ፣ 349,816 ኩ/ል ምርጥ ዘር ጥቅም ላይ በማዋልና 1,477,087 (237,366 ሴት አርሶ አደሮችን) በማሳተፍ እንደለማ መረዳት ተችሏል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የአረንጓዴ አሻራ ልማትን ለማጠናከር በፍራፍሬ ተከላ ሰፊ ሥራዎች የተሰሩ ሲሆን ከክልሎች በተገኘው መረጃ ከተዘጋጁት 61,819,110 ችግኞች 56,363,861 ችግኞች ተከላ ተከናውኗል፡፡ ይህም ከተዘጋጀው ችግኝ 91% መተከሉን ያመላክታል፡፡ በሌላ በኩል የፍራፍሬ ክላስተር ልማትን ለማበረታታትና በዘርፉ ከተሰማሩ ባለሀብቶች ጋር በመሆን በኦሮሚያ ክልል በአደአ ወረዳ በግማሽ ሄክታር የአርሶ አደር ማሳ ላይ ተከላ የተካሄደ ሲሆን ባሳለፍናቸው ሶስት ዓመታት የተከናወነ የክላስተር ተከላን በመንብኘት ለቀጣይ የኤክስፖርት ሂደት ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

**የመስኖ አትክልት ፍራፍሬና ስራ ስር ልማት**

አብዛኛው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት በመስኖ በመታገዝ የሚለማ ሲሆን በመስኖ ከለማው ይገኛል ተብሎ የታቀደው ምርት 71.7 ሚሊ. ኩንታል በማ/ስ/ኤ መረጃ መሰረት **66.7** (93%) ሚሊዮን ኩንታል ምርት ተሰብስቧል፡፡

### 3.1.4 የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ልማት

**የቡና ምርታማነትን ለማሳደግ** በ2012/13 ምርት ዘመን የቡና ማሣ ምርታማነት ማሻሻያ ሥራዎችን በመፈፀም ለምርት የደረሰውን 861,435 ሄ/ር በአነስተኛ አርሶ አደሮችና ሰፋፊ እርሻ የቡና ማሣ ምርታማነቱን በሄ/ር 6.9 ኩ/ል ከነበረበት ወደ 7.9 ኩ/ል በማድረስ 6.15 ሚሊ. ኩንታል ምርት ለማምረት ግብ ተይዞ በማዕከላዊ ስታትስቲክስ የምርት ግምገማ መሰረት 857 ሺህ ሄ/ር የቡና መሬት ላይ **6.73** ሚሊ. ኩንታል /109%/ ምርት የተገኘ ሲሆን ምርታማነቱ **6.83** ኩ/ል/ሄ/ር /98%/ መድረሱን ሪፖርቱ ያሳያል፡፡

**የሻይ ምርታማነትን በማሳደግ** ምርት ዘመን በአልሚ ባለሀብቶችና በአነስተኛ አርሶ አደሮች 0.15 ሚ. ኩንታል ለማምረት ታቅዶ በማ/ስ/ኤ.መረጃ መሰረት 0.76 ሚ. ኩንታል />100% ለማምረት ተችሏል፡፡ በትስስር እያለሙ የሚገኙ 925 ወንዶችና 70 ሴቶች በድምሩ 995 አ/አደሮች በልማቱ ተሳትፈዋል፡፡

**የቅመማ ቅመም ምርታማነት** ለማሳደግ በአስተዳደራዊ መረጃ መሰረት በምርት ዘመኑ 364,006 ሄ/ር ማሳ በተለያዩ የቅ/ቅመም ሰብሎች ለመሸፈንና 720 ሺህ ቶን ምርት ለማምረት ታቅዶ 360,289 ሄር (99%) ማሳ በማልማት 644.3 ሺህ ቶን (89%) ተሰብስቧል፡፡ የዋና ዋና ቅመማ ቅመም ምርቶች አፈጻጸም በዝርዝር ሲታይ፡- የዝንጅብል ልማት በማሳ ሽፋንም ሆነ በምርት 100% የተፈጸመ ሲሆን በርበሬ በማሳ ሽፋን 95% በምርት 79%፣ ኮረሪማ በማሳ ሽፋን 100% በምርት 86%፣ ዕርድ በማሳ ሽፋንም ሆነ በምርት 100% አፈጻጸም ተመዝግቧል፡፡

**የቡና ዘር ብዜት** በበጀት ዓመቱ 5,450 ኩ/ል የቡና ዘር ለማዘጋጀት ታቅዶ 5,609 (103%) ተከናውኗል:: እንዲሁም ለ2013 ተከላ የሚውል 1.53 ቢሊዮን የቡና ችግኝ ለማዘጋጀት ታቅዶ ከፈሰሰው 5,529.44 ኩ/ል በቁጥርም 1,757,689,375 ዘር ውስጥ 1,482,939,038 የበቀለ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 1,376,371,655 ችግኞች በእንክብካቤ ላይ ይገኛሉ፡፡

**የቅመማ ቅመም ዘር አቅርቦት** በበጀት ዓመቱ ከምርምር ማዕከላት የቅመማ ቅመም ዘሮችን በማሰባሰብ የዋና ዋና ቅመማ ቅመም ሰብሎች የተሻሻሉ ዝርያዎች በተመረጡ የመንግስት ችግኝ ጣቢያዎች በመሞከር ውጤታማነታቸውን ለአርሶ አደር በማስተዋወቅ በቀጣይ ወደ ዘር ብዜት ለማስገባት ከተለያዩ

ምርምር ማዕከላት 30.5 ኪ.ግ የተለያዩ የቅመማ ቅመም ዝርያዎች ለማሰባሰብ ታቅዶ ከደ/ዘይት፣ መልካሳ፣ ሲናና እና ጎንደር ግብርና ምርምር ማዕከላት ጥቁር አዝሙድ 9.8 ኪ.ግ፣ ነጭ አዝሙድ፣ 3 ኪ.ግ፣ አብሽ 10 ኪ.ግ፣ ድንብላል 4 ኪ.ግ እና በርበሬ 0.54 ኪ.ግ በድምሩ 27.34 ኪ.ግ (89%) በማሰባሰብ ለክልሎች ማሰራጨት ተችሏል።

**የሻይ ችግኝ አቅርቦት** በበጀት ዓመቱ 4,000,000 የሻይ ችግኝ ለማዘጋጀት ታቅዶ 3,085,135 (77.13 %) ችግኞች ተዘጋጅተው እንክብካቤ እየተደረገላቸው ይገኛል።

**የታጠበ ቡና ምርት ዝግጅት** በበጀት ዓመቱ 697 ሺህ ቶን ቀይ እሸት ቡና ለመሰብሰብ ታቅዶ 739.9 ሺህ ቶን (100% በላይ)፣ እንዲሁም 129 ሺህ ቶን የታጠበ ቡና ከነገለፈቱ ለማዘጋጀት ታቅዶ 135.5 ሺህ ቶን (100% በላይ) ተከናውኗል።

**የቅመማ ቅመም ምርት ዝግጅት** የበርበሬ፣ ዝንጅብል፣ ኮረሪማ፣ ዕርድ፣ አብሽና አዝሙድ እና ሌሎች ቅመማ ቅመሞች በበጀት ዓመቱ 661.8 ሺህ ቶን ምርት ለማዘጋጀት ታቅዶ 390.723 ሽህ ቶን 59% ተከናውኗል።

**የሻይ ምርት ዝግጅት** በሻይ አልሚ አርሶ አደሮች እና ልማት ድርጅቶች ከሚለማውና ምርት መስጠት ከሚችለው የሻይ ማሳ በበጀት ዓመቱ 11.766 ሺህ ቶን ደረቅ የሻይ ምርት እንደሚዘጋጅ ታቅዶ 11,430 ቶን የሻይ ቅጠል (›100%) ምርት እንደተዘጋጀ ተረጋግጧል።

**ዕሴት የተጨመረባቸው ምርቶች ምርት ዝግጅት** በበጀት ዓመቱ 0.99 ሺህ ቶን ተቆልቶ የተዘጋጀ ቡና እና 0.011 ሺህ ቶን የቅመማ ቅመም ምርት ለውጪ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ ተቆልቶ የተዘጋጀ ቡና 0.42 ሺህ ቶን (43%) እና የቅመማ ቅመም ምርት 2.18 ሺህ ቶን (>100%) ማከናወን ተችሏል።

### 3.1.5 የሜካናይዜሽን አገልግሎት ማሳደግ

የግብርና ሜካናይዜሽንን ለማስፋፋት በተደረገው ጥረት ከአጠቃላይ 17 ሚሊዮን ከሚገመት አርሶ /አርብቶ አደሩ ብዛት ውስጥ 17 በመቶ የሜካናይዜሽን አገልግሎት ተጠቃሚ ሲሆኑ ጠቅላላ ከለማው 13 ሚሊዮን ሄ/ር መሬት በሚካናይዜሽን የለማው መሬት 19.5 በመቶ ነው። የትራክተር አጠቃቀምን በተመለከተ በ1000 ሄ/ር የእርሻ መሬት የትራክተር ብዛት 0.68 መድረሱን ለመገመት ተችላል። የሚካናይዜሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ለማበረታታት ለ300 የቀረጥ ነጻ እድል ተጠቃሚዎች በመመሪያው መሰረት በማስተናገድ አገልግሎት ለመስጠት እንዲሁም የማማከር እና መረጃ የመስጠት ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለ980 ተገልጋዮች የተሟላ አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን በግብርና መካናይዜሽን የሞያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለተገልጋዮች ለመስጠት የተዘጋጀውን ሰነድ በማጸደቅ ስራ ላይ ለማወል ተችሏል።

በሁለተኛ ዙር የጸደቁ የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎች ስታንዳርድ ማስተዋወቂያ መድረክ፤ በአዳማና ባህር ዳር ከተማ የጸደቀዉን የስታንዳርድ ሰነድ የማስተዋወቂያ መድረክ በማዘጋጀት ለተግባራዊነቱ አጠቃላይ ስምምነት ተደርጎ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

የግብርና ሜካናይዜሽን የታክስና ልዩ ልዩ ቀረጥ ነጻ ዕድል በኩል ከውጪ ሃገር የሚገቡ መሳሪያዎችን በተዘጋጀው መስፈርት እና በደረጃዎች ኤጀንሲ በፀደቀው መሰረት በተለያዩ የጉምሩክ ጣቢያዎች በመስክ በመገኘት በመካናይዜሽን ባለሞያዎች መሳሪያውን የመፈተሽ እና ጥራቱን የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል፡፡

በቆላማ የሀገራችን አካባቢዎች በመስኖ ለሚለሙ ሰብሎች በግብርና ማሽነሪ ቴክኖሎጂዎች የማስመጣትና ኪራይ አገልግሎት ላይ የተሰማሩ የግል ባለሃብቶችን በማስተባበር በዱብቲ እና አሳይታ በለማው የመስኖ ስንዴ የአጭዶ መውቂያ እና የሳር ማሰሪያ ቴክኖሎጂዎች ላይ የሰርቶ ማሳያ ተከናውኗል፡፡

በተመረጡ የአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማእከላት በግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት መስጠት ስራ የልህቀት ማዕከል እንዲሆኑ ለማስቻል በጊምቢቹ ወረዳ ፍቃደኛ ወጣቶች እና አርሶ አደሮችን የመመልመልና ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኙ ድጋፍ የመስጠት ስራ ተከናውኗል፡፡

በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀውን የማሽነሪ መጠለያ ዲዛይን መሰረት ሼድ ለገነቡ ወረዳዎች ለግብርና መካናይዜሽን ቴክኖሎጂ ኪራይ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የተመደቡ በቁጥር ስምንት የተለያዩ የቅድመ እና ድህረ ምርት ቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ከ110 የፈረስ ጉልብት ትራክተር ጋር ድጋፍ ተደርጓል፡

በጊምቢቹ ወረዳ የተጀመረውን ስራ በሌሎች ሥራው በሚከናወንባቸው ክልሎች ለማስቀጠል የሰልጥና፣ የዴሞንስትሬሽን፣ የክትትል እና የሶሻላይዜሽን ፕሮግራም ተከናውኗል፡፡

### 3.1.6 የኤክስቴንሽን አገልግሎት ማጠናከር

የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ/ከፊል አርሶ አደሮች ዕድገት በሁሉም ክልሎች የኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎችን ቁጥር ለማሳደግ 10.6 ሚለዮን ታቅዶ ሙሉ በሙሉ የተከናወነ ሲሆን አበወራ 6.6 ሚሊ. እማወራ 1.7 ሚሊ. ወጣት 0.96 ሚሊ. ባለትዳር ሰሴቶች 3.43 ሚሊ. ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

የሙሉ ፓኬጅ ተጠቃሚ ተሳታፊ ብዛት ወንድ 4,862,572 (69.9%) ሴት 893,266 (12.85%) ወጣት 808,152 (11.62%) ጥቅል አፈፃፀሙ 94.4% ነው፡፡ የሞዴል አርሶ፣ አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሮችን ወንድ 2,562,033 (69.02%) ሴት1,015,033 (27.34%) ወጣት 134,933 (3.64%) ሲሆን ጥቅል አፋፃፀሙ 94.7% ነው፡፡

እስካሁን በተሰጡ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ላይ የአርሶ፣ አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩን እርካታ ለመለካት በታቀደው መሠረት የተለያዩ መለኪያዎችን በማዘጋጀት በሁሉም ክልሎች ከትግራይና ቤኒሻንጉል ክልሎች ውጪ የእርካታ ዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል፡፡

የአርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩን የግብርና ኤክስቴንሽን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በተያዘው ዕቅድ መሠረት የአርብቶ አደር ኤክስቴንሽን ሥርዓት ሰነድ ተዘጋጅቷል፣ የአርሶና አርብቶ አደር የመስክ ትምህርት ቤት የአሰልጣኞች መመሪያም ተዘጋጅቷል፡፡

በምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር በማጠናከር ውጤታማ የኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት ይቻል ዘንድ ከሁሉም ክልሎች 13 ቀበሌዎችን በመምረጥ ከተቋማቱ ጋር የጋራ እቅድ በማቀድ ቀበሌዎቹን ሞዴል ለማድረግ የጋራ እቅድ በማዘጋጀት ሥልጠናዎች እየተሰጡ ነው፡፡

### 3.1.7 የግብርና ቴክኒክና ሙያ ስልጠና

በፌደራል ቴ/ሙ/ት/ሥ ኤጀንሲ በተዘጋጀ የውይይት መድረክ በመሳተፍ እና ከተቋሙ አመራሮች ጋር በመወያየት በአሁኑ ሰዓት የግብርና ዘርፍ ሥራ የአገር አቀፍ የገበያ ፍላጎት ጥናትን በጥራት ለማከናወን የሚያስችል ዝርዝር የዳሰሳ ጥናት፣ የአካሄድ እና የማስፈፀሚያ መመሪያ ሰነድ በመዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡

በግብርና ሚኒስቴር እና በማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬቱ የ10 ዓመት መሪ እቅድ ላይ ለኮሌጅ አመራሮች እና መምህራን በጥቅሉ 750 ሰዎችን ያሳተፈ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም ተከናውናል፡፡

በአለም ባንክና በሌሎች አጋር ድርጅቶች እንደሚደገፍ ታሳቢ ተደርጎ በተዘጋጀው Integrated Agricultural Development Project (IADP) ውስጥ የግብርና ቴ/ሙ/ት/ሥ/ ዘርፍ ትኩረት አግኝቶ እንዲያዝ በማስቻል የተለያዩ የዘርፉን 10 ዓመት መሪ ዕቅድ ለማስፈፀም የሚያስችሉ ፕሮጀክቶች ተካተው ተቀርፀዋል፡፡

በፌደራል ግብርና ኮሌጆች የአመራሮች እና መምህራን የደረጃ እድገት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የኮሌጅ አመራርና ሠራተኞች ማትግያ እና የመምህራን የስራ አፈፃፀም መገምገሚያ መመሪያዎችን በማዘጋጀት ለውሳኔ ቀርበዋል፡፡

በ11 የሥልጠና መስኮች (ሰብል ልማት፣ እንስሳት እርባታ፣ እንስሳት ጤና፣ ተፈጥሮ ሀብት፣ አነስተኛ መስኖ፣ ግብርና ሜካናይዜሽን (ኦፕሬሽን እና ሜይንቴይናንስ)፣ ኅ/ሥራ (ሥራ አመራር፣ ሂሳብ አያያዝ እና ግብይት) እንዲሁም መሬት አስተዳደር) በመደበኛ 9,750 (ወንድ 5,655 ሴት 4,095) የደረጃ IV ባለሙያዎች ትምህርትና ሥልጠና ለመስጠት የታቀደ ሲሆን፤ አስፈላጊው የኮቪድ-19 መከላከያ የቅድመ ጥንቃቄና የቅድመ ዝግጅት ስራዎች በማከናወን ሰልጣኞችን በየደረጃው ከታህሳስ 23/2013 ጀምሮ ወደ የኮሌጁ እንዲገቡ ተደርጎ የመማር ማስተማር ስራው እየተከናወነ ይገኛል፡፡

ለትምህርትና ስልጠናው በየኮሌጁ የገቡ ተማሪዎች አጠቃላይ ብዛት ወንድ 4,525፣ ሴት 2,804 በድምሩ 7,329 ነው፡፡ በማታና ተከታታይ በመካከለኛ ደረጃ ወንድ 1,408 ሴት 663 በድምሩ 2,071 ተማሪዎች እንዲሰለጥኑ ታቅዶ ወንድ 907 ሴት 464 በድምሩ 1,371 እየሰለጠኑ ይገኛሉ፡፡

ለእርሻ መካናይዜሽን ትምህርት ክፍል ለደረጃ 4 የጥገናና የኦፐሬሽን የሙያ ስልጠና መስክ የማስተማሪያ ማቴርያል ዝግጅትና የቫልዴሽን ስራ የተከናወነ ሲሆን በዓሳ ሀብት የሙያ ደረጃና ስርዓተ-ትምህርት ለመቅረፅ ከሚመለከተው ጋር የቅድመ-ዝግጅት ስራዎች እየተደረገ ይገኛል፡፡

ሰርቶ ማሳያዎች፤ ወርክሾፖች፣ ላብራቶሪዎች የማጠናከርና የማደራጀት ስራዎች በመስራት ለመማር ማስተማር፤ ለተግባር ልምምድና ለቴክኖሎጂ ብዜት ስራዎች ዝግጁ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

በቁጥር 5 ቴክኖሎጂዎችን ለማላመድ፣ ለማባዛት እና ለማሸጋገር ታቅዶ 6 ቴክኖሎጂዎች የማባዛትና የማሻጋገር ስራ ተከናውኗል፡፡ ወንድ 1,804 ሴት 1,312 በድምሩ 3,116 ሰልጣኞች አገራዊ የሙያ ብቃት ምዘና እንዲወስዱ ታቅዶ፤ ወንድ 1,363 ሴት 968 በድምሩ 2,331 ሰልጣኞች ምዘና የወሰዱ ሲሆን ወንድ 949 ሴት 572 በድምሩ 1,521 ሰልጣኞች የሙያ ብቃት ምዘናውን ማለፍ ችለዋል፡፡ ከተመዘኑት ሰልጣኞች የሙያ ብቃት ምዘናውን ያለፉ በመቶኛ 65.25 ነው፡፡

በ2012 የትምህርት ዘመን የምረቃ ስነ-ስርዓት ባላከናወኑ ኮሌጆች ለተመራቂ ተማሪዎች ማጠናቀቂያ ትምህርት በመስጠት በቁጥር ወንድ 1,077 ሴት 690 በድምሩ 1,767 ለደረጃ አራት የሚጠበቅባቸውን ትምህርትና ስልጠናቸውን ያጠናቀቁ ሰልጣኝ ተማሪዎች በደረጃ አራት እንዲመረቁ ተደርጓል፡፡

የቻይና መንግስት የተግባር ትምህርትና ስልጠናውን ለማጠናከር በእርዳታ የላካቸውን የተግባር ስልጠናው መስጫ የላቦራቶሪ ቁሳቁሶች ወደ የኮሌጆቹ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

በአጋርፋ ኮሌጅ የተማሪዎች መማሪያ፣ ቢሮና የመሰብሰቢያ አዳራሽ ግንባታ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ የፊዚካል ስራ አፈፃፀሙ 86.21% እና የፋይናንሻል አፈፃፀሙ 80.7% (ብር 75,739,380.91) ላይ የሚገኝ ሲሆን፤ በተመሳሳይ በኮሌጁ ሶስት ብሎክ የተማሪዎች ዶርሚተሪ ግንባታ እየተከናወነ ሲሆን፤ የፊዚካል ስራው አፈፃፀም 72.49% እና የፋይናንሻል አፈፃፀሙ 75% (ብር 75,693,751.61) ላይ ይገኛል፡፡

40 መምህራን አቅም ለማጎልበት ታቅዶ 25 (ወንድ 13 ሴት 12) በኮሌጆች በስራ ላይ ያሉ መምህራን ብቃታቸው ለማሳደግ የማስተርስ ዲግሪ ትምህርታቸው እንዲከታተሉ ዕድሉ ተሰጥቷል፤ በ2012 በጀት ዓመት የትምህርት ዕድል ለተሰጣቸው 39 መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችም አስፈላጊው ድጋፍ እየተደረገላቸው ሲሆን፣ ለ150 (ወንድ 130 ሴት 20) መምህራን ክፍተትን መሰረት በማድረግ ለ15 ቀናት በተፈጥሮ ሀብት /በGIS/ የሙያ መስክ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

ለ20 (ወንድ 17 ሴት 3) መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች (በወተት አመራረትና ግብይት ሰንሰለት፣ በዶሮ እርባታና በአግሮኖሚ የሙያ መስክ፣ የኢፌክቲቭ ቲቺንግ ስኪል (ETS) ፣ በቴክኖሎጂ ማላመድ፣ ማባዛት እና ማሸጋገር ላይ ለ70 ከየኮሌጁ ለተውጣጡ አካላት ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ58 (ወንድ 51 ሴት 7) የስራ ኃላፊዎች፣ መምህራንና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል።

18 የኮሌጅና የማስተባበሪያው የስራ ኃላፊዎች በቲቪቲ ረቂቅ ስትራቴጂ ሰነድ ማዳበር ፕሮግራም ላይ እንዲሳተፉ የተደረገ ሲሆን የ5ቱን ኮሌጆች እና የማስተባበሪያውን በፀደቀው የዓመቱ በጀት ተመስርቶ የስድስት ወራት የጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ዕቅድ በማዘጋጀት ለገንዘብ ሚኒስቴር በወቅቱ እንዲቀርብ ለማድረግ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ተከናውኗል።

በግብርና ሚኒስቴር የግብርና ቴክኒክ እና ሙያ ትምህርት ስልጠና ለረጅም ዓመታት ከፍተኛ የተሰብሳቢና የተከፋይ የሂሳብ ክምችት ሆኖ በመታየቱና በየጊዜው የኦዲት ግኝት በመሆን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሲያስወቅስ መቆየቱ ይታወቃል:: በመሆኑም ችግሩን ለመቅረፍ ሚ/ር መ/ቤቱ ከፍተኛ ሀላፊነት በመውሰድ የሂሳብ አጣሪ ቴክኒክ ኮሚቴ አቀቁሞ ሂሳቡ እንዲጣራ ሲያደርግ ቆይተዋል:: በዚሁ መሰረት በ2010 በጀት ዓመት በአዲስ መልክ የሂሳብ አጣሪ ቴክኒክ ኮሚቴው ሲቋቋም የነበረው እና ሰኔ 30/2012 ያለው የሂሳብ ሚዛን ከዚህ በታች ተመልክተዋል::

በ2010 በጀት ዓመት የተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛ ሚዛን ብር 69,736,371.39 ሲሆን ሚዛኑ ያልጠበቀ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 20,335,326.07 ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቱ ሲወጣ ትክክለኛ ሚዛን ከያዘው ተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛ ያልሆነው ተሰብሳቢ ሂሳብ አቀናንሶ ብር 49,401,045.32 እንዲሆን ምክንያት ሆነዋል:: በተመሳሳይ በ2012 በጀት ዓመት የተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛ ሚዛን ብር 48,259,807.36 ሲሆን ሚዛኑ ያልጠበቀ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 1,680,527.07 ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቱ ሲወጣ ትክክለኛ ሚዛን ከያዘው ተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛ ያልሆነው ተሰብሳቢ ሂሳብ አቀናንሶ ብር 46,579,280.29 ሆነዋል::

በመሆኑም የሂሳብ አጣሪ ቴክኒክ ኮሚቴው ሚዛኑ ያልጠበቀ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 18,654,799.00 ለማወራረድ የቻለ ሲሆን ስራው በሚሰራበት ጊዜ ሂሳቡ የአመዘጋገብ ችግር የነበረው በመሆኑ ትክክለኛ ተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን ሳይነካ ሀብትን በመንካት የተሰራ መሆኑ ከትክክለኛው የተሰብሳቢ ሂሳብ ከብር 69,736,371.39; ብር 21,476,564.03 እንዲወራረድ የተደረገ ሲሆን ብር 48,259,807.36 አሁን በመዝገብ ላይ ተመዝግቦ የሚገኝ ቀሪ ተሰብሳቢ ሂሳብ ሆኖ ይገኛል::

ተሰብሳቢ ሂሳብ በ2012 በጀት ዓመት በመዝገብ ተመዝግቦ የሚታየው ብር 4,498,321.46 ሲሆን ሂሳቡ ለረጅም ጊዜ የይገባኛል ጥያቄ የማይቀርብበት የደመወዝ; የአደራ እንዲሁም ልዩ ልዩ የግንባታ ስራ የማያዣ ተከፋይ ሂሳብ ሆኖ በየጊዜው የኦዲት ግኝት እየሆነ የመጣና በሂሳብ ማጣራት በሚከናወንበት ጊዜም መረጃ የታጣበት መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በቀን 12/4/2013 ዓ/ም ከገንዘብ ሚኒስቴር

በተፃፈ ደብዳቤ ሂሳቡ ከመዝገብ ለመሰረዝ እንዲቻል ስለ ሂሳቡ ዝርዝር መረጃ እንዲቀርብ በተጠየቅነው መሰረት በቂ መረጃ በማስደገፍ ተልኳል፡፡

በበጀት ዓመቱ በኮሌጆች በተለያዩ የገቢ ርዕሶች ብር 93,848,715.00 ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 60,231,340.00 መሰብሰብ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 64.18 በመቶ ላይ ይገኛል፡፡

በአምስቱም የፌዴራል ግብርና ኮሌጆችና በማስተባበሪያው ብር 369,020,000.00 ስራ ላይ ለማዋል ታቅዶ ብር 267,884,000.00 ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙም 72.59 በመቶ ነው፡፡

የመደበኛ ሥራዎችን ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ እና ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ በአምስቱም የፌዴራል ግብርና ሙ/ት/ሥ/ኮሌጆች የ2013 የትምህርት ዘመን የቅድመ ዝግጅት ስራ እና የየሩብ ዓመቱ የስራ አፈፃፀም በተመለከተ የክትትልና ድጋፍ ስራ ተሰርቷል፡፡

### 3.1.8 የዕፅዋት ጥበቃ አገልግሎት ማስፋት፣

ከተገልጋዮች ለሚቀርቡ በቁጥር 11 የተባይ መለየትና የመከላከል የምክር አገልግሎት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ 10 ተከናውኗል፡፡ (የትልቁ እህል ቦርቧሪ ባለባቸው አካባቢዎች በሰብል ምርት ማከማቻ የሚከሰቱ አደገኛና መደበኛ የጎተራ ተባዮች ላይ የክስተት ክትትልና መከላከል እንዲሁም በነጭ የማንጎ ስኬል የመከላከል ምክረ ሃሳብ እንዲሁም በማንጎ፣ በፓፓዬ፣ ብርቱካን፣ ስንዴ፣ ግሪሳ ወፍ፣ የበረሃ አንበጣና በምስጥ የልየታና መከላከል ተከናውኗል)፡፡

በ173 ወረዳዎች ላይ የበረሃ አንበጣ አሰሳና መከላከል ሥራ ለማከናወን ታቅዶ በ381 ወረዳዎች ላይ ተከናውኗል፡፡ (የወረዳ ድግግሞሽ አለው (አንድ ወረዳ ላይ ሁለት እና ከዚያ በላይ ስለሚከሰት) በ72 ወረዳዎች የአዲሱ መጤ ተምች አሰሳና መከላከል ሥራ ለማከናወን ታቅዶ በ15 ወረዳዎች ላይ ተከናውኗል፡፡

በአየር እና በምድር 4.2 ሚሊዮን ሄ/ር መሬት ታሰሶ 1.5 ሚሊዮን ሄ/ር መሬት የተወረረ ሲሆን **600,216** (በመርጫ መሳሪያ) እና **924,631** (በአውሮፕላን) ርጭት የመከላከል ስራ ተከናውኗል፡፡ **954,726 ሊትር** ኬሚካል በመጠቀም በ5 የርጭት አውሮፕላን ፤ 5 የርጭት ሄሊኮፕተሮች ፤ 3 የአሰሳ ሄሊኮፕተሮች ርጭት ተካሂዷል፡፡ በአጠቃላይ 1 ቢሊየን ብር የወጣ ሲሆን (400 ሚሊየን ብር) ከመንግስት የተመደበ ነው፡፡ የ2012/13 ምርት ዘመን ልምድ በመውሰድ ለ2013/14 ምርት ዘመን መከላከል ዝግጅት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት አሰሳ በ17 ወረዳ ውስጥ 229,807 ሄ/ር አሰሳ ተካሂዶ በ5,8181 ሄ/ር ላይ መከሰቱ የተረጋገጠ ሲሆን 1,230 ሊትር ኬሚካል በመጠቀም በ1,253 ሄ/ር የመከላከል ስራ ተከናውኗል፡፡

በ7 የግሪሳ ወፍ መራቢያ ስፍራዎች ልየታ ለማከናነው ታቅዶ 4 ተከናውኗል፡፡ ግሪሳ ወፍ ክትትል፤ አሰሳና የመከላከል ስራ መስራት በ18 የወፍ ማደሪያ ስፍራ ለማከናወን ታቅዶ በ15 የግሪሳ ወፍ ማደሪያ ስፍራ ተከናውኗል፡፡ የግሪሳ ወፍ ክትትል፣ አሰሳና የመንጋ ብዛት መገመትና መከላከል በማደሪያ ብዛት ለማከናወን ታቅዶ በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ሸዋ ዞን (ዱግዳ፣ ሉሜ፣ ቦራ፤ አዳሚ ቱሉ ወረዳዎች)፣ እና በአርሲ ዞን (ዝዋይ ዱግዳ ወረዳ) 17 ሚሊዮን የሚገመት የግሪሳ ወፎች በ275 ሄ/ር ላይ 550 ሊትር ፀረ-ወፍ ኬሚካል በመጠቀም መከላከል ተችሏል፡፡

በ7 ወረዳዎች ላይ የመደበኛ ተምች ክትትልና መቆጣጠር ለማድረግ ታቅዶ ይህንን የሚከታተል ባለሙያ በበረሃ አንበጣ አሰሳና መከላከል ተግባር ላይ ስለነበሩ አልተከናወነም፡፡

በ13 ወረዳዎች ድህረ ምርት ተባዮች አሰሳ በመስክና በማከማቻ በበልግ፣ መስኖና መኸር ወቅት ለማካሄድ ታቅዶ በ7 ወረዳዎች በኦሮሚያ ክልል (ቦረና ዞን ሞያሌ ወረዳ)፤ በሶማሌ ክልል (ሞያሌ ወረዳ) እና በደ/ብ/ብ/ህ/ክልል በደቡብ ኦሞ ዞን (በናፀማይ እና ሀመር ወረዳዎች)፤ በኮንሶ ዞን ካራት ዙሪያና ኬና ወረዳዎች እንዲሁም በቡርጂ ልዩ ወረዳ ላይ በትልቁ እህል ቦርቧሪና በሌሎች መደበኛ የጎተራ ተባዮች ላይ የክስተት ክትትል በማድረግ የጉዳት መንስኤ በመለየት በዘመናዊ የማከማቻ ዘዴ ከአካባቢው ማከማቻ ጋር በማነጻፀር ጥቅሙን በመለየት ቴክኖሎጂ እንዲጠቀሙ ምክረ ሃሳብ ተሰጥቷል፡፡

የእፅዋት በሽታዎችን አሰሳና መከላከል በበልግ፣ በመስኖና መኸር ወቅት በ211 ወረዳዎች ላይ በስንዴ ዋግ በ65 ወረዳዎች ለማከናወን ታቅዶ በ64 ወረዳዎች ተከናውኗል፤ በአገዳና በብርዕ ሰብሎች አረማሞ በ15 ወረዳዎች ለማከናወን ታቅዶ 17 ተከናውኗል፤ በቲማቲምና ድንች ብላይት በ12 ወረዳዎች ለማከናወን ታቅዶ በ14 ወረዳዎች ተከናውኗል፤ በበቆሎ ገዳይ ቫይረስ በ40 ወረዳዎች ታቅዶ በ37 ወረዳዎች ተከናውኗል፤ በባቄላ ጋልና ቸኮሌት ስፖት በ40 ወረዳዎች ታቅዶ በ40 ወረዳዎች ተከናወኗል እንዲሁም የእንሰት፣ ዝንጅብልና በርበሬ ባክቴሪያል ዊልት በ10 ወረዳዎች ሥርጭት ዳሰሳ ጥናት፣ መረጃ ማሰባሰብ፣ መረጃ መተንተን፣ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ አልተከናወነም፡፡

መጤ አረም ቁጥጥርና መከላከል ደንብና መመሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተከለሰውን ማፀደቅና የቁጥጥርና መከላከል ሠነዱን ተግባራዊ እንዲሆን መከታተል እቅድ ቢያዝም አልፀደቀም፡፡

በ30 ወረዳዎች የሳር ዘርና ቅጠለ ሰፋፊ አረሞች ቁጥጥርና መከላከል የአረም ሳምንት እንዲታወጅ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በ10 ወረዳዎች ተከነውኗል፡፡

በ5 ወረዳዎች የጥገኛ አረሞች (አሮባንኬ፣ አቀንጭራ የኑግ አንበሳ) ስርጭት ማጥናትና የተቀናጀ የአረም መከላከያ ስልቶችን በመጠቀም የመከላከል ምክረ ሃሳብ ለመስጠት ታቅዶ በ5 ወረዳዎች በኑግ አንበሳ ላይ ተከናወኗል፡፡

በ5 ወረዳዎች በመስኖ በሚለሙና ከፍተኛ የፀረ-ተባይ ርጭት በሚካሄድባቸው ወረዳዎች ተደጋጋሚ የፀረ-ተባይ ርጭት ያስፈለገባቸውን መንስኤዎችን ማጥናትና ምክረ-ሃሳቦች ለማቅረብ ታቅዶ አልተከናወነም፡፡

380,000 ሊትር ኢትዮላታየን 95% ዩ.ኤል.ቪ. ከአዳሚቱሉ የፀረ-ተባይ ማዘጋጃ ፋብሪካ ለመግዛት ታቅዶ 759,459 ሊትር ኢትዮላታየን 95% ዩ.ኤል.ቪ. እና 100,000 ሊትር ኢ.ሲ. ማላታይን ፀረ-ተባይ ኬሚካል ለወረርሽኝ ተባዮች መከላከል ግዥ ተፈፅሞ ተሰራጭቷል፡፡

2 አዲስና ነባር የአውሮፕላን ማረፊያ ሜዳ ግንባታ ጥናት ለማካሄድ በጀት ማፈላለግ ታቅዶ 3 ጥገና (ሽዋሮቢት፣ መቂ እና ኮንሶ) ጥገና የተደረገባቸው እና በጀት ተገኝቶ በላይኛው አዋሽ አግሮ እንዲስትሪ በመርቲ ወረዳ ላይ የአውሮፕላን ማረፊያ ሜዳ ተጠርጎ ተዘጋጅቷል፡፡

ለአርሶ አደሩ የዕፅዋት ተባዮች የልየታና የመከላከል የምክር አገልግሎት እየሰጡ ላሉ ከኦሮሚያ፣ ከአማራ፣ ከደ/ብ/ብ/ህ/ክልሎች፣ ከሲዳማ እና ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ለተውጣጡ እንዲሁም ከፌደራል ግብርና ሚኒስቴር ከተለያዩ ዳይሬክቶሬቶች (ከዕፅዋት ጥበቃ፣ ከሰብል ልማት፣ ከሆርቲካልቸር ልማት ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ከኤክስቴንሽን፣ ከዕፅዋት ጤናና ምርት ጥራት ቁጥጥር እና ከዕፅዋት ዝርያ፣ ለቀቃ፣ ጥበቃና የዘር ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬቶች) ለተውጣጡ 305 የልማት ጣቢያ ሰራተኞች፣ የክልል፣ የዞንና ወረዳ ባለሙያዎች እርስ በእርሳቸው የልምድ ልውውጥ አድርገዋል፡፡

በአዲሱ መጤ ተምች አሰሳ፣ ትንበያና ቅድመ ማስጠንቀቂያ አሰራር ለማጠናከር ከተለያዩ የግብርና ምርምር ማዕከላት፣ ከአለም አቀፍ የነፍሳት መካነ ጥናት፣ ከግብርና ሚኒስቴር እና ከክልል ግብርና ቢሮዎች ለመጡ ባለሙያዎች የ2 ቀናት የማነቃቂያ ሥልጠናና የልምድ ልውውጥ በአምቦ ግብርና ምርምር ማዕከል ተካሄዷል፡፡

በማህበረሰብ ተኮር የዕፅዋት ክሊኒኮች ላይ በተባይ ምርመራ፣ ልየታና የመከለካል የምክር አገልግሎት እየሰጡ ላሉ ለ305 ባለሙያዎች የልምድ ልውውጥና ማነቃቂያ በPlantwise Program ሥልጠና ተሰጥቷል ፡፡

ሁለገብ ላቦራቶሪው ተገንብቶ ወደ አገልግሎት በሚገባበት ወቅት ለአካባቢውና ለሰው ጤንነት ስጋት እንዳይኖር ከላብራቶሪው የሚወጣውን ፍሳሽ ለማስወገድ የሚያስችል የማስወገጃ ጥናት ለአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የቀረበውን የጥናት ውጤት ክትትል እንዲሁም ሁለገብ ላቦራቶሪ ዲዛይንና ግንባታ ክትትል እየተደረገ ነው፡፡

64 የተምች ፣ የበረሀ አንበጣ ወርሀዊ ቡለቲን ማዘጋጀት፣ የስንዴ ዋግ ቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃዎች አሰባስቦ በመተንተን ለማሰራጨት ታቅዶ 17 ተከናውኗል ፡፡

በ20 ወረዳዎች መጤ አረም (ፓርቲኒየም፣ ፕሮሶፒስና አጅራተም ሥርጭት ዳሰሳ ጥናት፣ መረጃ ማሰባሰብ ለማካሄድ ዕቅድ ተይዞ በ3 ወረዳዎች በኦሮሚያ ክልል (ሞያሌ፣ ሚዮ እና ኤሊወዬ) ወረዳዎች ላይ የፕሮስፒስ መከላከል እርምጃ እንዲወሰድ የምክር አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡

ለአዲሱ መጤ ተምች ማጥመጃ አገልግሎት ላይ የሚውል 400 ፌሮሞን ትራፕ ለማሰራጨት ታቅዶ 800 ፌርሞን ትራፕ ተሰራጭቷል፡፡

የተዛማችና ወራሪ ተባዮች መቆጣጠርና መከላከል ሀገራዊ አቅም ለመገንባት የርጭት አውሮፕላኖች፤ ሄሊኮፕተሮችና ድሮኖች ግዢ ድጋፍ ቢጋርና የፕሮጀክት ሀሳብ ተዘጋጅቶ ለዓለም ባንክ ቀርቦ ተደጋጋሚ ውይይቶች እየተደረጉ ሲሆን የአውሮፕላኖች አስተዳደር በተመለከተ ለሙያው ቅርበት ያላቸው የግል ካምፓኒዎችን በማወዳደር ከአሸናፊው ናሽናል አየር ርጭት ካምፓኒ ጋር የውል ስምምነት ተደርጓል፡፡

የበረሃ አንበጣ ርጭትና አሰሳ ክትትልና መረጃ ማዕከል በግብርና ሚኒስቴር ውስጥ በFAO ድጋፍ ተቋቁሟል፡፡

### 3.1.9 የእጽዋት ግብዓቶችና ምርቶች ጤንነት፣ ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ

የኢንስፔክሽን ስራ በቶን 1,302,000 ለማከናወን ታቅዶ 950,000 (72%)፣ የፋይቶሳኒተሪ ሰርተፊኬት መስጠት በቁጥር 58,284 ለማከናወን ታቅዶ 38,400 (65.6%) ፣ የማጠንት ክትትል በቶን 229,167 ለማከናወን ታቅዶ 156,000 (68%) ፣ የብቃት ማረጋጋጫ በቁጥር 917 ለማከናወን ታቅዶ 508 (55 %) ፣ የእፀዋት ማስገቢያ ፈቃድ መስጠት በቁጥር 1,746 ለማከናወን ታቅዶ 1,300 (74 %) የፀረ ተባይ እድሳትና ማስገቢያ ፈቃድ በቁጥር 1,650 ለማከናወን ታቅዶ 1c,530 (92.7%) ተከናውኗል፡፡

ከተለያዩ የምርምር ተቋሞች፣ ዩንቨርሲቲዎች እና የግል ኩባንያዎች የቀረቡ 100 ዕጩ ዝርያዎችን በመስክ ግምገማ ለማካሄድ ታቅዶ 112 ዝርያዎች (112%) በመስክ ተገምግመዋል፡፡ ከተገመገሙ ዝርያዎች ውስጥ አስፈላጊውን መረጃ በሟሟላት ለብሔራዊ ዝርያ አፅዳቂ ኮሚቴ ለመጨረሻ ውሳኔ የቀረቡ 112 ዝርያዎች ሲሆኑ 62 ዝርያዎች ሲጸድቁ/ሲመዘገቡ፣ 1 ዝርያ በግዚያዊነት ሲለቀቅ፣ 2 ተደግመዋል፣ 47 ወድቀዋል፡፡ በ2011/12 በጀት ዓመት የተለቀቁ ዝርያዎችን ዋና ዋና የባህሪ መገለጫ በማሰባሰብ የዝርያ መዝገብ ቁጥር 22 በማሳተም ለተጠቃሚዎች እንዲደረስ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በ2012/13 በጀት ዓመት የተለቀቁ ዝርያዎችን ዋና ዋና የባህሪ መገለጫ በማሰባሰብ የዝርያ መዝገብ ቁጥጥር 23 በሀርድ ኮፒ ለማሳተም ማተሚያ ቤት የተለከ ሲሆን በቅረቡ ለተጠቃሚዎች ተደረሽ ይደረጋል፡

የአትክልት ዝርያዎችን ከውጪ በማስገባትና ለአርሶአደሩ ለማቅረብ ጥያቄ ለሚያቀርቡ ለ15 የአትክልት ዘር አስመጪዎች የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ 17 ዘር አስመጪ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (113%) ተሰጥቷል፡፡

250 በተለያዩ የአትክልትና የሰብል ናሙናዎች በመውሰድ በላብራቶሪ የዘር ጥራት ፍተሻ ለማከናወን እና ዉጤት ለማሳወቅ ታቅዶ 256 (102%) የተለያዩ የአትክልት የሰብል ናሙናዎች ላይ የጥራት ፍተሻ ተካሂዶ ውጤቱ አገልግሎቱን ለማግኘት ጥያቄ ላቀረቡ ድርጅቶች እንዲያውቁት ተደርጓል፡፡ የአትክልት ዘር ከውጪ በማስመጣት የዘር ጥራት ፍተሻ ሳያከናውኑ ለተጠቃሚው የሚያከፋፍሉ 4 ካምፓኒዎች ላይ ክትትል በማድረግ የመጨረሻ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ ከየክልሎች የሚሰበሰብ 60 ዱፐሊኬት/ የተመሳሳይ ናሙና ላይ የጥራት ፍተሻ ለማድረግ በዓመቱ ታቅዶ 44 ናሙና መጥቶ የጥራት ፍተሻ ተደርጎ ለየክልሎቹ ውጤቱ ተልኳል፡፡

በዘር ህግ ማዕቀፎች ላይ በአግራ በጀት ድጋፍ ስልጠና መስጠት በአማራ፤ በኦሮሚያ እንዲሁም በደቡብ ክልሎች ስልጠና የተሳተፉ 285 ሲሆኑ ከዚህ ውስጥ ወንድ 231 ሴት 54 ናቸው። በዘር ጥራት ቁጥጥር በአማራ፤ በኦሮሚያ እንዲሁም በደቡብ ክልሎች ስልጠና የተሳተፉ 401 ሲሆኑ ከዚህ ውስጥ ወንድ 315 ሴት 86 ናቸው።

ከሆለታ ግብርና ምርምር ማዕከል ጋር በመተባበር ጥራቱ በተመሰከረለት የድንች ዘር አመራረት ላይ ከአምቦ፣ ከወልቂጤና ከደ/ማርቆስ የዘር ጥራት ቁጥጥር መዕከላት እንዲሁም በዙሪያቸው ለሚገኙ አምራቾች ወንድ 63 ሴት 17 በድምሩ 80 ለሆኑ ተሳታፊዎች ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል።

## 3.2 ገበያ ተኮር የእንስሳትና ዓሳ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ

### 3.2.1 የወተት ምርትና ምርታማነት

በ2013 በጀት ዓመት 4,827 ሚ/ሊ ሊትር ወተት ለማምረት የታቀደ ሲሆን በዓመቱ መጨረሻ ወር ላይ 7,225 ሚ/ሊ ሊትር ወተት ለማምረት ተችሏል፤ አፈጻጸሙም 150% ሲሆን በማ/ስ/ኤ መረጃ መሰረት የግመል ወተት በጣም በመጨመሩ ነው። ከዳልጋ ከብት ላም ወተት ምርት 3,978 ሚ/ሊ ሊ/ር ወተት ለማምረት ታቅዶ 4,692 ሚ/ሊ ወተት የተመረተ ስሆን አፈጻጸሙም 117.9% ልደርስ ችሏል። የፍየል ወተት ምርትን ከቆላው ስነ ምህዳር በያዝነዉ በጀት ዓመት 0.099 ሚሊየን ሊ/ር ለማድረስ የታቀደ ሲሆን እስከ 2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ወር 0.099 ሚ/ን ሊ/ር የተመረተ ሰሆን አፈጻጸሙም 100% ልደርስ ችሏል። የግመል ወተት ምርት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ 710 ሚሊየን ሊ/ር ለማድረስ ታቅዶ 2,434 ሚ/ሊ ሊትር የተመረተ ስሆን የ2013 አፈጻጸም 342% ልደርስ ችሏል።

### 3.2.2 የቀይ ሥጋ፤ ቆዳ እና ሌጦ ምርትና ምርታማነት

ከዳልጋ ከብት፣ ከበግ፣ ከፍየልና ከግመል 355 ሺህ ቶን ስጋ ለማምረት ታቅዶ 345 ሺህ ቶን (98.25%)) ማምረት ተችሏል። ከዳልጋ ከብት 217 ሺህ ቶን ስጋ ለማምረት ታቅዶ 214 ሺህ ቶን (97.2%) ማምረት ተችሏል። ከበግ 78 ሺህ ቶን ስጋ ለማምረት ታቅዶ 76 ሺህ ቶን (97.4%) ማምረት ተችሏል። ከፍየል 58 ሺህ ቶን ስጋ ለማግኘት ታቅዶ 53.6 ሺህ ቶን (92.4%) ተከናውኗል። ከግመል 2 ሺህ ቶን ስጋ ለማምረት ታቅዶ 1.3 ሺህ ቶን (65%) ማምረት ተችሏል።

ከዳልጋ ከብት፣ ከበግና ከፍየል የቆዳና ሌጦ ምርት 15.96 ታቅዶ 15.15 ሚሊየን ሲከናወን አፈጻጸሙም 95.04% ነው። ቆዳ 1.812 ሚሊየን ለማምረት ታቅዶ 1.81 ሚሊየን (99.6%) ማምረት ተችሏል። የበግ ሌጦ 7.75 ሚሊየን ለማምረት ታቅዶ 7.23 ሚሊየን (93.41%) ማምረት ተችሏል። ከፍየል 6.34 ሚሊየን ለማምረት ታቅዶ 6.1 ሚሊየን የተመረተ ሲሆን አፈፃፀሙም 95.46% መሆኑን ያሳያል።

### 3.2.3 የዶሮ ሥጋና እንቁላል ምርትና ምርታማነት

በ2013 በጀት ዓመት ዓመታዊ የዶሮ ሥጋና እንቁላል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በተያዘ እቅድ 51.5 ሺህ ቶን የዶሮ ሥጋ ለማምረት ታቅዶ 70 (+100%) ሺህ ቶን ስጋ ተመርቷል፡፡ በተመሳሳይ 3,047.5 ሚሊየን እንቁላል ለማምረት ታቅዶ 2,771.13 ሚሊየን እንቁላል የተመረተ ሲሆን ይህም የእቅዱን 90.9% ማከናወን ተችሏል፡፡ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በዓመቱ 26 ሚሊዮን የአንድ ቀን ጫጩቶችን ለማሰራጨት ታቅዶ 24.5 ሚሊዮን ጫጩቶችን ይህም የእቅዱን 94.23 በመቶ ለማሰራጨት ተችሏል፡፡

### 3.2.4 የዓሳ ምርትና ምርታማነት

በ2013 የዓሳ ምርት ከሀይቆች 52,000 ቶን፣ ከግድቦችና ትንንሽ ውሀ አካላት 15,000 ቶን፣ ከወንዞች 6,000 ቶን፣ ከዓሣ ግብርና (ኩሬ) 320 ቶን በአጠቃላይ 73,000 ቶን የዓሣ ምርት ለማምረት ታቅዶ ከሀይቆች 41,500፣ ከግድቦችና ከትንንሽ የውሀ አካላት 15,300፣ ከወንዞች 3,200 በአጠቃላይ 60,000 ቶን ተከናውኗል፡፡

በኩሬ የዓሣ ዕርባታ 440 ቶን ታቅዶ 534 ቶን ተመርቷል ማለትም (+100%) በመቶ ተከናውኗል፡፡ የደረቅ ዓሣ/ በጨው የተዘጋጀ የዓሳ ምርት /ኤክስፖርት በተመለከተ 1200 ቶን ታቅዶ 3,926 ቶን ተመርቷል፡፡ በጨው የተዘጋጀና የደረቀ የዓሣ ምርት ለጎረቤት ሃገሮች ኤክስፖርት የሚደረግ የዓሣ ምርት ውጤት ነው፡፡

በዓሣ ማምረት ጫና የተጎዱ የውሀ አካላት ላይ የዓሣ ሀብት አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት የውሃ አካላት ጥበቃና ክትትል ተደርጎላቸው ዓሳ ምርት ሳይቀንስ በዘላቂነት እንዲመረት ለማድረግ 4 የውሀ አካላት ላይ ለማከናውን ታቅዶ በጣና ሃይቅና በተከዜ ግድብ በሁለቱ የውሀ አካላት የዓሳ ሃብቱ ከጉዳት ለመጠበቅና እንዲያገግም የማድረግ ስራዎች ተከናውኗል፡፡

በ2013 በጀት ዓመት የዓሳ ማስገር ፈቃድና መታወቂያ ለአስጋሪዎች የሚሰጠው በአማራ ክልል ብቻ ሲሆን በክልሉም ለ5,000 አስጋሪዎች የማስገር ፈቃድ መታወቂያ ለመስጠት/ለማደስ ታቅዶ 2,945 ማከናወን ተችሏል፣ ከታቀደው እቅድ አንጻር ክንውኑ አነስተኛና 59 በመቶ ሊሆን ችሏል፡፡

### 3.2.5 የማር ሰምና የሐር ኩብኩባ ምርትና ምርታማነት

የማር ሰምና የሀር ኩብኩብ ምርትን ከማሳደግ አንጻር በ2013 በጀት ዓመት 64.4 ሺህ ቶን የማር ምርት 5.9 ሺህ ቶን የሰም ምርትና 33 ቶን ሀር ኩብኩባ ይመረታል ተብሎ ታቅዶ 129 ሺህ ቶን ማር፣ 6 ሺህ ቶን ሰምና 32.6 ቶን የሀር ኩብኩባ የተመረተ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 124.8 ሺህ ቶን ማርና 3.8 ሺህ ቶን ሰም ከባህላዊ ቀፎ፤0.92 ሺህ ቶን ማርና 0.92 ቶን ሰም ከሽግግር ቀፎና፤ 3.6 ሺህ ቶን ማርና

1.28 ከፍሬም ቀፎ የተመረተ ነው፡፡ ሁሉም አፈፃፀም ከዕቅድ በላይ ሲሆን 2013 በጀት ዓመት አፈጻጸም 200% የተከናወነ ነው፡፡

### 3.2.6 የመኖ ምርትና ምርታማነት ማሳደግ

በ2013 በጀት ዓመት ከሁሉም የእንስሳት መኖ ምንጮች (የተፈጥሮ ግጦሽ፣ የሰብል ተረፈ ምርት፣ በመስኖ የለማ መሬት፣ በጓሮ መኖ ልማት፣ በወል ግጦሽ መሬት የለማ መኖ፣ ወዘተ) 154 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ታቅዶ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ 133.3 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 86.6 በመቶ ነው፡፡ አፈፃፀሙ የተሻለ የሆነበት ምክንያት በዋናነት በዚህ ዓመት የዝናብ ስርጭቱ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች የተሻለ በመሆኑ እንዲሁም የመኖ ዘር እና ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት ላይ በፌደራልና በክልሎች እስከ ወረዳ ጽ/ቤት በጀት በመመደብ የአቅርቦት ስራዎችን በመስራታቸዉ የህብረተሰቡ ግንዛቤ ከጊዜ ወደ ግዜ እየተሻሻለ በመምጣቱ እና ከተፋሰስ ልማት ስራዎች ጋር በማቀናጀት አስሮ/ የተገደበ ማስጋጥ ስራዎች በተጠናከረ መልኩ መስራት በመቻሉ ነዉ፡፡

የተለያዩ የተፈጥሮ ግጦሽ የማሻሻያ ስትራቴጂዎችን በመተግበር እና ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ 50.2 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ታቅዶ 40.3 ሚ/ን ቶን ለማምረት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 80.3 በመቶ ነው፡ ፡የተሻሻለ መኖን ለማልማት ፓኬጆችን በማዘጋጀትና ድጋፍ በማድረግ 10 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ታቅዶ 9.68 ሚ/ን ቶን ለማምረት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 96.8 በመቶ ነው፡፡ ለዚህም አፈጻጸሙ በዋናነት የመኖ ዘር ላይ በፌደራልና በክልሎች እስከ ወረዳ ጽ/ቤት በጀት በመመደብ የአቅርቦት ስራዎችን በመስራታቸዉ የህብረተሰቡ ግንዛቤ ከጊዜ ወደ ግዜ እየተሻሻለ በመምጣቱ እና ከተፋሰስ ልማት ስራዎች ጋር በማቀናጀት አስሮ/ የተገደበ ማስጋጥ ስራዎች በተጠናከረ መልኩ መስራት በመቻሉ ነዉ፡፡

በ2013 በጀት ዓመት የሰብል ተረፈ ምርትን በተገቢዉ በማሰባሰብ ለመጠቀም እንዲቻል 64.9 ሚ/ን ቶን በማሰባሰብ በተገቢዉ በማከማቸት ጥቅም ላይ እንዲዉል ለማድረግ ታቅዶ 58.6 ሚ/ን ቶን የተሰበሰበ ሲሆን አፈፃፀሙ 90.2 በመቶ ነው ይህም የአሰባሰቡ ስራ በንቅናቄ የተፈጸመ በመሆኑ ነዉ፡፡ የኢንዳስትሪ (ስኳርና ሌሎች) ተረፈ ምርቶችን 4.2 ሚ/ን ቶን በማምረት ጥቅም ላይ እንዲዉል ለማድረግ ታቅዶ 6 ሚ/ን ቶን በማምረት ከእቅድ በላይ ተፈጽሟል፡፡ ለዚህም አፈጻጸም የተሻለ መሆን የአርሶ አደሩ በተሻሻለ የእንስሳት እርባታ በተለይም በተሻሻለ የዶሮ እርባታ ተግባር ላይ ያለዉ ፍላጎት በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መምጣት በዚህም የመኖ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋትና በተሻለ አቅም መስራት መቻላቸዉ ነው፡፡ የወል ግጦሽ መሬትና ሬንጅላንድን የተለያዩ ማሻሻያ ስትራቴጂዎችን በመጠቀምና ድጋፍ በማድረግ 22.7 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ታቅዶ 17.6 ሚ/ን ቶን የተመረተ ሲሆን አፈፃፀሙ 77.5 በመቶ ነው፡፡ እንዲሁም ከግል የአርሶ አደር ግጦሽ መሬትና ሬንጅላንድን በማሻሻል 1,791.30 ሺ/ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ታቅዶ 1,080 ሺህ ቶን ተመርቷል አፈጻጸሙም 60.3 በመቶ ነው፡፡

የመኖ ዘር ምርታማነትን በማሳደግና ጥራት ያለዉ የተሻሻሉ የመኖ ዘሮች 3.9 ሺህ ቶን ለማምረት ታቅዶ 2.8 ሺህ ቶን መኖ ዘር ለማምረት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 71.7 በመቶ ነው፡፡

በሁሉም ስነ ምህዳር በመስኖ የመኖ ማልማት ትግበራ ላይ የስልጠናና የመስክ ላይ ድጋፍ በማድረግ በ2013 በጀት ዓመት 15,059.7,ሄ/ር መሬት በመስኖ ለማልማት ታቅዶ 19,515 ሄ/ር መሬት በማልማት ከእቅድ በላይ ተፈጽሟል፡፡ ለዚህም በዋናነት የደቡብና አማራ ክልሎች የተሻለ ስራዎች መስራት መቻላቸውን ሪፖርታቸው ያሳያል፡፡

የመኖ ዘር ምርታማነትን በማሳደግና ጥራት ያለዉ የተሻሻሉ የመኖ ዘሮች 3.4 ሺህ ቶን ለማምረት ታቅዶ 2.8 ሺህ ቶን መኖ ዘር ለማምረት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 82.3 በመቶ ነው፡፡

### 3.2.7 የእንስሳት ዝርያን ማሻሻል

በ2013 በጀት ዓመት 1,400,000 ዶዝ አባለዘር ለማምረት ታቅዶ 1,096,150 ዶዝ የዕቅዱን 78% ዶዝ አባለዘር እንዲመረት ተደርጓል፡፡ ከ2013 ዓመት አጠቃላይ ምርት ውስጥ 884,125 ዶዝ በኢንስቲትዩቱ የተመረተ ሲሆን ቀሪዉ 212,025 ዶዝ በክልሎች አባለዘር ማምረቻ ማዕከላት የተመረተ ነዉ፡፡

የአባለዘር ሥርጭትን በተመለከተ በእስክ 2013 ዓመት መጨረሻ በክልሎችና በኢንስቲትዩቱ 1,400,000 ዶዝ አባለዘር ለማሰራጨት ታቅዶ 786,488 ዶዝ አባለዘር የዕቅዱን 56% ተከናውኗል፡፡ ይህ ስርጭት በክልሎች እና በኢንስቲትዩቱ የተሠራጨዉን ያካተተ ሲሆን 717,670 ዶዝ በኢንስቲትዩቱ ሲሠራጭ ቀሪዉ 68,818 ዶዝ በአራቱ የክልሎች አባለዘር ማምረቻ ማዕከላት የተሠራጨ ነው፡፡ ክንውኑ ከዕቅዱ ዝቅ ያለው አብዛኞቹ ክልሎች የድቀላን ሥራ በመደበኛ ከሚሠሩት ውጪ በሲንክሮናይዜሽን ለማዳቀል ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የእንስሳት ለማዳቀል አቅዶ የነበረ ቢሆንም በሆርሞን እጥረት ምክንያት ወደ ሥራ ባለመግባቱ፣ ክልሎች፣ የምርምር ማዕከላት፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና በግል ዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች መጥተው ባለመውሰዳቸው ነው፡፡

በ213 በጀት ዓመት መጨረሻ በሶስት የዝርያ ዓይነቶች የርቢ ፕሮግራም ለማዘጋጀት በታቀደው መሠረት በሀገሪቱ ዉስጥ በዘርፉ ከፍተኛ ልምድ ያላቸዉን ባለሞያዎች በማሰባሰብ በሦስት የእንስሳት ዝርያ ዓይነት ማለትም በፎገራ ወተት ዳልጋ ከብት፣ በዶዮገና እና በሆሮ አነስተኛ አመንዣኪ እንድሁም በሆሮ ዶሮ ሶስት የርቢ ፕሮግራሞች ተዘጋጅተዋል፡፡ በተፈጥሮ ጥቂ የእንስሳት ዝርያን ለማሻሻል የሚውሉ ኮርማዎች የአጠቃቀም መመሪያ ረቂቅ ሰነድ ተዘጋጅቶ የማጥራት ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

ከብዝሃ-ሕይወት ጋር በቅንጅት ለመስራት በተፈረመው የመግባቢያ ሰነድ መሰረት ኢንስቲትዩቱ ዝርያቸው እየተመናመኑ ያሉትን እንስሳት አባለዘር ማምረትን በተመለከተ በ2013 ዓመት 900 ዶዝ አባለ ዘር

ለማምረት ታቅዶ 6,798 ዶዝ የኢሮቢ ኮርማ አባለዘር እና 2,182 ዶዝ የሼኮ ኮርማ አባለዘር በድምሩ 8,980 ዶዝ አባለ ዘር አምርቶ እየጠበቀ ይገኛል፡፡ በዚህም አፈፃፀሙ 99.7% ላይ ይገኛል፡፡

በ2013 ዓመት መጨረሻ 385,000 ሊትር ፈሳሽ ናይትሮጂን ለማምረት ታቅዶ 317,011 ሊትር የዕቅዱን 82.3% ሊትር ፈሳሽ ናይትሮጂን እንዲመረት ተደርጓል፡፡ ከዚህ ውስጥ በኢንስቲትዩቱ 57,692 ሊትር ቀሪው 25,9319 ሊትር በአራቱ የክልሎች ፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ማዕከላት የተመረተ ነዉ፡፡ በኣዓመቱ መጨረሻ 346,500 ሊትር ፈሳሽ ናይትሮጂን ለማሠራጨት ታቅዶ 244,819 ሊትር የዕቅዱን 71% ሊትር ፈሳሽ ናይትሮጂን እንዲሠራጭ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ውስጥ 201,927 ሊትር በክልሎች የተሠራጨ ሲሆን ቀሪዉ 42,892.5 ሊትር ደግሞ በኢንስቲትዩቱ የተሠራጨ ነው፡፡

### 3.2.8 የእንስሳት ጤና አጠባበቅ ማጎልበት

በ2013 በጀት ዓመት ለተለያዩ የሀገራችን ክልሎች 120 ሚሊ/ዶዝ ክትባት ለማሰራጨት ታቅዶ 128 ሚሊ/ዶዝ ክትባት ለማሰራጨት ተችሏል:: ይህም በንጽጽር 100% ነው፡፡

ለክትባት መበጥበጫ የሚሆን 85,237 ሊትር ጨዋማ ውሃ ለማሰራጨት ተችሏል፡፡ ለዚህም 71,680,560 ብር ለክትባት ግዥ ወጪ ተደርጓል:: ስለሆነም ከፍተኛ የሆነ የበጀት ክፍተት ያሳያል፡፡

ለስምጥ ሸለቆ ትኩሳት እና ለውርጃ በሽታ 128,179 በግና ፍየል ለመመርመር ታቅዶ 1,582 ተከናውኗል: ለአፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆን የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መከሰት ምክንያት ከመሆኑም በለይ አፋጻጸሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት የምርመራ ጥያቄ ባለመቅረቡ እና ለእቅዱ ማስፈፀሚያ ወጪን በሚመለከት ለማዕከሉ የተፈቀደው የ2013 በጀት በቂ አለመሆኑን ነው፡፡

በስጋት ላይ የተመሰረተ የክትባት አገልግሎት ሽፋንን 89% የታቀደ ሲሆን ፤ከክልሎች በተሰበሰበው መረጃ መሰረት 89% የክትባት ሽፋን አገልግሎት ማድረስ ተችሏል፡፡

2.2 ሚሊዮን የእንስሳት የቅድመ ዕርድ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ 1,829,654.802 (83.16%) እንስሳት ለመመርመር ተችሏል፣ 2.18 ሚሊዮን እንስሳት የድህረ ዕርድ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ 1,805.556 (82.82%) እንስሳት መመርመር ተችሏል፣18.6 ሺ.ህ ቶን ሥጋና 1.4 ሺ.ህ ቶን ተረፈሥጋ ምርት ላይ ምርመራ በማድረግ ወደ ውጪ እንዲላክ ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ 15,315.42 (82.33%) ቶን ሥጋና 1,950.33 (139.309%) ቶን ተረፈ ሥጋ ላይ ምርመራውን በማካሄድ ወደ ውጪ እንዲላክ ማረጋገጫ ተሰጥቷል፣ 8,000 የጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ 8,634 (104.18 በመቶ) የጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የመስጠት ተግባር በማከናወን ኤክስፖርቱን ለመደገፍ ተችሏል፡፡

ለኤክስፖርት ሥጋ ዕርድ ለምርመራ የቀረቡ እንስሳት ከዓምናው ተመሳሳይ አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር በ 11,012 እንስሳት ብልጫ ያሳየ ሲሆን የስጋ ኤክስፖርት አፈጻጸም ከዓምናው ተመሳሳይ ወቅት አፈጻጸም

ጋር ሲነጻጸር ደግሞ 112.1 ቶን የጨመረ ቢሆንም በተረፈ ሥጋ ኤክስፖርት ግን በ211 ቶን የቀነሰ እንደሆነ ለመገምገም ተችሏል፡፡ በመሆኑም በአጠቃላይ የሥጋው ኤክስፖርት ከዓምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር ጭማሪ ያሳየ ቢሆንም ይህን ያህል የጎላ ለውጥ እንደሌለውና ተመሳሳይ እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል፡፡

የመንግስትና የግል ሴክተሩን አቅም አቀናጅቶ በእንስሳት ልየታና ምዝገባ ስርዓት ስር የሚያልፉ የዳልጋ ከብት ቁጥር በዓመቱ 60,000 ለማድረስ ታቅዶ 3,947 የዳልጋ ከብት በእንስሳት ልየታና ምዝገባ ስርዓት ክትትል ተደርጎባቸው ወደ ውጭ ሀገር ኤክስፖርት ተደርገዋል፡፡ በተጨማሪም 1,793 የዳልጋ ከብት ታግ ተደርገው በማድለቢያ ቦታ በእንስሳት ልየታና ምዝገባ ስርዓት ክትትል እየተደረገባቸው ይገኛል፡፡ በዚህም መሰረት የእንስሳት ልየታና ምዝገባ ስርዓት ተግባራዊ በማድረግ የቁም እንስሳት ላኪዎች እና አድላቢዎች ወደ ውጭ ሀገር የዳልጋ ከብት እንዲልኩ ተደርጓል፡፡ 17 ባለድርሻ አካላት በእንስሳት ልየታ ምዝገባ ስርዓት ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ስለ እንስሳት ልየታና ምዝገባ ስርዓት ጠቀሜታን ጨምሮ አስፈላጊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማትና የሰው ሃይል እንዲያሟሉ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡

የእንስሳት የወረዳዎችን ወርሃዊ የእን/በሽታ ፍንዳታ ሪፖርት የመላክ ምጣኔና ጥራትን አሁን ካለበት 76% ወደ 85% ማድረስ (DOVAR-II)፡- በድረ-ገጽ የሚታገዘውን ወርሃዊ የእንስሳት በሽታ ሪፖርት ማቅረቢያና ማደራጃ ስርዓት (DOVAR-2) የማሻሻል ሥራ 100% ለማድረስ ታቅዶ የዕቅዱን ሙሉ ለሙሉ ማከናወን ተችሏል፡፡ የወረዳዎች ወርሃዊ የበሽታ ፍንዳታና የክትባት ሪፖርት (Disease Outbreak and Vaccination Reporting (DOVAR)) ምጣኔም 78.8% ደርሷል፡፡ በተጨማሪም ADNIS እና SILABን በማስተሳሰር የእንስሣት በሽታዎች ፍንዳታ መረጃ ወደ ላቦራቶሪ የሚደርስበት እና ምርመራ የሚካሔድበትን አሠራር በመዘርጋት ላይ እንገኛለን፡፡

በ2013 በጀት ዓመት ለ285 ሺህ ኤክስፖርት ለሚደረጉ ዳልጋ ከብቶች የጤና ምርመራ አድርጎ አለም አቀፍ የጤና ሰርተፍኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ28 ሺህ የዳልጋ ከብቶች ምርመራ ተደርጎላቸው ወደ ተቀባይ ሃገሮች እንዲላኩ ተደርጓል፡፡ ይህም 10 በመቶ ተከናውኗል፡፡ ኤክስፖርት ለሚደረጉ 465 ሺህ በግና ፍየል የኢንስፔክሽን እና ሰርተፍኬሽን እንዲሁም የክትባት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ 323,419 ሺህ በግና ፍየል የክትባት እንዲሁም እንደተቀባዩ ሃገር መስፈርት መሰረት የደም ምርመራ ተደርጎላቸው እንዲወጡ ተደርጓል፡፡ ይህም 54 በመቶ አፈጻጸም ሆኗል፡፡ ለ90 ሺህ ኤክስፖርት ለመሆን ለተዘጋጁ ግመሎች የኢንስፔክሽን እና ሰርተፍኬሽን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ17,343 ሺህ ግመሎች የኳራንቲን አገልግሎት ተሰጥቷቸው ወደ ተቀባይ ሀገር እንዲሄዱ ተደርጓል ይህም 18 በመቶ አፈጻጸም ሆኗል፡፡

ለ50 ቶን ዓሳ ምርመራ እና ሰርተፍኬሽን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 82.9 (166%) ቶን አሳ የጥራት ማረጋገጫ ተሰጥቷል፤100 ቶን ለኤክስፖርት የተዘጋጀ ሰም ጥራቱን አረጋግጦ ሰርተፍኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ 124 (134%) ቶን ሰም የጥራት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ተሰጥቷል፡፡

ቁብ ዶሮ ለ30,000 የጤና ሰርተፍኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ 20,000 (72%) የሰርተፍኬሽን አገልግሎት ተሰጥቶ እንዲላኩ ተደርጓል፡፡ ለ8 ሚሊዮን የበግና ፍየል ቆዳ የኢንስፔክሽንና ሰርተፍኬሽን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ 1.5 ሚሊየን (19%) ሰርተፍኬሽን ተከናውኗል፡፡ ለ20 ሺህ ቶን ስጋ በቦሌ ኳራንቲን ጣቢያ ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ ለ11,620 ቶን ስጋ ምርመራ አገልግሎት ተሰቷቸው ከሀገር እንዲወጣ የይለፍ ፍቃድ የተሰጠ ሲሆን ይህም እቅድ ከክንውን አንጻር 58% ነው፡፡

### 3.2.9 የበሽታ ዳሰሳ እና ቅኝት ስርዓት

ለስምጥ ሸለቆ ትኩሳት እና ለውርጃ በሽታዎች ምርመራ 128,180 በግና ፍየል ለመስጠት ታቅዶ 1,582 እንዲሁም ለ3,228 ግመል ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ 851 ምርመራዎች ተከናውኗል፡፡ ለ73 የእንስሳት በሽታ ፍንዳታ ክስተቶች ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ ለ54 (74%) የበሽታ ፍንዳታዎች አስፈላጊው የምርመራ ውጤትና ሙያዊ ድጋፍ ለመስጠት ተችሏል:: ምላሽ የተሰጠባቸ ዋና ዋና በሽታዎችም መካከል PPR, NCD, Fowltyphoid, MER-COV, CCPP, CBPP, anthrax እና LSD ይገኙበታል፡፡ አፈፃፀሙ የቀነሰበት ዋና ምክንያትም የእንስሳት በሽታ ፍንዳታ በወቅቱ ካለው የአየር ንብረት፣ አካባቢያዊ ሁኔታ፤ የእንስሳት ዝውውርና ሌሎች መሰል ምክንያቶች የተነሳ ሊቀነስ ወይም ሊጨምር ስለሚችል ሲሆን ለማዕከሉ ምላሽ እንዲያገኙ ሪፖርት ለተደረጉት ግን ሙሉ በሙሉ ምላሽ አግኝተዋል፤ አስፈላጊው ሙያዊ ምክረ-ሀሳብም ተሰጥቷል፡፡

### 3.2.10 የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሽፋንን ማሳደግ

የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ዳግም ወረራ ለመከላከል የተሸፈነ መሬት ውስጥ 83,848 ካ.ኪ.ሜ ለማከናወን ታቅዶ 84,100.6 ካ.ኪ.ሜ የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም 100.3 በመቶ ማከናወን ተችሏል: ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የፀዳ መሬት 73,361 ታቅዶ 49,921.24 ሲሆን አፈጻጸሙም 68 በመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

የገንዲ በሽታ ስርጭት መጠንን ለመለየት በተደረገው የደም ናሙና ምርመራ መሠረት ሶስት አይነት የገንዲ በሽታ አምጪ ተዋስያን ማለትም (T.Congolense T.Brcei, እና T.Vivax) ምርመራ ለተደረገላቸው እንስሳት በበሽታው ለተጠቁና የቀይ የደም ህዋስ መጠናቸው (PCV) ከ 20 በመቶ በታች ወርዶ ለተገኙት እንስሳት ከእንስሳቱ የደም ምርመራ ጎን ለጎን በአራቱም

ማዕከላት ለ20,800 እንሰሳት የህክምና አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ16,726 እንስሳት የህክምና አገልግሎት መስጠት በመቻሉ ከታቀደው ዕቅድ አንፃር 80.4 በመቶ ለማከናወን ተችሏል፡፡

## 3.3 የግብርና ግብዓት አቅርቦትና ምርት ግብይት

### 3.3.1 የሰብል ግብዓት አቅርቦት

ለ2012/13 ምርት ዘመን ጥቅም ላይ የሚውል የተለያዩ የአፈር ማዳበሪያ 17.3 ሚ ኩንታል ለማቅረብ ታቅዶ 14.5 ሚሊ. (83.8%) ማቅረብ ተችሏል፡፡ ከቀረበውም ውስጥ ም 14.07 ሚሊ. (96%) ለአርሶ እና ከፊል አርብቶ አደሮች ተሰራጭቷል፡፡

የ2013/14 ምርት ዘመን የአፈር ማዳበሪያ 18.5 ሚሊ ኩንታል ለማቅረብ ታቅዶ 15.8 ሚሊ (84 በመቶ) ቀርቧል፣ ከባለፈው አመት ተማሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃር የ12 በመቶ ብልጭ አሳይቷል፡፡ ለተጠቃሚ 1.1 ሚሊ (60 በመቶ) ተሰራጭቷል፣ ከባለፈው አመት ተማሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃር የ12 በመቶ ብልጫ አሳይቷል፡፡

ለ2012/13 ምርት ዘመን ለአርሶ እና ለከፊል አርብቶ አደሩ የተለያዩ የድቃይ የሆኑ እና ያልሆኑ የተለያዩ ምርጥ ዘሮች ፍላጎት 1 ሚሊ ለማቅረብ ታቅዶ 0.812 ሚ ኩንታል (74.5%) በማቅረብ ከቀረበው ውስጥ 0.745 ኩንታል (92%) ተሰራጭቷል፡፡ ለየአርሶ/የከፊል አርብቶ አደሩን የምርጥ ዘር ፍላጎት መሰረት በማድረግ በወቅቱ እንዲቀርብ አስፈላጊውን የክትትልና ድጋፍ ሥራ በመስራት ከ1,742,707.60 ኩ/ል ፍላጎት አንፃር 85% እንዲቀርብ ግብይቱን በማመቻቸት ለማርካት የታቀደ ቢሆንም 585,481.1 ኩ/ል ቀርቦ 478,544.7 ኩ/ል ተሰራጭቷል የኸውም ከእቅዱ የቀረበው 33.60%፤ ከቀረበው የተሰራጨው 81.74% ማሳካት ተችለዋል፡፡

ለ2012/13 ምርት ዘመን ጥቅም ላይ እንድውል ከተፈቀደ 26.87 ቢሊየን ብር ውስጥ የቀረበ ብድር 21.5 ቢሊየን (80 በመቶ) ይሸፍናል፡፡ ለ2013/14 ምርት ዘመን ለግብርና ግብዓት ግዥ ብድር 37.5 ቢሊየን ብር ተጠይቆ 30 ቢሊየን ብር (80 በመቶ) እንዲሁም 650 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (69 በመቶ ) ብድር ተመቻችቷል ፡፡

የኬሚካል አቅርቦትና ስርጭት ጋር ተያይዞ ያሉትን ጉዳዮች በዚህ ምርት ዘመን ልዩ ትኩረት በማስጠት እንደሌሎች የግብርና ግብዓት ስርዓት ውስጥ በማስገባት ከሁሉም ክልሎች ለ2013/14 ም/ዘመን ጥቅም ላይ የሚውል በሚፈለገው ዓይነት፣ መጠንና ይዛት ተለይተው እንዲቅረብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት የተለያዩ ዓይነት እና ይዠት ያለቸው 3.61 ሚ ሊ/ር ታቅዶ 1,692,313 (47.1%) ፍላጎት ተለይቶ

ለማቅረብ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የጸረ-ፋንጋስ ተባይ ኬሚካሎች በአገር ውስጥ ማምረት የሚያስችል ስራ ተጠናክሮ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

በአሲዳማ የተጠቀ የአፈር ጤንነት ለማሻሻል ከሚያስችሉ ግብዓቶች መካካል የግብርና ኖራ ትልቅ ሚና እንደለው የዘፉ ተመራመሪዎች እና ባላሙያዎች ያረጋግጠሉ፡፡ በሃገራችንም ከ3.5 ሚልዮን ሄ/ር በላይ መሬት በአሲዳማ እንደተጠቀ ጥናቶች መለክታሉ፡፡ ይህን ችግር ማቅረፍ እንዲቻል በ2013/14 ምርት ከአምስት ክልሎች ጋር ሰፊ ውይይት በማካሄድ የግብርና ኖራ አቅርቦት እንደሌሎች የግብርና ግብዓቶች ተይዞ አስፈለጊውን በጀት ተመድቦለት እና ስርዓት ተበጅቶለት ወደ ስርዓት ለማስገበት የየክልሎቹ የፍላጎት በመሳበሰብ ለዘንድሮ የግዥ ስርዓቱን ከፌዴራል የመንግስት ንብራት ግዥ እና ማስወገድ ኤጀንሲ በማስፈቀድ ወደ ክልሎች በራሳቸው እንዲገዙ የማድረግ ስራዎች ተሳርተዋል፡፡ በዚህም መሰረት የቀረበ ሲሆን የስርጭት ተግባሩ በሁሉም ክልልች በተጠናከረ መልኩ እየተከናወነ ይገኛል ፡፡

| ክልል | ፍላጎት በ/ኩል | የቀረበ በኩ/ል | የተሳራጨ በኩ/ል | አፈፃፀም ከቀረበው | አፈፃፀም ከዕቅዱ |
|---|---|---|---|---|---|
| አማራ | 111,676.00 | 53,994.00 | 31,728.50 | 58.76 | 28.4 |
| ኦሮሚያ | 189,384.00 | 42,670.00 | 34,963.00 | 81.94 | 18.4 |
| ሲዳማ | 10,000.00 | 10,000.00 | - | | |
| ደቡብ | 18,000.00 | - | - | | |
| **ድምር** | **329,060.00** | **106,664.00** | **66,691.50** | **62.52** | **20.2** |

አፈፃፀሙ ያነሰበት ምክንያት በአዲስ ወደ አቅርቦትና ስርጭት ስርዓቱ ውስጥ የገባ ግብዓት በመሆኑ ነው ፡፡

በ2013/14 ምርት ዘመን ከክልሎቹና ከፌደራል አምራቾች የምርጥ ዘር አሰባሰብ ሁኔታን በተመለከተ በክልል ደረጃ ከኦሮሚያ፣ ከደቡብ እና አማራ ክልል እንዲሁም በፌደራል ደረጃ ከኮርቲቫ አግሪሳይንስ ፤ ከግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን እና ከፌደራል ግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት በተሰበሰበው መረጃ መሰረት የተለያዩ ድቃይ የሆኑ እና ያልሆኑ 1,910,142.93 ኩ/ል **የተመሰከረለት** ዘር በአዲስ እንደሚሰበሰብ የተገመተ/የታቀደ ቢሆንም 1,239,575.5 ኩ/ል (64.9%) ተሰብስቧል፡፡ **የተለያዩ መስራች ዘሮች** 125,075.59 ኩ/ል በአዲስ እንደሚሰበሰብ የተገመተ ቢሆንም 83,571.28 ኩ/ል (66.8 % ) ተሰብስቧል፤ **የተለያዩ ቅድመ-መስራች ዘሮች** 13,839.31 ኩ/ል በአዲስ እንደሚሰበሰብ የተገመተ ቢሆንም 7,923.05

ኩ/ል (57.3%) ተሰብስቧል፡፡ 178.5 ኩ/ል የተለያዩ አራቢ ዘሮችን በአዲስ እንደሚሰበሰብ የተገመተ ቢሆንም 84.2 ኩ/ል (47.2 % ) ተሰብስቧል ፡፡

በአምስቱ የግብርና ግብዓት ተጠቃሚ የሆኑ ክልሎች ከ2003/04 እስከ 2010/11 ምርት ዘመን ጥቅም ላይ የዋለ ብድር መጠን ብር105,291,058,200.81 ሲሆን የተመለሰ ብድር መጠን ብር101,339,333, 137.90 ቀሪ እዳ ብር 3,951,725,062.91 አፈፃፀሙም 96.25% ደርሷል፡፡

የ2012/13 ምርት ዘመን የግብዓት መግዣ ብድር ጥቅም ላይ የዋለ ብር 20,021,123,450.54 ሲሆን የተመለሰ ብድር መጠን ብር 13,021,123,450.65 ቀሪ እዳ ብር 7,043,304,133.89 አፈፃፀሙም 70.35 % ደረሷል፡፡

ለ2013/14 ምርት ዘመን ከግብዓት ተጠቃሚ ክልሎች የቀረበ ብድር ፍላጎት መጠን ብር 37.3 ቢሊዮን ብር እና 940.2 (ዘጠኝ መቶ አርባ) ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሲሆን በዚሁ መሰረት ለብሔራዊ ባንክ የብድር ፍላጎት ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም የተፈቀደ ብድር መጠን 30 (ሰላሳ) ቢሊዮን ብር እና 650 (ስድስት መቶ ሃምሳ) ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል ድልድል ተሰርቷል፡፡

በፓርላማ ቋሚ ኮሚቴ በተሰጠው ግብረ መልስ መሰረት ለብሔንድድ ማዳበሪያ ማምረት ግብዓትነት ወደ አገር ውስጥ ገብተው በክምችት ለብዙ ዓመታት የቆዩ ንጥረ ነገሮች እንዲሸጡ በገንዘብ ሚኒስቴር በተወሰነው መሰረት የሚሸጡበት ዝርዝር ሁኔታ ተዘጋጅቶ በክልሎች ውክልና ለተሠጠው የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ሽያጭ እንዲያከናውን ቀርቦለታል፡፡

### 3.3.2 የገበያ መሰረተ ልማት ማስፋፋት

የመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከል ግንባታ 10 እንዲጠናቀቅ ክትትልና ድጋፍ ማድረግና ወደ ስራ የማስገባት ስራ ለመስራት በዕቅድ ተይዞ 10 ተጠናቆ 8 ወደ ስራ ገብቷል፡፡ በተጨማሪም 8 የሁለተኛ ደረጃ የገበያ ማዕከል ግንባታ እንዲጠናቀቅ ክትትልና ድጋፍ ማድረግና ወደ ስራ የማስገባት ስራ ለመስራት 8 በዕቅድ ተይዞ ስምንቱንም ተጠናቋል፡፡ አምስት የወተት ማሰባሰቢያና መሸጫ ማዕከላት እና ሶስት የማር ማሰባሰቢያና መሸጫ ማዕከላት እንዲጠናቀቅ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ወደ ስራ ለማስገባት በተያዘው ዕቅድ መሰረት 14 የወተት ማሰባሰቢያና መሸጫ ማዕከላት እና 5 የማር ማሰባሰቢያና መሸጫ ማዕከላት ወደ ስራ ማስገባት ተችሏል፡፡

### 3.3.3 ግብርና ምርቶች ኤክስፖርት

#### 3.3.3.1 የሆርቲካልቸር ምርቶች የወጪ ንግድ

በ2013 በጀት አመት በአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት 425,337 ቶን ምርት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 309,857 ቶን (73 %) ምርትን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ተችሏል፡፡ ካላፈው በጀት አመት ክንውን አኳያ ሲታይ የ7 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡

አፈጻጸሙ በየምርቱ ተከፋፍሎ ሲታይ በድምሩ 101,579 ቶን የአበባ ምርትን ወደ ውጭ በመላክ የእቅዱን 76 በመቶ ለማሳካት ሲቻል ካለፈው በጀት አመት ጋር ሲነጻጸር የ10 በመቶ ቅናሽ አሳይቷል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ 173,115 ቶን የአትክልት ምርትን ወደ ውጭ በመላክ የእቅዱን 68 በመቶ ለማሳካት ሲቻል ካለፈው በጀት አመት ጋር ሲነጻጸር የ16.3 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡ በአንጻሩ 35,163 ቶን የፍራፍሬ ምርት ወደ ውጭ በመላክ የእቅዱን 97 በመቶ ለማሳካት ሲቻል ካለፈው በጀት አመት ጋር ሲነጻጸር የ29 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡

ከውጭ ምንዛሪ ገቢ አንጻር በ2013 በጀት አመት በአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ሆርቲካልቸር ልማት በድምሩ 658.2 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 531.5 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ተችሏል፡፡ ይህም ከተያዘው እቅድ አንጻር 81 በመቶ አፈጻጸም ያለው መሆኑን ሲያሳይ ካለፈው በጀት አመት አኳያ ሲታይ የ 11 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡

የውጭ ምንዛሬ ገቢ በየምርቱ ተከፋፍሎ ሲታይ በ2013 በጀት አመት በአበባ ኤክስፖርት በድምሩ 530 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 470.6 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ተችሏል፡፡ ይህም ከተያዘው እቅድ አንጻር 89 በመቶ አፈጻጸም ያለው መሆኑን ሲያሳይ ካለፈው በጀት አመት ክንውን አኳያ ሲታይ የ11.5 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡

በሌላ በኩል በአትክልት ኤክስፖርት 108.8 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 47.5 (44%) ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ተችሏል፡፡ ካለፈው በጀት አመት ክንውን አኳያ ሲታይ የ2.7 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በፍራፍሬ ኤክስፖርት 19.5 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 13.4 (69%) ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ተችሏል፡፡  ካለፈው በጀት አመት አኳያ ሲታይ የ+44 በመቶ ልዩነት አሳይቷል፡፡

## ለሆርቲካልቸር ኤክስፖርት መቀነስ ከሚጠቀሱ ምክንያቶች ውስጥ፦

በአውሮፓ ሀገሮች በሁለተኛ ዙር በተቀሰቀሰው የኮቪድ ወረርሽ ምክንያት እና ይህንንም ተከትሎ የገበያ መዳረሻ ሀገሮች ድንበር በከፊልና በሙሉ መዘጋቱ (ስፔን፣ ሆላንድ ወዘተ)፤ በተመሳሳይ ሁኔታ የአትክልት አምራች ኩባንያዎች የገበያ መዳረሻ በሆኑ በአውሮፓ ሀገራት የኮቪድ ተፅዕኖ በወሩም ተጠናክሮ በመቀጠሉና ገበያ ፍላጎት በመቀነሱ፣ ኩባንያዎች ከፍተኛ ምርት ያላቸው ቢሆንም ምርታቸውን በሀገር ዉስጥ የሸጡ መሆናቸው፤ ከመሬት ጋር በተያያዘ ችግራቸው ያልተፈታላቸው ኩባንያዎች የባንክ ብድር ለማግኘትና የንግድ ፈቃድን ለማደስ ያለመቻላቸው (ለአብነት ቤቲ ኦርናሜንታል ባለፉት ሁለት ወራት ወደ ኤክስፖርት መግባት ያለመቻሉና ምርቱን እየጣለ መሆኑ)፤ በጅጅጋ ኬላ በኩል ወደ ጎረቤት አገር የሚላክ ከፍተኛ የአትክልት ምርት በኬላ መዘጋት ምክንያት መቆሙ፣ ባለፈዉ ወር እንደተመለከተዉ 70 ሄ/ር የሚሆን ነባር የአበባ እርሻ ኩባንያዎች ያረጁ ዝርያዎችን ለመቀየር በመንቀል በአዲስ ዝርያዎች የመተካት ስራ ላይ በመሆናቸዉ አቅርቦቱ መቀነሱ፤ በቆቃ ልማት ክላስተር የፍራፍሬ አምራች ኩባንያ የሆነው ኢላንቶት እርሻ 40 ሄክታር ለሌላ ባለሀብት በመሸጡና ኩባንያውን የገዙ ባለሀብቶች በአዲስ ዕቅድ እየሰሩ በመሆናቸው ወደ ኤክስፖርት አለመግባታቸው፤ በቢሾፍቱ እና በቆቃ ልማት ክላስተር በተከሰተው ከፍተኛ የጎርፍ አደጋ በቁጥር ከ8 የሚበልጡ ኩባንያዎች ወደ ውጭ ለመለክ የደረሰ ምርት መጠን መቀነሱ እና ጎርፉ በፈጠረው እርጥበት ችግር የሰብል ተባይና በሽታ በመከሰቱ በምርታማነቱ ላይ ተጽኖ ማሳደሩ፤ የሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ልማት በሚካሄድባቸው ደጋና ወይና ደጋ አካባቢዎች የተከሰተው ቅዝቃዜ የተክሎችን እድገት መገደቡና በወቅቱ ወደ ውጭ ሊላክ በሚችለው ምርት መጠን ላይ ተጽዕኖ ማድረሱ፤ ከፍተኛ የአበባ ምርት ሲልክ የነበረዉ የሼር ኢትዮጵያ ኩባንያ በደረሰበት ጉዳት በየወሩ ለዉጪ ገበያ ሊያቀርብ የሚችለዉ የአበባ መጠን መቀነሱ፤

**ከላይ የተዘረዘሩት ችግሮች በሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ለመቀነስ፡-**

ከሚመለከታቸው የክልል መንግስታዊ ተቋማት ጋር ሰፊ ውይይትና የአካል ምክክር በማድረግ የጎርፍ ክስተቱ ሊያስከትል የሚችለውን ተጨማሪ አደጋ መቀነስ ተችሏል፤ እርሻዎች ወደ መደበኛ ስራቸው እንዲመለሱና የቅድመ አደጋ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ተጠናክሮ እንዲዘረጋ ተደርጓል፤ ጉዳት ከደረሰባቸው ኩባንያዎች፣ ከአካባቢ መስተዳድር አካላትና ከህብረተሰቡ ጋር በመወያየት የኢንቨስትመንት አካባቢዎች ወደ ተረጋጋ ሰላም እንዲመለሱ ተደርጓል፤ በጸጥታ መደፍረስ የተነሳ የወደመ ንብረት መልሶ እንዲገነባ በባለሙያ በማስጠናት የድጋፍና የክትትል ሥራ ተሰርቷል፤ በሀገራችን በተከሰተው የጸጥታ መደፍረስ የሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ልማት እንዳይስተጓጎል ከኢትዮ ቴሌኮምና ከዘርፍ ማህበሩ ጋር በመቀናጀት (የዝዋይ ልማት ክላስተርን) ጨምሮ በሌሎች ክላስተሮች የሚገኙ ኩባንያዎች IP Address እንዲሰባሰብ ተደርጎ ያልተቆራረጠ የኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፤ ባልተገባ ወርሃዊ የመጠጥ ውሃ ታሪፍ ትመና ብር 870,000 የውሃ መጠቀሚያ ክፍያ እንዲከፍል የተጠየቀና በዚህም የተነሳ ሥራዉን ያቀዘቀዘ (Slow Down) ሼር ኢትዮጵያ ሃ/የተ/የግ/ኩባንያ ባቀረበው አቤቱታ ላይ ተመስርቶ

መረጃው በባቱ አስተዳደር ውሃና ፍሳሽ ጽ/ቤት እንዲጣራ ተደርጎ ስህተቱ እንዲታረምና ወደ ብር 30,000 ዝቅ እንዲል ተድርጎ ኩባንያው በሙሉ አቅሙ ወደ ሥራ እንዲገባ ተደርጓል፤ በሌላ በኩል ከጸጥታ መደፍረስ ጋር በተገናኘ ምርታቸውን ከእርሻ ወደ ካርጎ ተርሚናል ለማጓጓዝ ችግር ያጋጠማቸው ኩባንያዎች ጉዳያቸውን ከሚመለከተው የክልል ጸጥታ መዋቅር ጋር በመነጋገር እንዲፈታ ተደርጓል፡፡

### 3.3.3.2 የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም የወጪ ንግድ

በበጀት ዓመቱ 313,062 ቶን ቡና በመላክ 1,173.5 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 248,311.65 ቶን (ከዕቅዱ 80%) በመላክ 907 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር (ከዕቅዱ 77.3%) ገቢ ተገኝቷል፡ ፡አፈጻጸሙ ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከተላከው ጋር ሲነጻጸር በመጠን (-8%) በገቢ ደግሞ (+6.18%) ቅናሽ ተመዝግቧል፡፡ ለአፈጻጸሙ መቀነስ በኮቪድ-19 ምክንያት አንዳንድ ገዢ ሃገሮች የገቡትን ኮንትራት በጊዜው አለመውሰዳቸው፣ የሀገር ውስጥ የቡና ዋጋ ከዓለም አቀፉ ዋጋ ጋር የማይናበብ መሆኑ እና የዓለም የቡና ዋጋ በሚጠበቀው ደረጃ መሻሻል አለማሳየቱ ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡

#### የሻይ የወጪ ንግድ

በበጀት ዓመቱ 2,191 ቶን ሻይ በመላክ 3.54 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 1,814.46 ቶን (ከዕቅዱ 83%) በመላክ 2.93 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር (ከዕቅዱ 82.8%) ገቢ ተገኝቷል፡፡ አፈጻጸሙ ካለፈው በጀት ዓመት በተመሳሳይ ወቅት ከተላከው ጋር ሲነጻጸር በመጠን (2.8%) እና በገቢ ደግሞ (10.6%) ጭማሪ ተመዝግቧል፡፡

#### የቅመማ ቅመም የወጪ ንግድ

በበጀት ዓመቱ 15,000 ቶን ቅመማ ቅመም በመላክ 18.8 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 12,880.25 ቶን (ከዕቅዱ 86%) በመላክ 15.7 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር (ከዕቅዱ 83.6%) ገቢ ተገኝቷል፡ ፡ አፈጻጸሙ ካለፈው በጀት ዓመት በተመሳሳይ ወቅት ከተላከው ጋር ሲነጻጸር በመጠን (-1.3%) ጭማሪ እና በገቢ ደግሞ (+13.13%) ቅናሽ ተመዝግቧል፡፡

በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ 329,252 ቶን የቡና፣ ሻይ እና ቅመማ ቅመም ምርቶችን በመላክ 1,195.84 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 263,006 ቶን (ከዕቅዱ 80%) በመላክ 926 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር (ከዕቅዱ 77.4%) ገቢ ተገኝቷል፡፡ አፈጻጸሙ ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከተላከው ጋር ሲነጻጸር በመጠን (-8%) እና በገቢ ደግሞ (+6.7%) ቅናሽ ተመዝግቧል፡፡

### 3.4 ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም

#### 3.4.1 የተፋሰስ ልማት ስራዎች

በሀገር-አቀፍ ደረጃ የተፋሰስና የአረንጓዴ አሻራ ድህረ ተከላ ሥራዎችን አስመልክቶ በ2012 በጀት ዓመት በክረምት ወራት ለተተከሉ ችግኞች የድህረ ተካለ ወቅት ከተተከሉት 5.9 ቢሊዮን ችግኞች ውስጥ ለ5.35 ቢሊዮን ችግኞች በ1,347,118.87 ሄ/ር መሬት ላይ 18,478,974 አርሶ አደሮችን በማሳትፍ የአረም፣ የኩትኳቶና ውሃ የማጠጣት ስራ ለማከናወን ተችሏል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ የተተከሉ ችግኞች አማካይ የጽድቀት መጠን 83.87 በመቶ መሆኑን ከግብርና ሚ/ር፣ ከደን፣ አካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን እና ከውሀ መስኖና ኢነርጂ ሚ/ር መ/ቤቶች የተውጣጡ ባለሙያዎች ከክልል ባለከሙያዎች ጋር በመሆን ካደረጉት የጽድቀት ምዘና ተገኝቷል፡፡

የ2013 በጀት **ዓመት የችግኝ ዝግጅት ሥራዎችን በተመለከተ፤** በአገራችን የሚገኙ የችግኝ ጣቢያዎች ብዛት፣ ችግኝ የማፍላት አቅማቸውን፣ መገኛ ቦታቸውን (Geo-reference)፣ የሚሸፍኑት ስፋት እና የባለቤት ዓይነት የመለየት ሥራ ተሠርቷል፡፡ ከዚህም አንፃር የችግኝ ጣቢያዎች ሊየታን በተመለከተ በመንግስት፣ በመያድ፣ በፕሮጀክት፣ በማህረሰብ እና በሌሎችም አካላት በአጠቃላይ 124,545 ችግኝ ጣቢያዎች እንዳሉ በተደረገው ክትትልና ድጋፍ ለመለየት ተችሏል፡፡

በተለያዩ ችግኝ ጣቢያዎች 7.46 ቢሊዮን ችግኞች የተዘጋጁ ሲሆኑ ከዚህም ውስጥ 3.708 ቢሊዮን የዛፍ፣ 0.0579 ቢ/ን የቀርከሀ፣ 2.105 ቢ/ን ዘርፈ-ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው ዕፅዋት፣ 0.486 ቢ/ን የፍራፍሬ፣ 1.1.1 ቢ/ን የእንስሳት መኖ እንዲሁም 0.0027 ቢ/ን የውበት ዛፍ ችግኞች ናቸው፡፡ ከተዘጋጁት 7.46 ቢሊዮን ችግኞች ውስጥ 6 ቢሊዮን ችግኞች በአገር ውስጥ የሚተከሉ ሲሆን 1 ቢሊዮን ችግኞች ደግሞ ለጎረቤት አገራት የሚሰጥና የሚተከል ይሆናል፡፡

የ2013 በጀት ዓመት የሶስተኛው ዙር አገራዊ አረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ መርሀ-ግብር የሚካሄድበት 1,927,264 ሄ/ር መሬት የተለየ ሲሆን የዓመቱ የአረንጓዴ አሻራ ተከላም አንደየክልሎች ዝናብ የማግኘት ፀጋ (ሥነ-ምህዳር ቀጠና) የሚካሄድ ታሳቢ ተደርጎ ታቅዷል፡፡ በዚሁ አግባብ እስካሁን በሀገር ውስጥ ለመትከል ከተዘጋጁ 6.43 ቢልዮን ችግኞች 5.199 ቢልየን ችግኝ ተተክሏል፡፡ በተጨማሪም የችግኝ ተከላን ከ6ኛው አገራዊ ምርጫ ጋር በማያያዝ ለመትከል

በመንግስት በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በየምርጫ ጣያዎቹ ከተመዘገበው መራጭ ውስጥ 25,727,081 መራጮችን በማሳተፍ 117,299,558 ችግኞች ለመትከላ ታቅዶ 87,450,168 የተለያዩ ችግኞችን በ16,024,866 መራጮች መትከል ተችሏል፡፡ ከዕቅድ በታች የሆነበትም ምክንያት በዕለቱ በ11 የኦሮሚያ ዞኖችና ምስራቅ አማራ ዞኖች የዝናብ እጥረት በማጋጠሙ ነው፡ ለ2013/14 ተከላ የዘር አቅርቦትንና ሥርጭትን በተመለከተ 5,200 ኩ/ል ዘር ለማሰራጨት ታቅዶ 11,762.98 ኩ/ል ዘር ማሰባሰበና ማሰራጨት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም +100 % ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ለችግኝ ዝግጅት የሚሆን የችግኝ ፕላስቲክ ከፌዴራል በተደረገዉ ድጋፍ መሰረት 2,235,464.80 ኪ.ግ የቀረበ ስሆን አፈጻጸሙ ከዕቅዱ የበለጠበት ምክንያት ለዘር ግዥና ማሰባሰብ ከፌደራል መንግስት ጀምሮ በፕሮጀክቶች ጭምር ለሥራው ትኩረት በመስጠቱና አስፈላጊው ድጋፍ በመደረጉ ነው፡፡

በ2013 ዓ/ም ለ1,500 የማህበረሰብ ተፋሰሶች የልማት ዕቅድ ለማዘጋጀት ታቅዶ ለ1,800 ዕቅድ የተዘጋጀላቸው ሲሆን አፈጻጸሙ 120% ነው፡፡ ከዚህም ውስጥ 300,000 ሄ/ር የተጎዱና የተራቆቱ አካባቢዎችን በመከለል ከንክኪ ነጻ ለማድረግ ታቅዶ 215,469.9 ሄ/ር (71.82%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በበጀት ዓመቱ 2.5 ሚሊዮን ሄ/ር መሬት በተለያዩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ቴክኖሎጂዎች ለመሸፈን ታቅዶ 2.76 ሚሊዮን ሄ/ር (110%) መሬት ላይ መስራት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በ1.5 ሚሊዮን ሄ/ር መሬት ላይ የተሰሩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ቴክኖሎጂዎችን ለማደስና ለመጠገን ታቅዶ 415,625 ሄ/ር ላይ መስራት የተቻለ ሲሆን ይምም ከዕቀዱ 27.7% ብቻ ነው፡፡

መልሶ በማልማት ያገገመ መሬት ላይ 83.5 ሺህ ወጣቶችና ሴቶች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቀዶ 53.4 ሺህ (63.9%) ለማከናወን ተችሏል፡፡

### 3.4.2 የአፈር ለምነት ማሻሻል ሥራዎች

የአፈር ለምነትንና ጤንነትን ከማሻሻል አኳያ ኮትቻ አፈርን በዘመናዊ አሠራር ለማጠንፈፍ 600,000 ሄ/ር ለማልማልት ታቅዶ በቢ.ቢ.ኤም 316,452 ሄ/ር እና በባህላዊ ዘዴ 308,070 ሄ/ር በድምሩ 624,522 ሄ/ር /104%/ ማልማት ተችሏል፡፡ በቀጣይም ይህንኑ ስራ አጠናክሮ ለመስራት የክረምቱ ዝናብ የዘገየ በመሆኑ ስራው በቀጣይ በስፋት የሚሰራ ይሆናል፡፡

110 000 ሄ/ር አሲዳማ መሬትን በኖራ ለማከም ታቅዶ 17,617 ሄ/ር 4% መሬት ለማከም ተችሏል፡፡ ይህም ከኖረ አቅርቦት ውስንነት የተነሳ አፈጻጸሙ ዝቅ ሊል ችላል፡፡ የግል ኖራ

አምራች ድርጅቶችን በማሳተፍ የኖራ አቅርቦት ስርዓት ዝርጋታ ስራ በ4ቱም ክልሎች ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል።

አሲዳማ አፈር ልማትን ከሌሎች የግብርና ግብአትና ቴክኖኮጂዎች ጋር በኤክስቴንሽን ፓኬጅ ጋር አቀናጅቶ ለመስራት እንዲቻል የተቀናጀ የአሲዳማ አፈር ልማት ረቂቅ የኤክስቴንሽን ፓኬጅ ሰነድ ዝግጅት የተጠናቀቁ ሲሆን በባለድርሻ አካላት አስተያየት ተሰጥቶበት አስተያየቱ በቴክኒክ ቡድን ተካቶ ለህትመት ዝግጁ ተደርጓል።

የጨዋማ አፈር ችግርን ለመቅረፍ በተመረጡ ክልሎች (አፋር፣ አማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ) ክልሎች በ12 ወረዳዎች (ዱብቲ፣ አሚባራ፣ ራያ ቆቦ፣ ቀውት፣ አዳሚ ቱሉ ጂዶ ኮምቦልቻ፤ አፋምቦ፤ ዳሰነች፤ ሃመር፤ ድሬ፤ አሬሮ እና ቦራ) ከፕሮጀክት በጀት በማፈላለግ ጨዋማነትን የሚቋቋሙ 1,015 ኪ/ግ ዘር የመኖና የሰብል ዝርያዎች ለወረዳዎች በማሰራጨት በገበሬ ማሳ እና በአርሶ /አርብቶ አደር ማሳ ላይ ለመዝራት በዝግጅት ላይ ይገኛል ተከፋፍሏል።

በተጨማሪም በጨዋማ አፈር ልማት ዙሪያ ለአመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል።

በ2013/14 ዓ.ም የምርት ዘመን በጥራጥሬ ሰብሎች 120,000 ሄ/ር መሬት በህየው ማዳበሪያ ለማልማት ታቅዶ እስካሁን ድረስ 22,423.5 ሄ/ር መሬት የለማ ሲሆን ለዚህም 132,869 ከረጢት ተመርቶ 89,694 ሳቼት ህየው ማዳበሪያ ጥቅም ላይ ውሏል። የህየው ማዳበሪያ የሥርጭት ዕቅድ ክንውን ሪፖርት እየተጠናከረ ያለው በበጀት ዓመት ሳይሆን በምርት ዘመን ስለሆነ ሪፖርቱ እስከ ጥር 30/2014 ዓ/ም የሚቀጥል ነው።

የአፈር ንጥረ ነገር ይዘትን በማሻሻል የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር 70 ሚ/ሜ$^3$ ኮምፖስት ለመስራት ታቅዶ 71 ሚ/ ሜ$^3$ (102%) ተዘጋጂቷል። በልማት አጋር ድርጅቶች ድጋፍ ለአርሶና አርብቶ አደሮች የተሰሩ 21,128 የባዮጋዝ ባዮስላሪ ቴክኖሎጂዎችን የጋራ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ከባዮጋዝ ፕላንቱ የሚገኘውን የስላሪ ምርት ለአፈር ጤንነትና ለምነት ለማዋል እንዲቻል 18,600 የባዮ ጋዝ ፕላንቶችን ላይ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል። ከባዮጋዝ ፕላንት በተረፈ ምርት መልክ የተገኘውን 120,000 ኩ/ል የተዘጋጀ የባዮ ስላሪ ኮምፖስት ለአፈር ጤንነትና ለምነት ተግባር በማዋል 7,500 አርሶደሮችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል። በተጨማሪም የስላሪ ምርቱን በሰርቶ ማሳያ ደረጃ በ2013/14 የምርት ዘመን የሰብል፣ የጥራጥሬና የአትክልት ዝርያዎችን አሽቶ በመዝራት በምርትና ምርታማነት እንደዚሁም በአፈር

ጤንነትና ለምነት ደረጃ ሊያስገኝ የሚችለውን ዘርፈ ብዙ ጥቅም የማስተዋወቅና የማስፋት ስራ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተሰርቷል፡፡

የባዮጋዝ ቴክኖሎጂ ግንባታና ዘርን በባዮስላሪ አሽቶ መዝራት ላይ እየተከናወኑ የሚገኙትን ተግባራትና እያስገኙ ያሉትን ጠቀሜታዎች ከሶማሌ፣ አፋር፣ ጋምቤላና ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ከባዮጋዝ ማስተባበሪያ ፕሮግራም፣ ከውሃ መስኖና ኢነርጂ ቢሮና ከፌደራል ግብርና ለተውጣጡ 22 ከፍተኛ ባለሙያዎች በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን ወረኢሉ ወረዳ በሚገኙ ቀበሌዎች በመገኘት የልምድ ልውውጥ ስራ ተከናውኗል፡፡

በ2012/13 ዓ.ም 10,000 የእቀባ እርሻ ሰርቶ ማሳያዎችን ለመስራት ታቅዶ 28,903 ሰርቶ ማሳያዎች በኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ እና ቤንሻንጉል ጉሙዝ በተመረጡ ወረዳና ቀበሌዎች ተከናውኗል፡፡ ቴክኖሎጂውን ይበልጥ ለማስፋት እንዲቻል ከአጋር የልማት ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት በተለያዩ ባለድርሻ አካላት እየተከናወኑ ያሉትን የዕቀባ እርሻ ተግባራት በሪፖርትና በመስክ በመታገዝ በደቡብ ክልል ወላይታ ሶዶ ዞን ባሉ 2 ወረዳና ቀበሌዎች 35 (6 ሴት) ባለሙያዎች በተገኙበት የመስክ ጉብኝት ስራ ተካሂዷል፡፡

በ2013 ዓ.ም በ20,000 ነባር እና አዳዲስ አ/አደሮች ላይ እየተካሄደ የሚገኘውን የቨርሚ ኮምፖስት ቨርሚካልቸር ቴክኖሎጂ ክትትል ለማድረግ እና ለማስፋት ታቅዶ 26,000 አ/አደሮች ላይ የማስፋትና የክትትል ስራዎችን በማካሄድ 65,000 ኩንታል ቨርሚ ኮምፖስት ማዘጋጀትና መጠቀም ተችሏል፡፡

የቨርሚ ኮምፖስትና ቨርሚ ካልቸር ቴክኖሎጂን በኦሮሚያ፣ ደቡብና ሲዳማ ክልሎች ስራ ፈላጊ ሴትና ወጣት አ/አደሮችን የያዙ 15 ቡድኖችን ለማደራጀት ታቅዶ 17 ቡድኖችን ማደራጀት ተችሏል፡፡ በተጨማሪ ቴክኖሎጂውን በስፋት በማካሄድ እና ስራ ፈላጊ ወጣትና ሴት አ/አደሮችን ተጠቃሚ ለማድረግ የቢዝነስ ሞዴል በማዘጋጀት ለክልሎች የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ተሰርቷል፡፡

የሰው ሰራሽ ማዳበሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ ምርት ዘመኑ ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች ማለትም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ሀረሪ ክልሎች እና ድሬዳዋ ከተማ መስተዳደር የማዕድን ማደበሪያ እና በኦሮሚያ ክልል የተቀናጀ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ሰርቶ ማሳያ ማለትም የማዕድን እና የተፈጥሮ ማዳበሪያ በተቀናጀ መልኩ በ450 አርሶ አደር ማሳ ላይ ለመስራት ታቅዶ 450 (100%) ሰርቶ ማሳያ ተከናውኗል፡፡

የማዳበሪያ ጥራት ቁጥጥር መዋቅራዊ አደረጃጀት ሀገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ የሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ በማጣጣም አንድ የማዳበሪያ ጥራት ቁጥጥር አደረጃጀት አስፈላጊነትን የሚገልፅ ጥናታዊ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለበላይ አካል ቀርቦ ለተግባራዊነቱ የሚሰጠውን የውሳኔ አቅጣጫ በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን፡፡

በተጨማሪም ይህን ስራ በአማካሪ ድርጅት የዳሰሳ ጥናት በስፋትና በጥልቀት እንዲሰራ በማድረግ የአደረጃጀት ሰነድ (Consultancy Services to Assess the Quality of Fertilizers Distributed in the Country and Capacity of Soil Laboratories to Test Fertilizers) እንዲዘጋጅ የአማካሪ ድርጅት ቅጥር በማከናወን እና የውል ስምምነት በመፈራረም አማካሪ ድርጅቱ ወደ ስራ ገብቶ እየሰራ ይገኛል፡፡

የማዳበሪያ ጥራት ቁጥጥር ስራ ዕውን ለማድረግ የማዳበሪያ ጥራት ፍተሻ (Fertilizer Quality Analysis) ለሚሰሩ አምስት የተመረጡ የአፈር ምርመራ ላብራቶሪዎች የተገዙ የላቦራቶሪ መሳሪያዎችን (ሞባይል ቴስቲንግ ቱልስ (Soil Fertilizer Instrument and Soil Moisture Tester) ለባህርዳር፣ ደብረማርቆስ፣ ዝዋይ፣ ነቀምቴ፣ ወላይታ ሶዶ እና ሀዋሳ አፈር ምርመራ ላብራቶሪዎች ተሰራጭቷል፡፡

ከተለያዩ መስሪያ ቤቶች የተውጣጡ ሁለት የባለሙያ ቡድን ጥራት ያለውን ማዳበሪያ ከመጠቀም አኳያ የማዳበሪያ አጠቃቀም በመስኖ ልማት፣ አበባ ልማት እና አትክልት እና ፍራፍሬ ልማት፣ ከማዳበሪያ ንግድ አኳያ በጅምላ እና ችርቻሮ ንግድ ላይ የሚገኘው የማዳበሪያ ዓይነት ልየታ እና በተለያዩ ጊዜያት በህብረት ስራ ማህበራት መጋዘን ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ ማዳበሪያዎችን በምዕ/ሸዋ፣ ምስ/ሸዋ፣ አርሲ እና ሰሜን ሸዋ ዞኖች በሚገኙ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች በመዘዋወር የድጋፍና ክትትል ስራ በመስራት ህገ-ወጥ የማዳበሪያ አይነቶች በአ/አደሩ ዘንድ በጥቅም ላይ የዋሉ መሆኑንና የቀጣይ ጠቋሚ አቅጣጫዎችን የመስክ ቡድኑ አስቀምጧል፡፡

ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ጋራ በመተባበር የስድስት የማዳበሪያ ዓይነቶች (NPS, NPSB, NPSZn, NPSZnB, KCl እና UREA) ደረጃ የመከለስ ስራ እና በ2013/14 ምርት ዘመን ለሚገዙ የማዳበሪያ ዓይነቶች (NPS, NPSB, NPSZn, NPSZnB እና UREA) ስፔሲፊኬሽን ተዘጋጅቶ ግዢው እንዲፈጸም ለግብዓት ዳይሬክቶሬት ተልኳል፡፡

በ2014/15 ምርት ዘመን ለሚገዙ የአፈር ማዳበሪያ ዓይነቶች (NPS, NPSB, NPSZn, NPSZnB እና UREA) ስፔሲፊኬሽን በተጠየቀው መሰረት ተከልሶ እንዲቀርብ እና ግዥው በጊዜ እንዲፈጸም እየተሰራበት ይገኛል፡፡

የማዳበሪያ ፍቱንነት ሙከራ ፕሮቶኮል (Fertilizer Efficacy Testing Manual-protocol) እና የማዳበሪያ ቴክኒክ እና መማክርት ኮሚቴ የግንኙነት መድረክ ለመፍጠር የሚያስችል የመነሻ መመሪያ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡ በተጨማሪም ኮሚቴውን ወደ ስራ ለማስገባት የሚያስችል የበጀት ምንጭ ለመፈለግ አንድ የበጀት ፕሮፖዛል (Concept Note) ተዘጋጅቶ ለአጋር አካላት ተሰጥቷል፡፡

የማዳበሪያ ማምረት፣ አያያዝ፣ ንግድና ስርጭት ረቂቅ አዋጅ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ለህግ ጉዳዮች ቀርቦ ለህዝብ ተወከዮች እንዲቀርብና እንዲጸድ ተልኮ እየተጠባበቅን እንገኛለን፡፡

የአፈር፣ የውሃና የዕፅዋት ናሙና ምርመራ አገልግሎት አቅርቦትን በማሳደግ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ሥራን ከመደገፍ አንፃር ዘመናዊ፣ አስተማማኝና ቀልጣፋ የሆነ የፊዚካል እና ኬሚካል (Wet Chemistry) ምርመራ በአፈር፣ በማዳበሪያ በውሃና በዕፅዋት ናሙናዎች ላይ ለማካሄድ ነው፡፡

**40,000** ፓራሜትር ታቅዶ 37,053 ፓራሜትር የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ 93% ነው፡፡ በአዲስ መልክ በሚደራጅ የስፔክትራል (Infrared Scanning) መሣሪያ ላይ የአፈር ናሙናዎችን ምርመራ ለማካሄድ 1,600 ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት ሙሉ በሙሉ ለማከናወን ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ባለድርሻ አካላት ወደ ዉጭ ሀገር ልክው ለማስመርመር ፈልገው የሚያመጧቸውን የአፈር ናሙናዎች ፍቃድ በመስጠት እንዲላክ ለማስቻል 1,000 ኪ.ግ ታቅዶ 1,015 ኪ.ግ አፈር እንድላክ የተደረገ ሲሆን አፈፃፀሙ 100% ነው፡፡ በተጨማሪም ባለድርሻ አካላት ወደ ዉጭ ሀገር ልከው ለማስመርመር ፈልገው የሚያመጧቸውን የውሃ ናሙናዎች ፍቃድ በመስጠት እንዲላክ ለማስቻል 60 ሊትር ታቅዶ 116 ሊትር ውሃ ናሙናዎች እንድላክ ተደርጓል፡፡

### 3.4.3 የአፈር ሀብት መረጃና ካርታ ዝግጅት

በበጀት ዓመቱ በ48 ወረዳዎች የአፈር ሀብት ዓይነትና ባህርይ በመስክ በመለየት ካርታ ለማዘጋጀት የታቀደ ሲሆን በፌደራልና ክልል ባሉ የተለያዩ ተቋማት በተለያየ ጊዜ የተሰበሰቡ 8000 ውርስ (Legacy) የአፈር ዓይነት መረጃዎችን በማጥራትና በመተንተን የጂ-ኦስፓሻል ቴክኖሎጂንና ሳይንሳዊ ሞዴል በመጠቀም በ1 ኪ.ሜ ሪዞሉሽን በአገር አቀፍ ደረጃ የአፈር ዓይነት ካርታ ተዘጋጅቷል (አፈጻጸም 93.7%)። ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከልማት ድርጅት ከምርምርና ከተለያዩ ተቋማት ከተውጣጡ ከፍተኛ የአፈር ሳይንስ ባለሙያዎችንና ምሁራንን (Pedologists) በማሳተፍ የመረጃ ማጥራትና የማረጋገጥ (Validation Workshop) ሥራ ተሰርቷል።

የተለያዩ ባዮፊዚካል መረጃዎችንና በማቀናጀትና በመተንተን ለአምስት ዞኖች (አርሲ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ ስልጤ፣ ምስራቅ ሸዋ እና ሐላባ) የተመረጡ የሰብል ዝርያዎችን (ስኳር ድንች፣ በቆሎ እና ቦለቄ) የአካባቢ ተስማሚነት ምክረ-ሐሳብ ካርታ (Innovation Recommendation Map) ለማዘጋጀት ታቅዶ ለሶስቱ ዞኖች (አርሲ፣ ምስራቅ ሐረርጌ እና ስልጤ) የተጠናቀቀ ሲሆን የሁለቱ ደግሞ እየተሰራ ይገኛል (አፈጻጸሙም 76% ነው) ።

የስርዓተ-ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚሰሩ ሥራዎችን ለማገዝ የአፈር ንጥረ ነገር (Iron and Zinc) ይዘት የሚያሳይ ካርታ የኢትዮሲስ መረጃን በመጠቀም በአገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅቷል።

የአፈር እና ተያያዥ መረጃዎችን በየፈርጁ በማደራጀት ለተጠቃሚው በሚፈለገው አግባብ ተደራሽ ለማድረግ በዓለም አቀፍ አማካሪ ድርጅት የአፈር መረጃ ቋትና ጂኦፖርታል ለማበልጸግ በታቀደው መሰረት እስከዚህ ወር ስራው 98% ተጠናቋል፤ በየስራ መስኩ ያሉ ተጠቃሚ ባለሙያዎች (የአፈር ቅየሳ፣ ምርመራ፣ ካርታ ዝግጅት፣ አይ.ቲ) የሚመለከታቸውን ክፍሎች (Components) በመገምገም አስተያየታቸውና ሐሳባቸው እንዲካተት ተደርጓል።

በጂ.አይ. ዜድ የገንዘብ ድጋፍ የአፈር ናሙና ለመሰብሰብ አስራ አምስት ታብሌት፣ ግዙፍ የአፈርና ተያያዥ መረጃዎችን ለመተንተንና ካርታ ለማዘጋጀት ከፍተኛ አቅም ያላቸው ስምንት ዎርክስቴሽን ላፕቶፕ እንዲሁም ለመረጃ ማከማቻ አንድ ሰርቨር ለዳይሬክቶሬታችን የተገዛ ሲሆን በመሬት አያያዝ ፕሮግራፍ ድጋፍ ደግሞ አንድ ዊንዶው ሰርቨር ሶፍትዌር ተገዝቶ በአገልግሎት ላይ ውሏል።

የአፈርና አግሮኖሚ መረጃ ልውውጥ ፖሊሲ ሠነድ ዝግጅትን አስመልክቶ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ የነበረውን የአፈርና አግሮኖሚ መረጃ ልውውጥ ፖሊሲ እና የአተገባበር ማኑዋል ወደ አማርኛ በመተርጎም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ አመራር እንዲፀድቅ በሃርድ ናሶፍት ኮፒ ለማስፀደቅ የቀረበ ሲሆን ቢሆንም እስካሁን ድረስ በሚ/ር መሥሪያ ቤቱ በበላይ አመራር ደረጃ ባለመፅደቁ አፈፃፀሙን 5% ብቻ ነው፡፡

የአፈር መረጃ ስርዓት ግንባታ ላይ ለክልሎችና ፌዴራል ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በጂኦስፓሻል ቴክኖሎጂ እና በጂኦስፓሻል መረጃ ቋት አጠቃቀም እንዲሁም የአፈር ዓይነት ካርታ ዝግጅት (Digital Soil Mapping) እና የአፈር ዓይነት ልየታን በሚያስችሉ ሶፍትዌሮችና ሞዴሎች ዙሪያ በበይነ-መረብ ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡

### 3.4.4 አነስተኛ መስኖ ልማት

የአነስተኛ ባለይዞታዎች የተለያዩ ውሀ አማራጮችን በመጠቀም የመስኖ ሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የመስኖ ውሀ አቅርቦት ላይ ሰፊ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ የመስኖ ውሀ አቅርቦትን ለማሳደግ በ2012 የተደረሰበትን 790 ሺህ ሄ/ር መነሻ በማድረግ በ2013 ተጨማሪ 26,200 ሄ/ር የመስኖ መሬት ዝግጁ በማድረግ አጠቃላይ በመስኖ የሚለማ መሬትን 816,200 ሄ/ር ለማድረስ ግብ የተጣለ ሲሆን አዲስ የመስኖ መሬት 56,540 ሄ/ር (215%) መሬት ዝግጁ በማድረግ አጠቃላይ በመስኖ የሚለማ መሬት 872,000 ሄ/ር ለማድረስ ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ ከፍ ያለው የውሃ መሳቢያ ፓምፖች በስፋት በግዢ ለአ/አደር ስለተሰራጩ ነው፡፡ በአዲስ ወደ መስኖ ልማት የሚገቡ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/ከፊል አርብቶ አደሮች ብዛት 183,000 ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 129,000 አርሶ/አርብቶ አደሮችን /70%/ ተጠቃሚ የተደረገ ሲሆን አፈፃፀሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት በግለሰብ የሚጠቀሙት የመሬት መጠን ከታቀደው ከፍ ማለትና በቤተሰብ ደረጃ የሚዘጋጁ የውሀ አማራጮች አፈፃፀም ማነሱ ነው፡፡

የመስኖ መሰረተ ልማት ከማስፋፋት አኳያም በማህበረሰብ 201፣ በቤተሰብ 103,535 ለመገንባት ታቅዶ በማህበረሰብ 134 /67%/ በቤተሰብ የሚተዳደሩ 37,768 /48%/ የመስኖ አውታሮችን መገንባት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ህጋዊ ሰውነት ያገኙ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራትን ብዛት 121 ለማድረስ ታቅዶ 62 የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ 30.% ነው፡፡

የባለ አነስተኛ ይዞታ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ተግባራትን በተመለከተ የአነስተኛ መስኖ ልማቱን ለማፋጠን በበጀት ዓመቱ ለመስኖ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚውል በመንግስት በኩል የልማት አጋሮችን በማሳተፍ ተጨማሪ በጀት እንዲመደብ በማድረግ ለፕሮጀክቱ የተመደበው የበጀት መጠን 501.8 ሚልዮን ሲሆን 308.74 (61.52%) ሚልዮን ስራ ላይ ውሏል፡፡

የጥናት እና ዲዛይን ሰነድ ዝግጅት፤ግምገማ፤ የድሬይኔጅ እና ጨዋማነት ጥናት ከማካሄድ አንፃር በክልል ደረጃ 32 የአነስተኛ መስኖ ልማት ጥናቶች ለመስራት ታቅዶ 24 የጥናትና ዲዛይን ሀረሪ እና ጋምቤላ በአማካሪ ድርጅት የጥናትና ዲዛይን ስራ ዉል ተይዞላቸው በመሰራት ላይ ያሉ ሲሆኑ ሁሉም የቅድሚያ ረቂቅ ጥናት (Inception Report) ክፍያ ተከናውኗል፡፡ የመጀመሪያው ድራፍት የጥናትና ዲዛይን ሪፖርታቸው በመጠቃለል ላይ የሚገኝ ሲሆን ለ8ቱ ፕሮጀክቶች አሁን ሰነዶች የማጠቃለል ሥራ ተሰርታል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በፌደራል ደረጃ በሶማሊ፣ድሬዳዋ፣ ወቅት የመጨረሻ ረቂቅ የጥናትና ዲዛይን ሰነድ ተዘጋጅቶ ግብረ-መልስም ተሰጥቷል፡፡ አጠቃላይ 8 ሳይቶች ጥናት እና ዲዛይን ሲጠናቀቅ ከ500 እስከ 1000 ሄ/ር መሬት መልማት የሚችሉ የጥናት ሰነዶች ይኖሩናል፡፡

በተጨማሪም ከትግራይ ክልል በስተቀር በኦሮሚያ፣ አማራ፣ በደቡብ፣ በሶማሌ እና አፋር ክልሎች በተመረጡ ቦታዎች የድሬይኔጅ እና ጨዋማነት ጥናት ለማካሄድ ቢ.ጋር በማዘጋጀት ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር መማክርት ሴክሪተሪያት ቢያንስ በ100 የመስኖ ተቋማት ጥናት እንዲያካሂዱ ውል ተይዞ ስራ የጀመሩ ሲሆን የመጀመሪያ ረቂቅ ጥናት ሪፖርት ቀርቦ ከተገመገመ በኋላ ክፍያ ተፈፅሟል፡፡ በተመረጡት ክልሎች እና ተቋማት ተመራማሪዎች መካከል በፕሮጄክቱ አተገባበር ላይ አውደ ጥናት በማካሄድ እና የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም በ95 የአነስተኛ መስኖ አውታሮች ላይ ጥናቱ እየተካሄደ ይገኛል፡፡

በበጀት ዓመቱ አዲስ የሚገነቡት የ1 መሥኖ ፕሮጀክት በጨረታና በውል ሂደት ላይ የሚገኝ፤ 29 ዉል የተገባ፣ 20 ፕሮጀክቶች ግንባታቸው የተጀመረ ሲሆን ነባር የመስኖ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ግንባታቸው በ2012 በጀት ዓመት ተጀምሮ በተለያዩ ምክንያቶች ማጠቃለል ባለመቻላቸው ወደ 2013 በጀት ዓመት ተሸጋግረው እየተገነቡ ካሉት 52 የመስኖ አውታሮች 13 የተጠናቀቁ ሲሆን ቀሪዎቹ በተለያየ የግንባታ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡

ወጪ ቆጣቢ የሆኑ የአነስተኛ መስኖ ልማት ቴክኖሎጅዎችን በመለየት ጥቅም ላይ ከማዋል አንፃር 150 የሶላር ፓምፕ ግዥ ለማከናወን ስፔስፊኬሽን ተዘጋጅቶ በግዥ ሂደት ላይ የሚገኝ ሲሆን አንድ የውሀ ጉድጓድ የቁፋሮ ማሽን/Well Drilling Machine/ ግዥም ውል ተገብቶ አቅርቦቱ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የተለያየ መጠን እና ዓይነት ያላቸው በ2012 በጀት

ዓመት ግዥያቸው የተከናወኑ በቁጥር 400 የሆኑ 3,700.23 ሄ/ር የማልማት ዓቅም ያላቸው ፓምፖችን በፀጥታ ምክንያት ከትግራይ ክልል በስተቀር ለሁሉም ክልሎች ተሠራጭቷል፡፡ ለመስኖና ድሬኔጅ ቴክኖሎጂ እና የአገልግሎት አቅርቦት ሰንሰለት እንዲኖር ከማድረግ አንፃር ለ50 የተክኖሎጂ አቅራቢዎች ወይም አገልግሎት ሰጪ ማህበራት (ለ200 አባላት) በስልጠና በተለያዩ ሙያዊ ድጋፎች ለማጠናከርና ለማደራጀት በታቀደው መሰረት በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡

### 3.4.5 የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም

የሁለተኛ ደረጃ ቅየሳ፣ ምዝገባና የይዞታ ማረጋገጫ ሰርቴፊኬት አሰጣጥን በተመለከተ ለ2.6 ሚሊዮን ማሳዎች የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ918,162 ማሳዎች ላይ ተከናወነ ሲሆን አፈፃጸሙም 35.32% ብቻ ሲሆን አፈፃፀሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት በመጀመሪያው ሩብ ዓመት በኮቪድ 19 እንቅስቃሴ በመገደቡ የስራው ባህርይ ደግሞ የሰዎች መሰባሰብን እና ዝውውርን የሚፈጥር በመሆኑ የመሬት ቅየሳና ልኬት ባለሙያዎችን ለማሰልጠን ባለመቻሉ ነው፡፡ ከባለይዞታዎች አኳያም ሲታይ ለ0.74 ሚሊዮን (0.52 ሚሊዮን አባወራ እና 0.22 ሚሊዮን እማወራ) ባለይዞታዎች የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋጫ ሰርተፍኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ0.26 ሚሊዮን (0.184 ሚሊዮን አባወራ እና 0.0787 ሚሊዮን እማወራ) ለሚሆኑ ባለይዞታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የተሰጣቸው ሲሆን አፈፃፀሙም 35.45% ነው፡፡ ለ78 ወረዳዎች የብሄራዊ የገጠር መሬት አስተዳደር የመረጃ ስርዓት ለመዘርጋት ታቅዶ ለ114 ወረዳዎች የተዘረጋ ሲሆን አፈፃፀሙም 146% ሲሆን የዚህ አፈፃፀሙ ከዕቅድ በላይ የሆነበት ምክንያት ኮቪድ-19 እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመውሰድ በጥቂት ባለሙያዎች በቤት ውስጥ በመስራት የሥርዓት ዝርጋታ ሥራው ሙሉ በሙሉ ለማከናወን ተችሏል፡፡ የመረጃ ስርዓት ዝርጋትን ተከትሎ በፌደራል ደረጃ የመረጃ መሸጋገሪያ ስርዓቱን (Data Migration Support) ለማፋጠንና የመረጃ ሽግግሩን ከ90% በላይ ለማምጣት የሚያግዙ ሥራዎች በአራቱም ክልሎች (አማራ፣ትግራይ፣ኦሮሚያ እና ደቡብ) ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪም በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በISLA አጠቃቀም ምክንያት የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት የመረጃ ማሸጋገሪያ ስርዓት (Migration Tool) በተጨማሪነት ለክልሉ በልጽጎ ለትግበራ የሚረዳ አጭር ስልጠና ለባለሙያዎች ተሰጥቷል፡፡ የብሄራዊ የገጠር መሬት አስተዳደር የመረጃ ስርዓትን በ114 ወረዳዎች የመጫን ስራ ላይ ድጋፍና ክትትል ከማድረግ በተጨማሪ የመሬት ግብይት ተግባራትን ወቅታዊ የማድረግ ሥራ ለመስራት እንዲያስችላቸው ባለሙያ የመመደብና ግብይት አገልግሎት ሥራ እንዲያከናወኑ ድጋፍና ክትትል በክልሎች ተደርጓል፡፡ በተደረገው ክትትልና

ድጋፍ መሠረት የሁለተኛ ደረጃ ሰርተፊኬትን በመጠቀም በወረዳ ደረጃ የተመዘገቡና የተከናወኑ የመሬት ግብይት (Transaction) ብዛት 63,139 ለማድረስ ተችሏል፡፡

በቀበሌ ደረጃ 850 የአሳታፊ መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ለማዘጋጀት ታቅዶ 575 ሰነዶች የተዘጋጀ ሲሆን አፈፃፀሙም 67.65% ነው፡፡ በተጨማሪም ለ650 ቀበሌ አሳታፊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ትግበራ ለማስጀመር ታቅዶ 345 (53%) ተከናውኗል፡፡

የገጠር መሬት አስተዳደር የመረጃ ስርዓቱን በጥሩ ሁኔታ በመዘርጋት መተግበር እንዲቻል በወረዳ ውስጥ የሚሠሩ ባለሙያዎችን በተለያዩ የሥልጠና ርዕሶች አቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን ለ2,000 ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ1,630 (1,249 ወንድ እና 381 ሴት) ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 81.5% ነው፡፡

### 3.4.6 የምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ሥራዎች

በያዝነው በጀት ዓመት በምግብ ዋስትና የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ዕቅድ ሁለት ምዕራፎችን የያዘ ሲሆን በመጀመሪያው ምዕራፍ ከሀምሌ እስከ ታህሳስ ድረስ ያለው የአራተኛ ምዕራፍ የልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም ስራዎችን ማጠናቀቅና ማጠቃለል ላይ ያተኮረ ሲሆን በሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ ከጥር እስከ ሰኔ ባለው ጊዜ የሚያተኩረው የአምስተኛ ምዕራፍ የገጠር ልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም (RPSNP-5) ትግበራ መሰረት የሚጣልበት ተግባራት ላይ ያተኮረ ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የመረጃ ሥርዓትን በማዘመን ወቅታዊ እና ተአማኒነት ያለው መረጃ ከማጠናከር አንፃር የልማታዊ ሴፍቲኔት ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም (MIS) በተዘጋጀው የፍላጎት ጥናት እና በቀረበው የለውጥ ጥያቄ (CR) መሰረት የሁሉም ሞጁሎች (Module) የማበልፀግ ስራ ተጠናቋል፡፡ በለማው የመረጃ ሥርዓት ላይ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እና የልማት አጋሮች በሰጡት ግብዓት ላይ በመመስረት ተጨማሪ ዝርዝር መግለጫዎች ከመዘጋጀታቸውም በተጨማሪ መሬት ላይ ካለው የአሠራር ሂደት ጋር የማጣጣም ሥራ ተከናውኗል፡፡ ይህንንም ተከትሎ የሙከራ ፍተሻ (User Acceptance Testing) በፌዴራልና በክልሎች በሚገኙ ተጠቃሚዎች አማካኝነት ተከናውኗል፡፡

የተሻሻለውን የልማታዊ ሴፍቲኔት የተጠቃሚዎች የክፍያ ሥርዓት አዳዲስ ባህርያት ማለትም አውቶማቲክ ክፍያ ወዘተ... ተግባራዊ የሚያደርጉ ወረዳዎችን ቁጥር ከፍ ለማድረግ በድሬዳዋ፤ በሃረሪ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል ለሚገኙ የወረዳ ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል።

የወረዳ ግንኙነትን (Woreda Connectivity) በተመለከተ የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም በሚተገበርባቸው ክልሎች የሚገኙ የገጠር ወረዳ የግብርና ጽ/ቤቶችን፣ ክልሎችን እንዲሁም ከፌዴራል መረጃ ከሚያቀናጁ እና ከሚጠቀሙ ተቋማት ጋር በወረዳኔት በማገናኘት የመረጃ ቅብብሎሹን የተሳለጠ ከማድረግ አንፃር 96 የPSNP ፓይለት ወረዳዎች የዳታ እና የኢንተርኔት አገልግሎት በወረዳኔት አማካኝነት እንዲገናኙ ተደርጓል። በተጨማሪም የአገልግሎት ክፍያ በተፈፀመባቸው 23 ወረዳዎች ላይ የዝርጋታ ስራው በመከናወን ላይ ይገኛል፡

ለልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ ለክልሎች የሚላከው ሀብት በወቅቱ እንዲላክ ከማድረግ አንፃር በበጀት ዓመቱ ለፕሮግራሙ ማስፈፃሚያ ማለትም ለቋሚ ቀጥታ ድጋፍ እና ለማህበረሰብ የልማት ሥራ ተጠቃሚዎች ክፍያ፤ ካፒታል በጀት፣ የወረዳ አስተዳደራዊና የሠራተኞች ደመወዝ፣ ለክልሎች አስተዳደራዊ በጀት፤ ለክልሎች አቅም ግንባታ በጀት፤ ለኤሌክትሮኒክ ክፍያ እና ለወረዳ አቅም ግንባታ የሚውል በጀት ብር 8,430,299,195.92 ወደ ክልሎች የተላለፈ ሲሆን ክልሎችም ወደ ወረዳ መተላለፍ ያለበትን በጀት ያስተለለፉ መሆናቸውን በተደረገው ክትትል ማረጋገጥ ተችሏል።

የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚዎች ክፍያ ወቅቱን ጠብቆ መጠናቀቁን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ከማረጋገጥ አንፃር በተለያዩ ምክንያቶች ከ2012 በጀት ዓመት ወደ 2013 በጀት አመት የተሸጋገረውን የቋሚና ቀጥታ ድጋፍ እና የማህበረሰብ የልማት ሥራ ተጠቃሚዎች ብር 146,384,684 በታቀደው መሰረት ሙሉ በሙሉ ክፍያው ተፈፅሟል። በተመሳሳይ መልኩ ከ2012 በጀት ዓመት ወደ 2013 የተዘዋወረው የ442,889.71 ኩንታል የምግብ እህል ውስጥ 432,936.75 ኩንታል (97.8%) ለተጠቃሚዎች የተከፈለ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል።

በሌላ በኩል ደግሞ በ2013 በጀት ዓመት ለፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ክፍያ ከጥር እስከ ሚያዝያ ወራት ክፍያ የሚውል የምግብ እህል 128,641 ሜ/ቶን ወደ ማሰራጫ ጣቢያዎች እንዲጓጓዝ የተጠየቀ ሲሆን ከተጠየቀው ውስጥም 89,239 (69%) ሜ/ቶን ወደ ወረዳ ማሠራጫ ጣቢያዎች ተጓጉዞ 68,495 ሜ/ቶን (53%) ለተጠቃሚዎች ክፍያ ተፈፅሟል። በተመሳሳይ መልኩ በበጀት ዓመቱ በአስር ወራት የቋሚ የቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ ለሆኑ የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች

(ከሀምሌ 2012 እስከ ሚያዝያ 30, 2013 ዓ.ም) ክፍያ አገልግሎት የሚውል ገንዘብ ለክልሎች ለመላክ በታቀደው መሰረት ብር 2,758,210,420 የተላለፈ ሲሆን ከዚህ ውስጥም ብር 2,196,390,059 (79.6%) ለተጠቃሚዎች መከፈሉን በተደረገው ክትትልና ድጋፍ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የማህበረሰብ ልማት ተሳታፊዎች ክፍያን በተመለከተ ለተጠቃሚዎች ክፍያ የሚውል የአራት ወራት ክፍያ (ከጥር እስከ ሚያዝያ) ብር 7,200,971,305 ለክልሎች የተላለፈ ሲሆን ከዚህም ውስጥ ብር 4,562,002,400 የተከፈለ ሲሆን አፈፃፀሙም 63.3% ሆኗል፡፡ በዋናነት ለሁለቱም ክፍያዎች ማለትም ለቋሚ ቀጥታ ድጋፍ እና ለማህበረሰብ ልማት ሥራ ተሳታፊዎች ክፍያ አፈፃፀም ማነስ ዋነኞቹ ምክንያቶች የብሔራዊ ባንክ መመሪያ ማለትም በቀን ከባንክ የሚወጣ የገንዘብ ጣሪያ ከ50 ሺህ ብር እንዳይበልጥ ስላገደ ለክፍያ የሚያስፈልገውን ገንዘብ በበቂ መጠን አውጥቶ ለተጠቃሚው መክፈል ለመፈፀም ባለመቻሉ እና በወረዳ ደረጃ የሚገኙ ባንኮች በካዝናቸው በቂ ገንዘብ የመያዝ አቅም ዝቅተኛ መሆን ናቸው፡፡

የኮቪድ ምላሽ ክፍያን በተመለከተ በስድስት ክልሎች /ሶማሌ፣ ደቡብ ብ/ብ/፣ ሲዳማ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ እና አፋር/ ለሚገኙ 2,540,844 ተጠቃሚዎች ብር 1,449,480,904 እና ለ274,243 ተጠቃሚዎች ደግሞ የ8,227.29 ሜ/ቶን እህል በታቀደውና በተላከው መሠረት ለተጠቃሚዎች ክፍያው ሙሉ ለሙሉ መፈፀሙን በተደረገው ክትትልና ድጋፍ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

6,803,770 የተፈጥሮ ሀብት ልማት ተጠቃሚዎች በህብረተሰብ ተሳትፎ የማህበረሰብ የልማት ስራዎች በማከናወን የወል ጥሪት እንዲገነባ ከማድረግ አንፃር ተያያዥነት ባላቸው በተለያዩ ርዕሶች ላይ ለባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ክትትልና ድጋፍ ሥራዎችን አስመልክቶ በአርብቶ አደር ክልሎች አፋርና ሱማሌ እንዲሁም በሲዳማ ክልል የ6 ወር አፈጻጸምና በማህበረሰብ የልማት ሥራዎች የግጦሽ መሬትና ተፋሰሶች ላይ የሚሰሩ የአፈርና ውሀ ጥበቃ ሥራዎች ቅድመ ዝግጅትና ትግበራ ያለበትን ደረጃ ክትትልና የመስክ ድጋፍ ተካሂደል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በአፈፃፀም ላይ የምክክር መድረኮችን ከማካሄድ አንፃር በዕቅድ ላይ ከክልል ባለድርሻ ኣካላት ጋር የምክክር መድረክ ተካሄዷል፡፡

በ5ኛው ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ዕቅድ መሰረት የአካባቢና ማህበራዊ አያያዝ ማዕቀፍ የማሰልጠኛ ማኑዋሎች የተዘጋጁ ሲሆን የአየር ንብረት ለውጥ ተስማሚነት ለማስረፅ ለታችኛው ፈፃሚዎች መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚዎች (141,883) በቤተሰብ ደረጃ ጥሪት እንዲገነቡ ከማድረግ አንፃር በ2012 በጀት ዓመት በሌሎቹ ክልሎች የአንድ ጊዜ የቤተሰብ ጥሪት መፍጠሪያ ድጋፍ ተሰጥቶ የተጠናቀቀ ሲሆን በኦሮሚያ ክልል ግን በጀት ዓመቱ መሠራጨት ሲገባው ሳይሰራጭ ቀርቶ ወደ 2013 በጀት ዓመት የዞረ የአንድ ጊዜ የቤተሰብ ጥሪት መፍጠሪያ ድጋፍ 5,218,776 ብር በአራት ወረዳዎች ለሚገኙ 601 ወንድ እና 287 ሴት በድምሩ ለ888 ተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡ በተጨማሪ በ2012 በጀት ዓመት የአንድ ጊዜ የቤተሰበ ጥሪት መፍጠሪያ ድጋፍ ያገኙ የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች የተሰጣቸውን ድጋፍ ለታለመለት አላማ ማዋላቸውንና ጥሪት መፍጠራቸውን ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡

በ2012 በጀት ዓመት ተዘጋጅተው ወደ 2013 በጀት ዓመት ለዞሩ 6,083 በዝነስ ፕላኖች ወይም የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ድጋፍ ተጠቃሚዎች (44 በመቶ ሴት) 77.6 ሚሊዮን ብር የብድር አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡

በአርብቶ አደር ክልሎች የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራምን ለማስጀመር በሶማሊና አፋር ክልሎች ባለሙያዎች እና ባለ ድርሻ አካላት ጋር ውይይት እና የዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል፡፡ በዚህም መሰረት በአርብቶ አደር ክልሎች ተጠቃሚዎች ሊሳተፉባቸው የሚችሉባቸው የስራ ዘርፎች (Livelihoods Pathways) የተለዩ ሲሆኑ በክልሎቹ ያሉ የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያን በቀጣይ ለማስጀመር የማያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች እና ተግዳሮቶች ተለይተው ማስተካከያ እርምጃዎች እንዲተገበሩ ክልሎች ከስምምነት ተደርሷል፡፡

አየር ሁኔታን ያማከለ የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ትግበራ እና የንግድ እቅድ ዝግጅት ስልጠና ከክልሎች ጋር በመሆን ወደ ወረዳ ባለሙያዎች ለማውረድ በተያዘው እቅድ መሰረት ለአማራ፤ ለደቡብ፤ ለኦሮሚያ ክልሎች የወረዳ ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ የእቅድ ዝግጅት መመሪያ በማዘጋጀት ለክልሎች የተላከ ሲሆን ይህም ከክልሎች የሚመጣው እቅድ ተመሳሳይ ወጥነት ያለው እና ማካተት የሚገባውን የሚይዝ እንዲሆን ያግዛል፡፡ በተጨማሪም የፕሮግራሞች የእቅድ እና የአፈፃፀም ሪፖርት ማቅረቢያ ቅፆችን በሁሉም ክልሎች የተወከሉ ባለሙያዎች በማሳተፍ በአዲሱ ምዕራፍ እይታዎች የተቃኘ ክለሳ ተደርጓል፡፡

የ5 ምዕራፍ የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም በፌዴራል ደረጃ ከክልሎች፣ ከፌዴራል ባለድርሻ አካላት እና ከለጋሽ ድርጅቶች ጋር የጋራ የምክክር መድረክ በማካሄድ ፕሮግራሙን በይፋ የማስጀመሪያ መድረክ እንዲካሄድ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ከመጋቢት 27/2013 እስከ ሚያዚያ 27/2013 ዓ.ም ድረስ በክልሎች ደረጃ በይፋ ፕሮግራሙን የማስጀመሪያ መድረክ ካስኬድ ተደርጎ ተጠናቋል፡፡ በቀጣይም የፕሮግራሙን የአፈፃፀም መመሪያ የማስተዋወቅ ሥራ በተከታታይ በየክልሉ ለሚገኙ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

በ2012 በጀት ዓመት ሊገዛ ዕቅድ ተይዞለት የግዢ ሂደቱ ሳይጠናቀቅ ወደ 2013 በጀት ዓመት የዞረ የ75,000 ሜ/ቶን ስንዴ ግዢ ከአቅራቢ ድርጅቱ ጋር ውል የተፈረመ ሲሆን ድርጅቱ 64,500 ሜ/ቶን ስንዴ በአንድ መርከብ በመጫን ወደ መቀሌና ኮምቦልቻ ማዕከላዊ መጋዘኖች በማጓጓዝ ርክክቡ ተፈጽሟል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ከ2012 በጀት ዓመት የዞረ የ80,000 ሜ/ቶን ስንዴ ግዢ ሂደት ተጠናቆ 30,000 ሜ/ቶን ከሚገዛበት ሃገር የተጫነ ሲሆን ለቀሪው 50,000 ሜ/ቶን ስንዴ ለማስጫን መርከብ በማፈላለግ ላይ እንደሆነ ከአስመጪው ለመረዳት ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል በ2013 በጀት ዓመት ሊገዛ የታቀደው 80,000 ሜ/ቶን ስንዴ ግዢ ለመፈፀም በዓለም ባንክ የግዢ መመሪያ መሠረት የጨረታ ሰነዱ ተዘጋጅቶ ለዓለም ባንክ ተልኮ የይሁንታ መልስ (No Objection) ተገኝቶ ሌሎች ሥራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡ በተመሣሣይ መልኩ ለትግራይ ክልል ከዓለም ባንክ በተገኘ የበጀት ድጋፍ 30,000 ሜ/ቶን ስንዴ ለመግዛት የጨረታ ሂደቱ ተጠናቆ አሸናፊው ድርጅት ስንዴውን ለማስጫን መርከብ በመምረጥ እንደሆነ ታውቋል፡፡

### 3.5 የግብርና ምርምር

የግብርና ቴክኖሎጂዎችና መረጃዎች ለማውጣት በ2013 በጀት ዓመት 2,417 የምርምር ሙከራዎችን እና ጥናቶችን ለማካሄድ አቅዷል፡፡ በበጀት ዓመቱ 2,269 (የዕቅዱ 94 በመቶ) ሙከራዎች የተከናወኑ ሲሆን ከዚህም ውስጥ የ369 ሙከራዎች ጥናት ተጠናቋል፡፡ በጸጥታ ችግር፣ በውጭ ምንዛሪ ዕጥረት እና ግብዓቶች በጊዜ ባለመቅረባቸው እና በጠብታ መስኖ መሳሪያ ግዢ መዘግየት ምክንያት 21 ሙከራዎች ያልተጀመሩ ሲሆን 127 ሙከራዎች በጎርፍ አደጋ፣ በበረዶ እና በዘረ መል እጥረት፤ በበሽታ፣ በጸጥታ ችግር፣ በኤሌትሪክ ሃይል መቆራረጥ፣ ለኬሚካል ፍተሻ እና ብቃት ማረጋገጫ የሚውል ኬሚካል ከአቅራቢ ካምፓኒው ባለማቅረቡ ምክንያቶች ለጊዜው ተቋርጠዋል፡፡

### የቴክኖሎጂና መረጃ አቅርቦት አፈጻጸም

በተለያዩ የምርምር መስኮች በተጀመሩና በበጀት ዓመቱ ተከናውነው በሚጠናቀቁ የምርምር ተግባራትና መዳረሻ ውጤቶች ላይ የተመሰረቱ 107 ቴክኖሎጂዎች እና 415 መረጃዎች በድምሩ 522 ውጤቶችን ለማውጣት የታቀደ ሲሆን በበጀት ዓመቱ 458 (ከዓመቱ 88 በመቶ) የምርምር ውጤቶች (104 ቴክኖሎጂና 354 መረጃዎች) ተገኝተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ባለፈው በጀት ዓመት ለዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ቀርበው የነበሩና መጽደቃቸው በዚህኛው በጀት ዓመት የተረጋገጠላቸው ሌሎች 30 ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ ይውሉ ዘንድ ወጥተዋል፡፡

### የቴክኖሎጂ ማላመድ ሥራዎች አፈጻጸም

ለአገሪቱ የግብርና ቀጠናዎች ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በመደበኛ ፕሮግራም በምርምር ከማፍለቅ ጎን ለጎን ከውጭ አገር ያለቀላቸውን ቴክኖሎጂዎች በማስመጣት በ2013 የበጀት ዓመት 91 (72 የሰብል፣ 2 የእፅዋት ጥበቃ፣ 3 የእንስሳት፣ 3 የእንስሳት መኖ፣ 7 የግብርና ምህንድስና፣ 2 የግብርና ባዮቴክኖሎጂ እና 2 የአየር ጠባይና ጂኦስፓሻል) ምርትና ምርታማነትን በማሻሻል ለምግብ ዋስትና፣ ለውጭ ገበያና ለአግሮ ኢንዱስትሪ ግብዓት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ዝርያዎችን /ቴክኖሎጂዎችን/ የማላመድ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ በበጀት ዓመቱ 4 የሰብል እና 3 የእንስሳት መኖ ዝርያዎች የማላመድ ጥናታቸው ተጠናቆ ለብሔራዊ የዝርያ አፅዳቂ ኮሚቴ ለግምገማ የቀረቡ ሲሆን ሶስት የእንስሳት መኖ ዝርያዎች (አንድ አልፋልፋ ዝርያ፣ አንድ ብራካሪያ ዝርያ እና አንድ የመኖ ሲናር ዝርያ) በግብርና ሚኒስቴር የዝርያ ገምጋሚና አጽዳቂ ኮሚቴ እንዲመዘገቡ የተፈቀደ ሲሆን በሰብል ምርምር እንዲጠናቀቁ በዕቅድ ተይዘው የነበሩት ዝርያዎች የተሰበሰበው መረጃ በቂ ባለመሆኑ ምክንያት እና የተሟላ መረጃ ለዝርያ አጽዳቂ ባለመቅረቡ እና ችግኝ ለማባዛት ጊዜ በመውሰዱ ስላልተጠናቀቀ በቀጣይ ዓመት አሟልቶ ለማስገምገም ተወስኗል፡፡

### የቴክኖሎጂ ማስተዋወቅ ሥራዎች አፈጻጸም

በ2013 በጀት ዓመት አዳዲስና ነባር ቴክኖሎጂዎችና መረጃዎችን ለ38,687 (28,759 ወንድና 9,928 ሴት) አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮች፣ የልማት ጣቢያ ሠራተኞች፣ የግብርና ባለሙያዎች፣ የዘር አባዦች፣ የግል ባለሃብቶች እና ከተለያዩ የልማት ድርጅቶች ለተውጣጡ አካላት የማስተዋወቅ ሥራዎች የታቀዱ ሲሆን ለ41,886 (30,964 ወንድና 10,922 ሴት) ተጠቃሚዎች የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅ ከዕቅድ በላይ ተከናውኗል፡፡ በሌላ በኩል ከዕቅድ ውጭ በድምሩ ለ1,576 (1,309 ወንድ እና 267 ሴት) አርሶ አደሮች፣ የልማት ጣቢያ ሠራተኞችና የግብርና ባለሙያዎች በእጽዋት ጥበቃ እና በተቀናጀ ቴክኖሎጂ የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪም 1,047 ሄክታር ኩታ-ገጠም በሆነ መሬት ላይ በስንዴ፣ በቢራና በምግብ ገብስ እንዲሁም በጤፍ ሰብሎች አሲዳማ አፈርን በኖራ የማከም ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ላይ የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡

## የቴክኖሎጂ ማስፋት ሥራዎች አፈጻጸም

ኢንስቲትዩትቱ አርሶ አደሩን፣ አርብቶ አደሩን፣ ከፊል አርብቶ አደሩን፣ የልማት ጣቢያ ሠራተኞችን፣ የግብርና ባለሙያዎችን፣ የዘር አባዦችን እንዲሁም በግብርና መስክ በሚሳተፉ የግል ባለሀብቶችንና ድርጅቶች በቴክኖሎጂ ተደራሽ ለማድረግ በበጀት ዓመቱ ለ50,232 (38,400 ወንድ እና 11,832 ሴት) ቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች የቅድመ ማስፋት ሥራዎች ታቅዶ፤ 47,076 (36,784 ወንድ እና 10,292 ሴት) የዕቅዱ 94 በመቶ ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርጓል።

የቴክኖሎጂ ማስፋት ስራውን ለማጠናከር ከመስክ ስራው በተጓዳኝ ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉባቸው 4 የፓናል ውይይቶችና 12 የመስክ ቀኖች 10 የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ፣ በኢንስቲትዩቱ የምርምር ውጤቶችና ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ 5 የቴሌቪዝን ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ለመላ ተጠቃሚው እንዲሰራጭ፤ እንዲሁም ሣምንታዊ የሬዲዮ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት 8 የምርምር መረጃዎችን ለአርሶና አርብቶ አደሮች የማስተዋወቅ፣ 10 በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ እና በሌሎች ጋዜጦች ላይ አርቲክሎችን በማዘጋጀትና በማሳተም የማሰራጨት፣ የኢንስቲትዩቱን የምርምር ውጤቶች የሚያስተዋውቁ፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ቡክሌቶች፣ ፓስተሮች፣ ባነሮች የማዘጋጀትና የማሰራጨት ስራዎች እንዲሁም 2 የግብርና ምርምር ሚዲያ አካላት ፎረም መመስረትና ተቋማዊ ገጽታ የመገንባት ስራዎች ተከናውነዋል።

ለክልል የምርምር ተቋማት ፕሮጀክቱ ላይ ያተኮረ ምርምርና ምርት ተግባር የሚውል ዘር፣ ማዳበሪያ እና ኬሚካል እንዲሁም የስራ ማስኬጃ በጀት ብር 211,306,691 ተልኳል። በኢንስቲትዩቱ ስር ባሉ የምርምር ማዕከላት 500 ሄ/ር መሬት የሰርቶ ማሳያ ስራዎች ተከናውኗል። የዳቦ ስንዴ ቅድመ መስራች ዘር በ111 ሄ.ር መሬት ላይ እንዲመረት እንዲሁም ለቆላማ አካባቢዎች የሚውሉ በአዳቃይ ዘር ደረጃ አስር የስንዴ ዝርያዎች በ1.25 ሄክታር ላይ እንዲባዙ ተደርጓል።

## ለቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች የተሰጠ የአቅም ግንባታ ስልጠና

ኢንስቲትዩቱ በበጀት ዓመቱ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ የአሰራር (አመራረት) ዘዴ፣ አያያዝ (እንክብካቤ)፣ በእንስሳት እና እፅዋት በሽታዎች ቅድመ መከላከልና ቁጥጥር ዘዴዎች ላይ ለ45,112 (32,052 ወንድና 13,060 ሴት) አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮች፣ የልማት ጣቢያ ሠራተኞች፣ የግብርና ባለሙያዎች፣ የዘር አባዦች፣ የግል ባለሀብቶች እና ከተለያዩ የልማት ድርጅቶች ለተውጣጡ አካላት የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎች ለመስጠት ታቅዶ 38,754 (27,801 ወንድና 11,020 ሴት) የዕቅዱን 85.9 በመቶ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎችን ማስልጠን ተችሏል። በጸጥታ ችግር እና በኮቪድ-19 ምክንያት በአንድ ፕሮግራም የሚሳተፉ አካላት ቁጥር ውስን በመሆኑ ምክንያት በተወሰኑ ዘርፎች ላይ ከዕቅድ በታች የሆነ አፈጻጸም ታይቷል። ይሁን እንጂ ቀደም ብለው ባልታቀዱ ዘርፎች የስልጠናው

አስፈላጊነት ታምኖበት በተጨማሪ ለ1,932 (1,237 ወንድና 695 ሴት) አርሶ አደሮች፣ የልማት ጣቢያ ሠራተኞችና የግብርና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

## የመነሻ ቴክኖሎጂ ብዜት ስራዎች

በግብርና ልማቱ ወቅታዊና መሰረታዊ ፍላጎት ላይ በማተኮር በምርምርና በማላመድ የወጡ ቴክኖሎጂዎችን በማባዛት ለወደፊቱ ተጠብቀው እንዲቆዩ እንዲሁም ለተጠቃሚዎች በቀጥታ እንዲተላለፉ ለማድረግ የተሰሩ ስራዎች አፈጻጸም እንደሚከተለው በየቴክኖሎጂው ዓይነት ተለይቶ ቀርቧል፡፡

## የሰብል ቴክኖሎጂዎች ብዜት

### የሰብል ቴክኖሎጂዎች አራቢ ዘር ብዜት

በበጀት ዓመቱ 9,985.58 ኩንታል ዘር፣ 1,039,600 ችግኝ እና 416,200 ቁርጥራጭ በአራቢ የዘር ደረጃ ለማባዛት ታቅዶ፤ 12,946.2 ኩንታል ዘር 1,375,040 ችግኝ እና 7,543,825 ቁርጥራጭ ተባዝቷል፡፡ በተጨማሪም 3,000 የሀረግ ቦዬ ኮረት፣ 6,000 የሙዝ ግንጣይ፣ 9,230 የአናናስ ሳከር፣ 40,000 የአቮካዶ እና ማንጎ ቀንበጥ በዕቅድ ባይያዝም ዘግይቶ በመጣ የተጠቃሚ ፍላጎት መሰረት ሊባዛ ችሏል፡፡

## የእንስሳት እና የእንስሳት መኖ ቴክኖሎጂዎች ብዜት

በእንስሳት ቴክኖሎጂዎች ብዜት በ2013 የበጀት ዓመት 1,500 ሌይንግ የሐር ትል እንቁላል፣ 120 ጊደሮች፣ 10 ወይፈኖች፣ 270 አውራ በጎች፣ 95 ኮርማ ፍየሎች፣ 409,000 የ1 ቀን የዶሮ ጫጩት እንዲሁም 1,100,000 የዓሳ ጫጩት ለማባዛት ዕቅድ ተይዞ፤ 1,250 ሌይንግ የሐር ትል እንቁላል፣ 176 ዲቃላ ጊደሮች፣ 37 ወይፈኖች/ኮርማዎች፣ 608 አውራ በጎች፣ 107 አውራ ፍየሎች፣ 351,238 የ1 ቀን የዶሮ ጫጩት እንዲሁም 1,066,800 የዓሳ ጫጩት ተባዝተዋል፡፡

የእንስሳት መኖን በተመለከተ በ2013 በጀት ዓመት ለእንስሳት የሚሆኑ 459.52 ኩንታል ዘር፣ 50,500 ቁርጥራጭ፣ 5,315,000 ዝንጣይ እንዲሁም 147,700 ችግኝ ለማባዛት፣ ለንብ መኖ የሚሆኑ 6 ኩንታል የጉሎ ተክል፣ 10,000 ቁርጥራጭ የእንጆሪ ተክል ለማባዛት ታቅዶ፤ 574.3 ኩንታል፣ 130,000 ቁርጥራጭ፣ 6,765,500 ዝንጣይ፣ እና 294,100 ችግኝ ተባዝቷል፡፡ እንዲሁም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ድጋፍ የሚሹ ክልሎች 2,245 የኮኮክ ጫጩትና ለአፈር ዕቀባ 30,000 የቨቲበር ሳር ዝንጣይ ተባዝተዋል፡፡ አጠቃላይ አፈጻጸሙ ከመቶ በላይ ነው፡፡

## የተፈጥሮ ሃብት ቴክኖሎጂዎች ብዜት

በበጀት ዓመቱ የአፈር ለምነትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ 10,000 ፓኬት የራይዞቢያ ሕየው-ማዳበሪያ (ባዮፈርቲላይዘር)፣ 1 ኩንታል የቨርሚኮምፖስት ትል እንዲሁም 20 ኩንታል ቨርሚኮምፓስት (የተፈጥሮ ማዳበሪያ) በበጀት ዓመቱ ለማባዛት ታቅዶ፤ 7,100 ፓኬት የራይዞቢያ ሕየው-ማዳበሪያ፣ 2.83 ኩንታል የኮምፖስት ትል፣ 28 ኩንታል ቨርሚኮምፓስት (የተፈጥሮ ማዳበሪያ) ተባዝቷል፡፡ በተጨማሪም ለተቀናጀ የተፋሰስ አያያዝ ስራዎች የሚውሉ 48,550 ችግኞች እና 705,888 ቁርጥራጮች ተባዝተዋል፡፡

### የባዮቴክኖሎጂ ቴክኖሎጂዎች ብዜት

በግብርና ባዮቴክኖሎጂ በመደገፍ በ2013 የበጀት ዓመት 229,500 (የቡና፣ የዝንጅብል፣ የአናናስ፣ የአፐል፣ የፐለም፣ የድንች፣ የስኳር ድንች፣ የኮክ እና የሙዝ) ችግኞች ለማባዛት ታቅዶ፤ 256,126 ችግኞች ተባዝተዋል፡፡ አጠቃላይ አፈጻጸሙ ከመቶ በላይ ነው፡፡

### የግብርና ምህንድስና ቴክኖሎጂዎች ብዜት

በግብርና ምህንድስና መስክ በበጀት ዓመቱ ለምግብ ዋስትና እና ለተፈጥሮ ሃብት አያያዝ ጠቀሜታ የሚሰጡ 545 ልዩ ልዩ የቅድመ-ምርት፣ ምርት እና ድህረ-ምርት የእርሻ መሣሪያዎችን ለማባዛት የታቀደ ሲሆን፤ 549 የተሻሻሉ የእርሻ መሣሪያዎች ተባዝተዋል፡፡ አጠቃላይ አፈጻጸሙ ከመቶ በላይ ነው፡፡

### ሀገራዊ የግብርና ምርምር ስርዓት ግንባታ ማስተባበር

የክልል ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተሮች በፌደራል ደረጃ የሚገኙ የግብርና፣ የደን እና አካባቢ ጥበቃ እንዲሁም የብዝሃ ሕይወት ምርምር ኢንስቲትዩቶች እና የሰባት ዩኒቨርሲቲዎች የምርምር ምክትል ፕሬዘዳንቶች እንዲሁም ተጋባዥ እንግዶች ተሳታፊ የሆኑበት የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት አምስተኛ መደበኛ ጉባኤ ተካሂዷል፡፡ በጉባኤው 3 አጀንዳዎች ለውይይት የቀረቡ ሲሆን የሴክሬታያቱ የአምስት ዓመት እና የበጀት ዓመቱ ሪፖርት ቀርቦ ውይይት ተደርጎበት ግብአት የተሰበሰበበትና በቀጣይ ጊዜያት ሊተገበሩ በሚገባቸው ጉዳዮችም ላይ አቅጣጫ የተቀመጠበት ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ምክር ቤቱ እና ሴክሬታሪያቱ የተቋቋመበትን ደንብ ለማሻሻል የቀረበውን አጀንዳ በጥልቅ የገመገመ ሲሆን፤ ማሻሻያ ነጥቦች በሕግ አግባብ ተቃኝተው በአዋጅ እንዲወጡ እንዲደረግ አቅጣጫም ተቀምጧል፡፡

የምርምር ሥርዓቱን የምርምር ሰው ኃይል አቅም ከመገንባት አንፃር የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር `ቤት ሴክሬታሪያት ከተለያዩ ዓለም አቀፋዊና የአገር ውስጥ ተቋማት ጋር በመተባበር ከሥርዓቱ ለተውጣጡ 536 ተመራማሪዎች፣ ቴክኒሽያኖች፣ ዩኒቨርሲቲ መምህራን፣ የሥራ መሪዎች እና ባለሙያዎች በተለያዩ የምርምር ስፔሻላይዜሽኖች ዙሪያ የክህሎት ማዳበሪያ የንድፈ-ሃሰባና የተግባር ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ ከስልጠና አኳያ ሴክሬታሪያቱ የእቅዱን ከመቶ ፐርሰንት በላይ የሆነ አፈፃፀም አስመዝግቧል፡፡ የተሰጡት ስልጠናዎችም በሶፍትዌር የተደገፈ የመኖ ቀመር አዘገጃጀትና በዘመኑ የእንስሳት ሥነ-ምግብ አስተሳሰቦች፣ በማዳበሪያ ምርምር አተገባበር፣ መረጃ አያያዝ እና በመረጃ ትንተና፣ በProduction Efficiency ምርምር ፅንሰ ሀሳብ እና የአተገባበር ቴክኒክ፣ በገበያ መር የዕፅዋት ዝርያ ማዳቀል ምርምር፣ የግብርና ኢኮኖሚክስ/የኤክስቴንሽን ምርምሮች የቅኝት (Sample Survey) ጥናቶች የመረጃ አሰባሰብ ሂደትን ኦቶሜት በማድረግ፣ ነፍሳትና ተባይን ለምርምርና ለስነ ሕይወታዊ የተባይ መቆጣጠሪያነት ማባዛት ስለሚቻልበት ዘዴ፣ በአድቫንስድ የሆርቲካልቸር ዘር አመራረትና የነርሰሪ ማኔጅመንት፣ በአግሪቢዝነስ ተኮር ተቋማዊ አመራር እና ኤክስቴንሽን አሰራር ስልቶች፣ በባዮማስ ፕሮሰሲንግ ምርምር ተግባራት የሙያ ዘርፎች ላይ ያተኮሩ ነበሩ፡፡

በአዳዲሶቹ ማዳበሪያዎች ዙሪያ የማረጋገጫ ጥናትና የፖሊሲ ምክረሃሳብ ሥራ በአገር ደረጃ በምርምር ተቋማት እና በሌሎች ምርምር በሚሰሩ አለም አቀፍ ድርጅቶች በጋራ እንዲፈጸም በተደረሰው ስምምነት መሰረት ሥራው ወደ ትግበራ ገብቷል፡፡ የተሟላ ግብዓት ለሌላቸው ተቋማት ግብዓቱን ከአጋር ድርጅቶች ጋር ድጋፍ በማፈላለግ ፎስፎረስ (100 ኩንታል)፣ ሰልፈር (100 ኩንታል)፣ ዚንክ (10 ኩንታል) እና ቦሮን (5 ኩንታል) ከውጭ ሀገር በትብብር እንዲገዙ በማድረግ ለፈጻሚ ተቋማት በማሰራጭት ፕሮጀክቱ እንዲጀመር ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ለ2013/14 በጀት ዓመት የሚያስፈልገውን 28 ሚሊዮን ብር በጀት በማፈላለግ ለተቋማቱ እንዲተላለፍ ተድርጓል፡፡ ፕሮጀክቱን ለማስጀመር ለ35 ወጣት ተመራማሪዎች ለ10 ቀናት የቆየ ጥልቀት ያለው ሥልጠና በዘርፉ በቂ እውቀትና ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች እንዲሰጣቸው ተደርጓል፡፡ ፕሮጀክቱም በበቆሎ፣ ጤፍና ስንዴ ሰብሎች ላይ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

ትራንስሌሽናል ምርምርን ከማስተባበር አኳያ ከደቡብ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር የአኩሪ አተርና የሱፍ ቅባት ሰብሎችን በደቡብ ኦሞ አካባቢ በሰፊው ለማስተዋወቅ በተደረገው ሙከራ በተለይ 130 ኩንታል የሱፍ ዘር የተመረተ ሲሆን ይህም 800 ሄክታር መሸፈን ይችላል፡፡ በዚሁ ስፍራ ከተካሄደው ለውዝን የማላመድ ሙከራ 34 ኩንታል በሄክታር ምርት ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም በዚህ አካባቢ ዘር ከፎገራ ብሄራዊ የሩዝ ምርምር ማዕከል በመውሰድ 16 የሩዝ ዝርያዎች ለምርታማነታቸው ተሞክረው በአገራችን ብቻ ሳይሆን በአፍሪካም እጅግ ከፍተኛ የሚባል እስከ 87 ኩንታል በሄክታር የደረሰ ምርት ተገኝቷል፡፡ በጋምቤላ ክልል ከጋምቤላ ግብርና ምርምር ኢንስትቲትዩት ጋር በመተባባር በሁለት ወረዳዎች ውስጥ በያንዳንዳቸው 10 ሄክታር የሰሊጥ ዝርያ ሁመራ አንድና አስር ሄክታር የሱፍ ዝርያ ኦሌሳ ለዘር ብዜትና ሰፊ የማስተዋወቅ ሙከራ በመካሄድ ላይ ነው፡፡ በተመሳሳይ በምዕራብ ጎጃም ዞን ከአማራ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ጋር በመተባባር በሰባት ሄክታር ላይ የአኩሪ አተር ፓዊ 1 ዝርያ ዘር በመባዛት ላይ ሲሆን ይኸው ዝርያ በ28 ሄክታር ላይ ሰፊ የማስተዋወቅ ስራዎች በመሰራት ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት ሴክሬታሪያት አስተባባሪነት የሶማሌ ክልል የአርብቶና ከፊል አርብቶ አደር ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ዘመናዊ የዶሮ እርባታ ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ወጣቶች ወደ እርባታ ሥራው እንዲገቡ ለማበረታታት፤ የእውቀትና ክህሎት ሽግግር በማድረግ ለወጣቶቹ ተጠቃሚነታቸውን ለማሳየትና ሥራውም በቀጣይ እንዲሰፋፋ ለማስተዋወቅ በደብረ ዘይት ግብርና ምርምር ማዕከል የቴክኒክ ድጋፍ እየተሰጠ የዶሮ እርባታ ሥራ በማከናወን በቀን እስከ ስድስት መቶ እንቁላል ለገበያ በማቅረብ ወጣቶቹ ገቢ በማግኘት ላይ ይገኛሉ፡፡ ከኦሞ ወንዝ የመስኖ ውሃ በመጥለፍ የመስኖ ውሃ ፓምፕ ተተክሎና የመስኖ መስመር ተዘርግቶ በ10 ሄክታር መሬት ላይ የመኖ ልማት ስራ ማከናወን ተችሏል፡፡ ከዚህም በመኖ ዘር ሽያጭ ከሚገኘው ጥቅም ባለፈ የኦሞ ወንዝ መሙላትን ተከትሎ በተከሰተው ጎርፍ ለተፈናቀሉ የአርብቶ አደሮች እንስሳት መኖ አቅርቦት በምንጭነት ያገለገለ ሲሆን ችግሩንም ለማቃለል የበኩሉን አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

የምግብ ዘይት እጥረትን ለማቃላል የቅባት እህሎችና የምግብ ዘይት ባለድርሻ አካላትን ያካተተ የሁለት ቀን አውደ ጥናት ተካሂዷል፡፡ የምክክር መደረኩ ዓላማም በቅባት እህሎች ላይ ያሉ ቴክኖሎጂዎች፣ እውቀቶችንና ልምዶችን መቀመርና የልማቱ መነሻ ግብዓት እንዲሆኑ ማድረግ፣ ለግብርና ኢንዱስትሪዎች ልማት ያሉ የፖሊሲ ማበረታቻዎችን ፋይዳ መገምገምና እጥረቶቹን ማሳየት፣ ለቅባት እህሎች ኢንዱስትሪ ውጤታማነት በቀጣይ መስራት የታሰበውን የፐብሊክ-ፕራይቬት አጋርነት ፕሮጀክት መገምገምና ማዳበር እንዲሁም በቅባት እህሎች ምርምር፣ ልማትና ኢንዱስትሪ የተሳለጠ ትስስር ላይ በቅርበት የሚሰራ አገራዊ አማካሪ ኮሚቴ ማቋቋም ነው፡፡ በተጨማሪም አጠቃላይ ግብ ተደርጎ የተነሳው ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማስተባበር በቅባት እህሎች ላይ ፈጣን የቴክኖሎጂ ሽግግር በማረጋገጥ ለሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች በቂ ጥሬ ምርት በማቅረብ የተፈጠረውን የምግብ ዘይት ዕጥረት በመጪው 10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ መቅረፍ እና ለዶሮና ስጋ ኢንዱስትሪ የሚውል የፋጉሎ መኖ በማቅረብ ዘርፉ በውጭ ምንዛሪ ግኝት ላይ ጠንካራ ድርሻ እንዲኖረው መሰረት መጣል ነው፡፡

በCompetitive Research Grant መልክ በመደገፍ ከኒም ዛፍ በሚገኝ ቅጠልና ዘይት አዲሱን መጤ ተምች ለስነ ምህዳር ተስማሚ በሆነው ስነ-ሕይወታዊ ፀረ-ተባይ ለመቆጣጠር የሚያስችል ተግባራዊ ምርምር እንዲካሄድ ሴክሬታሪያቱ ከኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ የሆርቲካልቸር ዘርፉን በሚቀጥሉት 10 ዓመታት በመምራት ትራንስፎርም በማድረግ ሀገሪቱ ያላትን ዕምቅ አቅም በሚገባ ለመጠቀም እንዲያስችል ታስቦ በግብርና ሚ/ር እና በሴክሬታሪያቱ ትብብር በመዘጋጀት ላይ ያለው የኢትዮጵያ የሆርቲካልቸር ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ፍኖተ-ካርታ ዝግጅት ተጠናቆ ለመጨረሻ ቫሊዴሽን ቀርበዋል፡፡ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በስፋት ወደ አርሶ አደሮች በማድረስ ጉልህ ፋይዳ ለመፍጠር የምርምርና ልማት እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲሁም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በቅንጅት የአርሶ አደሩን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎችን ለመተግበር የሚያስችል አሰራር ስርዓት (ማንዴት ዞኔሽን) የማስተዋወቅ፣ ግንዛቤ የመፍጠርና ስርዓቱን የመዘርጋት ስራዎች በአማራ፣ በኦሮሚያ እና በደቡብ ክልል በተመረጡ ዞኖች ላይ ተከናውነዋል፡፡

በአገራችን የእንጉዳይ (Mushroom) አመራረት እና ንግድ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመለየት እና ዘርፉን ለማጠናከር እንዲረዳ 66 ባለሙያዎች እና ከፍተኛ ኃላፊዎች (60 ወንድ 6 ሴት) የተሳተፉበት አገራዊ ሲምፖዚየም ተካሂዷል፡፡ በተጨማሪም እንጉዳይ ያለውን ዘርፈ ብዙ አገራዊ ጠቀሜታ ዕውቅና ተሰጥቶት የበለጠ ለማጠናከር እንዲቻል በየዓመቱ ግንቦት 23 (March 31) የእንጉዳይ ቀን ተብሎ እንዲከበር ተወስኗል፡፡ በተጨማሪም የእንጉዳይ ምርምርና የቴክኖሎጂ ስርፀት ለማሳለጥ ያስችል ዘንድ የምርምር ፕሮግራሙ በሆለታ ብሄራዊ ባዮቴክኖሎጂ ምርምር ስር እንደ አንድ አገራዊ ፕሮግራም እንዲተከል ተደርጓል፡፡

## 3.6 ህብረት ስራ ማህበራት

ማህበራትን ማጠናከርና ማደራጀትን በተመለከተ በዓመቱ 16,885 ለማጠናከር ታቅዶ 12,611 መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ማጠናከር ተችሏል፡፡ የዕቅዱን 100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡ 1,000 መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ለማደራጀት ታቅዶ 5,756 መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ማደራጀት ተችሏል፡፡ የዕቅዱ አፈጻጸም ከ100% በላይ ነው፡፡ 1.2 ሚ (ወንድ 500,000 ሴት 500,000 ወጣት 200,000) አባል ለማድረግ ታቅዶ በክንዉን ደረጃ 1,572,958 (ወንድ 1,016,937 (+100 %)፣ ሴት 555,942 (+100 %)) የተከናወነ ሲሆን በአጠቃላይ የዕቅዱን 100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራትን በተሰማሩበት ዘርፍ ጠንካራ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የውስጥ የካፒታል አቅማቸዉን ለማሳደግ የማጠናከር ሥራ በመስራት እንዲሁም አዳዲስ ኅብረት ሥራ ማህበራት በጠንካራ የካፒታል አቅም ለማቋቋም በዓመቱ ብር 2,280,000,000 ካፒታል ለማሳደግ ታቅዶ ክንዉኑ ብር 2,884,657,410 የካፒታል አቅማቸዉን ማሳደግ ተችሏል፡፡ በመሠረታዊ 1,852,812,447፤ በዩኒየን 666,527,210 ፤ በፌዴሬሽን 30,343,364 ካፒታል ማፍራት ተችሏል፡፡ የዕቅዱ አፈጻጸም ከ100% በላይ ነው፡፡ በዚህም የተሻለ አፈፃፀም ያስመዘገቡ ኦሮሚያ እና ሲዳማ ክልሎች ናቸዉ፡፡

የአገር ውስጥ የግብርና ምርት የግብይት ተሳትፎ እና ድርሻ ለማሳደግ በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 15 ከመቶ በ2013 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 20 በመቶ ለማድረስ ግብ የተጣለ ሲሆን ሙሉ በሙሉ ለማሳካት ተችሏል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራትን የውጭ ግብይት ድርሻ በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት በመጠን 5 ከመቶ ወደ 12 ከመቶ ለማድረስ ታቅድ 11 በመቶ ለማድረስ ተችሏል፡፡

በቅድመ እና ድህረ ምርት የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት የሚሰጡ ማሽነሪዎችን ቁጥር በ2012 ዓ.ም መጨረሻ በቆጠራ ከተደረሰበት 1,680 ወደ 1,780 ለማሳደግ በዕቅድ ተይዞ እየተሰራ ሲሆን የግብርና ቅድመ ምርት ሜካናይዜሽን አገልግሎት የሚሰጡ አዳዲስ ማሽኖችን 70 ታቅዶ፤ ትራክተር 15 መከስከሻ 10 ውሃ መሳቢያ ጄኔሬተር 826 ስንዴ መዝሪያ 12 በድምሩ 863 ሜካናይዜሽን አገልግሎት የሚሰጡ አዳዲስ ማሽኖችን በዓመቱ በማቅረብ ለአባሎቻቸዉ እና ለአካባቢዉ ማህበረሰብ አገልግሎት መስጠት ተችሏል:: አፈፃፀሙም ከዕቅዱ አንፃር ሲታይ  በጣም ከፍተኛ ነዉ ለዚህም እንደ ምክንያት መንግስት ለበጋ መስኖ በሰጠዉ ከፍተኛ ትኩረት በህብረት ስራ ማህበራቶች ተገዝተዉ እንዲቀርቡና አገልግሎት እንዲሰጡ በመመቻቸቱ ሲሆን የውሃ መሳቢያ ጄኔሬተር ሰፊዉን ድርሻ በመያዙ ነዉ በዚህም የተሻለ አፈፃፀም ያስመዘገቡ ኦሮሚያ፣ ደቡብ እና የአማራ ክልሎች አፈፃፀም ሪፖርት መሰረት ነዉ፡፡

የድህረ ምርት መካናይዜሽን አገልግሎት ለአባሎቻቸዉ እና በዙሪያቸዉ ለሚገኙ አርሶ አደሮች እና ለግብርናዉ ክፍለ ኢኮኖሚ የበኩላቸዉን ማበርከት እንዲችሉ 30 ታቅዶ 20 ኮምባይነር፣ 15 ትሬሸር 18 ስንዴ መዉቂያ 13 ቦቆሎ መፈልፈያ እና 3 የዘር ማበጠሪያ በድምሩ 69 የተለያዩ የግብርና ድህረ ምርት መካናይዜሽን ማሽነሪዎች ተገዝተው አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡

የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ቁጥር በ2012 ከተደረሰበት 951 በ2013 ዓ.ም መጨረሻ ወደ **1,026** ለማድረስ በዕቅድ የተያዘ ሲሆን በአፈጻጸም ደረጃ 1,699 (166%) ለማድረስ ተችሏል። በተጨማሪም ጥናት ተደርጎ አሶሳ ሁለገብ የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየን የዘይት ፋብሪካ ግንባታ እንዲጀምር ከልማት ባንክ ብድር ማግኘት እንዲችል አስፈላጊው ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል።

በፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰበሰበው የቁጠባ መጠን በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት ብር 20.5 ቢሊዮን በ2013 ዓ.ም መጨረሻ ወደ ብር 25.5 ቢሊዮን ለማድረስ ለመቆጠብ ታቅዶ ብር 5,184,340,617 (100%) በመሰብሰብ ከዕቅድ በላይ ማከናወን የተቻለ ሲሆን 3,683,566,316 በመሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ኅብረት ሥራ ማህበራት እና 1,490,872,969 በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየን ማሰባሰብ ተችሏል። የተሻለ አፈጻጸም ያላቸው አማራ እና ኦሮሚያ ክልሎች ናቸው።

## 3.7 ግብርና ትራንስፎርሜሽን

የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ በ2013 በጀት ዓመት በርካታ ተግባራትን ያከናወነ ሲሆን በተለይ በተመረጡ ዋና ዋና ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች የተከናወኑ ተግባራትና ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች እንደሚከተለው ቀርበዋል። ሪፖርቱ ከኤጀንሲው መሰረታዊ ተልዕኮዎች አንጻር በ3 ዋና ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን እነኚህም ምርትና ምርታማነትን የሚደግፉ ሥራዎች፣ የግብይት ሥራዎች እና የግብርና ኮሜርሻላይዜሽን ክለስተር (ACC) ሥራዎች ናቸው።

### 3.7.1 ምርትና ምርታማነትን የሚደግፉ ሥራዎች ቁልፍ ስኬቶች በተመለከተ

የቀጥታ የዘር ግብይት ፕሮጀክት ከአራት ክልሎች (ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች፣ እና ትግራይ) በቀጥታ ዘር ግብይት ስርዓት መስፋፋት ፕሮግራም 45 አዳዲስ ወረዳዎች ተመርጠዋል። በዚህም መሰረት የ2013 ዓ.ም የቀጥታ ዘር ግብይት ወረዳዎች ብዛት 366 ይደርሳል። በአራቱም ክልሎች የቀጥታ ዘር ግብይት ወኪሎች የብቃት ግምገማ እየተካሄደ ይገኛል። በኦሮሚያ ክልል ይህ ተግባር የተጠናቀቀ ሲሆን በአጠቃላይ 652 ወኪሎች ተገምግመዉ የብቃት ሰርትፍኬት አግኝተዋል።

የግብርና ግብዓትና አገልግሎት ፕሮጀክት 145 ማዕከላት ለ1.3 ሚሊዮን አ/አደሮች የተለያዩ ግብዓቶችንና አገልግሎቶችን በማቅረብ ከ500 ሚሊዮን ብር በላይ የሽያጭ ገቢ አግኝተዋል። በቅርቡ ተከፍተዉ ስራ ለጀመሩ 116 የግብርና ግብዓት አቅርቦትና አገልግሎት ማዕከላት ስለንግድ ሥራ አመራር ስልጠናዎች ተካሂደዋል።

የኅብረት ስራ ማሕበራት አቀፍ ዘር ብዜት ፕሮጀክት 12 ዩኒየኖች ዘር ለመሰብሰብና ለማዘጋጀት የሚያስችላቸውን ብድር አግኝተው ዘር መሰብሰብ ጀምረዋል። 12 ዩኒየኖች 80,000 ኩንታል

የተመሰከረለት ዘር ማምረት ችለዋል፤ 6 የሕብረት ስራ ማህበራት ዩኒየኖች ከክልል የምርምር ተቋማት ጋር በመተባበር 6000 ኩንታል መስራች ዘር ማምረት ችለዋል፡፡

የተቀናጀ ጥልቅ ያልሆነ የከርሰ ምድር ውሃ መስኖ ልማት ፕሮጀክት 21,804 ሄ/ር መሬት ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በሚያስገኙ አትክልት ሰብሎች (ሽንኩርት፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ቲማቲም፣ ድንች፣ ቃሪያ፣ ካሮት፣ ጥቅል ጎመንና ሌሎች የአትክልት ሰብሎች) በኦሮሚያ፣ አማራና ደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልሎች ተሸፍኗል፡፡

የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ማዕከላት የሙከራ ፕሮጀክት 11 ኮምባይነሮች እና 5 ትራክተሮች በኢት/ንግድ ባንክ፣ በኢትዮሊዝ እና በልማት ባንክ በኩል በሊዝ ፋይናንስ ለ5 ማዕከላት ተላልፈው ማሽኖቹ ወደ ስራ ተሰማርተዋል፡፡ በ6 ማዕከላት ከ9,000 ለሚበልጡ አርሶ አደሮች የአጨዳ እና የውቅያ፣ የመሬት ዝግጅት፣ በመስመር መዝራት እና የጸረ-አረም/ተባይ መድኃኒት ርጭት የሜካናይዜሽን አገልግሎቶች ተሰጥቷል፡፡

የኢትዮጵያ የአፈር ሃብት መረጃ ስርዓት ፕሮጀክት የአፋር ብሄራዊ ክልል የአፈር ለምነት ይዘትና የማዳበሪያ ዓይነት ምክረ ሀሳብን የያዘ መፅሐፈ ካርታ ተጠናቅቆ የክልሉ የግብርና ቢሮ ከፍተኛ አመራሮችና ባለሙያዎች በተገኙበት ርክክብ ተደርጓል፡፡ ከሁሉም የሐገሪቱ ክፍል የተሰበሰቡና የንጥረ ነገር ትንተና የተደረገላቸዉ የአፈር ናሙናዎችን 75 በመቶ ወደ አዲሱ ቤተ መዘክር ማዛወርና በትክክል የመመዝገብና የመደርደር ሥራ ተሰርቷል፡፡

### 3.7.2 የግብይት ሥራዎች ቁልፍ ስኬቶች

የግብርና ንግድ እና ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ከኦሮሚያ ክልል ጋር በመተባበር በተከናወኑ የገበያ ትስስር ሥራዎች የቢ.ቢ.ዜድ. ምግቦች ማምረቻ አ.ማ. ከተመረጡ ዩኒየኖች 35,500 ኩንታል አኩሪ አተር ለመግዛት ተስማምቷል፡፡ ኩዊት ላይቭስቶክ እና አግሪካልቸር ኃ/የተ/የግ/ማህበር በክብት እርባታና የኤክስፖርት ቄራ ላይ የ7 ሚሊዮን ዶላር ኢንቬስትመንት አድርጓል፡፡

የ8028 የአርሶ አደሮች ነፃ የድምፅ ቅብብሎሽ ምላሽ ፕሮጀክት በበጀት ዓመቱ የ11 የስራ እንቅስቃሴ በ8028 የአርሶ አደሮች የመረጃ መስመር በጥቅሉ ከ3.3 ሚሊዮን በላይ ጥሪዎችን ተስተናግደዋል፡፡ እንዲሁም 377,390 ያህል አዳዲስ ደዋዮች በስርአቱ ለመጠቀም ተመዝግበዋል፡፡ አይ.ቪ.አር እና ኤስ.ኤም.ኤስ (IVR/SMS) ስርአትን በመጠቀም የስንዴ ዋግ እና የበረሃ አንበጣ ክስተትን መለየት የሚያስችሉ የዳሰሳ ጥናት መጠይቆችን 454,892 ያህል ጊዜ ለልማት ሰራተኞች እና ለቀበሌ የግብርና ልማት ሰራተኞች (DAs) በመላክ መረጃ የመሰብሰብ እና ትንተና የመስራት ተግባር ተከናውኗል፡፡ ከተላኩት መጠይቆች መካከልም 79 በመቶው ለምላሽ ሰጪዎች መድረሱን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የአርሶ አደሮች ምርት ክላስተር /FPC/ ዲጂታይዜሽን ቅድመ ፓይለት ፕሮጀክት/ክሮፒን- CROPIN በአርሶ አደሮች ምርት ክላስተር ዲጂታይዜሽን መረጃ የመሰብሰቡ ሂደት የቀጠለ ሲሆን በዚህም መሰረት 1149 የሆኑ በአርሶ አደሮች ምርት ክላስተር ስር ያሉ የኩታ ገጠም መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የመረጃ

መሰብሰብያ ስርዓት አጠቃቀም ላይ የነበሩ ክፍተቶችን ለመሙላት የፕሮጀክት ኦፊሰሮች በአካል 38፣ በርቀት ደግሞ ከ100 በላይ ለሚሆኑ የልማት ጣቢያ ሰራተኞች እና የወረዳ ሰራተኞች የቴክኒክ እርዳታ እና የክትትል ስራ ተሰርቷል፡፡

## የግብርና ኢንቨስትመንት ካርታ ፕሮጀክት

በአማራ (51) ፣ በኦሮሚያ (41) እና በደቡብ ብ/ብ/ሕ (37) የተመዘገቡ በድምሩ 129 የግብርና ፕሮጀክቶች መረጃ፤ እንዲሁም፣ በፌደራል ደረጃ የተመዘገቡ 15 የግብርና ፕሮጀክቶች መረጃ፤ በጠቅላላው 134 የግብርና ፕሮጀክቶች መረጃ ወደ ግብርና ኢንቨስትመንት ማፕ /Agriculture Investment Mapping Tool, AIM Tool ተካቷል:

ሀገር አቀፍ የገበያ መረጃ ስርዓት ፕሮጀክት በተመረጡ የ157 የገበያ ቦታዎች 27,279 የሚሆኑ የተለያዩ የገበያ መረጃዎች በአምስት የሰብል ምርቶች (ጤፍ፣ ስንዴ፣ በቆሎ፣ በሎቄ እና ሰሊጥ) ተሰብስቧል፡፡ በሀገር ዓቀፍ ደረጃ ከ155,445 በላይ አዲስ ወደ መረጃ ስርዓቱ የተመዘገቡ ተጠቃሚዎች በ6077 የስልክ መስመር 952,519 ጥሪዎችን በመደወል ትክክለኛነታቸው የተረጋገጡ የገበያ መረጃዎችን አግኝተዋል፡፡

የገ/ቁ/ብ/ኅ/ሥ/ማ የዓቅም ግንባታ ፕሮጀክት የአሰልጣኞች ስልጠና በአቅም ዳሰሳና ክፍተት መለያ ዘዴን ለ174 የገ/ቁ/ብ/ህ/ሥ/ማህበራት ዩንየን ስራ አስኪያጆች፤ የብድርና የሂሳብ ባለሙያዎች እንዲሁም የክልልና የዞን ኅ/ሥራ ባለሙያዎች ተሰጥቷል፡፡

ለገ/ቁ/ብ/ህ/ሥ/ማህበራት የአቅም ክፍተትና ምዘና መለያ ዘዴ በመጠቀም ለ1019 ገ/ቁ/ብ/ህ/ሥ/ ማህበራት የአቅም ክፍተት የዳሰሳ ጥናት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

የግብርና ግብዓት የኩፖን ሽያጭ ሥርዓት ፕሮጀክት 6.3 ሚልየን አርሶአደሮች የግብዓት ኩፖን ሽያጭ ስርዓትን በመጠቀም 12.2 ሚልየን ኩንታል ማዳበሪያ፤ ምርጥ ዘር እና ኬሚካሎችን በ16.96 ቢልየን ብር ገብይተዋል፡፡ 459 ሺህ አርሶአደሮች 1.3 ቢልየን ብር የግብዓት ብድር አግኝተው 1.3 ሚልየን ኩንታል ማዳበሪያ፤ ምርጥ ዘር እና ኬሚካሎችን ግብዓት ገብይተዋል፡፡

## 3.7.3 የግብርና ኮሜርሻላይዜሽን ክለስተር (ACC) ሥራዎች ቁልፍ ስኬቶች

በአምስቱ ዋና ዋና ሰብሎች (ስንዴ፣በቆሎ፣ጤፍ፣ቢራ ገብስ እና ሰሊጥ) 1 ሚሊዮን ሄ/ር ማሳ በ1.7 ሚሊዮን የአርሶ አደር ምርት ክላስተር አርሶ አደሮች ተሸፍኗል፤ 440,700 ኩንታል ምርጥ ዘር እና 2.5 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ለአርሶ አደር ምርት ክለስተር አርሶ አደሮች ተሰራጭቶ ጥቅም ላይ ውሏል፤ የግብርና ግብዓት ብድር ተደራሽ የሆኑ የአርሶ አደር ምርት ክላስተሮች አጠቃላይ ብዛት 368,300 ሲሆን፤ በአርሶአደሮች ደረጃ ለምርጥ ዘር ተደራሽ የሆኑ 1.8 ሚሊዮን፣ ለማዳበሪያ ተደራሽ የሆኑ ደግሞ 3.3 ሚሊዮን ናቸው፡፡ ከዚህም ውስጥ በቅደም ተከተል 50%፣ 55.6% እና 45% የአርሶ አደር ምርት ክላስተር አርሶ አደሮች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የአርሶ አደር ምርት ክለስተር ሰብሎች ስንዴ፣በቆሎ፣የብቅል ገብስ፣ጤፍና ሰሊጥ 953,700 ሄክታር ማሳ ተሰብስቦ ግምቱ 36.4 ሚሊዮን ኩንታል የሚሆን ምርት ተገኝቷል፡፡ ከዚህም ምርት 9.3 ሚሊዮን ኩንታል ለገበያ ቀርቦ በ17.6 ቢሊዮን ብር ተሸጧል፡፡ ግብይት

ትስስር በአማራ፣ ኦሮሚያና ደቡብ ብ/ብ/ሕ እና ትግራይ ክልሎች የምርት ክለስተር አርሶ አደሮች 2.6 ሚሊዮን ኩንታል የስንዴ፣ በቆሎ፣ የብቅል ገብስ፣ ጤፍና ሰሊጥ ምርት ከገዥዎች ጋር በ4.4 ቢሊዮን ብር የኮንትራት ውል ተፈራርመዋል፡፡

### 3.7.4 የጥናት ሥራዎች ቁልፍ ስኬቶች

28 የጥናት ስራዎች የተከናወኑ ሲሆን ከነኚህም ውስጥ የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡- የሆርቲካልቸር የአርሶአደሮች ምርት ክላስተር/ኤፍ.ፒ.ሲ. ዲዛይን፤ በ4 ክልሎች የሚተገበር የእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮግራም ዲዛይን፣ በግብርና ልማት የሴቶች ተሳትፎን የማሳደግ ፕሮጀክት ዝግጅት፤ የ10 ዓመት የግ.ት.ኤ. ውጤቶች ጥናት፤ ከ10 ዓመት ዕቅድ ጋር የተገናዘበ የግብርና ትራንሰፎርሜሽን ኤጀንሲ አደረጃጀት ጥናት፤ የሶማሌ፣ አፋር፣ ጋምቤላ፣ ሀረሪ እና ቤንሻንጉል ክልሎች እንዲሁም የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የግብርና ልማት ስትራቴጂ፤ ከዋናው የኤሌክትሪክ ኃይል መረብ ትስስር ውጭ ላሉ አከባቢዎች መለስተኛ ከባቢያዊ የኃይል ምንጭን ለመስኖና ለሌሎች ግብርና ነክ ተግባራት ለማዋል የሚያስችል ስትራቴጂና የቢዝነስ ሞዴል ዝግጅት፤ አዲስ ግኝት /Innovation/ ማረጋገጫ ፕሮጀክት የማጠቃለያ ግምገማ ሪፖርት 100% ተጠናቋል፤ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ የአስር ዓመት ተፅእኖ /Impact/ ግምገማ ተጠናቋል፡፡

## 3.8 ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች

### 3.8.1 የገጠር ስራ ዕድል ፈጠራ

1,605,340 የስራ ፈላጊዎችን ለመመዝገብና ልያታ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 1,261,692 ሴት 522,770 በድምሩ 1,784,462 ልየታ የተካሄደ ሲሆን አፈፃፀሙም 111% ነው፡፡ በክልሎች ደረጃ ለተለየዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ማለትም የዩኒቨርሲቲና ኮሌጂ ምሩቃን እና ሌሎች ስራ ፈላጊ ዜጎችን ጨምሮ በቁጥር 3,890,919 ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ለ4,616,884 ህብረተሰብ ክፍሎች የግንዘቤ ማስጨበጫ ሥራ የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀመም 192% ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ ለ 951500 የስራ ፈላጊዎች የስራ እድል ለመፈጠርታቅዶ ለ 1,696,957(1,221,541 ወንድ ፣ 475,416 ሴት) (178%) የስራ እድል ለመፍጠር ተችሏል)

በአጠቃላይ ከተፈጠረው የስራ ዕድል በግብርና ዘርፍ በአጠቃላይ 1,015,050 ለወንድ 507525 ሴት 507525 የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ወንድ 607,535 ሴት 234,484 ድምር 842,019 የስራ እድል ለመፍጠር ታችሏል፣ አፈጻጸሙም 83 በመቶኛ ነው፡፡ በኢንዱስትሪ ዘርፍ በአጠቃላይ 249,975 ወንድ 124,987 ሴት 124,988 ለመፍጠር ታቅዶ ለወንድ 317,136 ለሴት 116,627 በድምር 433,764 የስራ እድል ልፈጠረላቸው ታችሏል፣አፈጻጸሙም 174 በመቶኛ ነው፡፡ በአገልግሎት ዘርፍ በአጠቃላይ 249,975

ወንድ 124,987 ሴት 124,988 ታቅዶ ለወንድ 296,870 ለሴት 124,304 ድምር 421,174 የስራ እድል ለመፍጠር ታችሏል፣ አፈጻጸሙም 168.5 በመቶኛ ነው፡፡

የገጠር ኢንተርኘራይዞች ድጋፍ ለማጎልበት የለማ መሬትና የሼድ አቅርቦት በተመለከተ በገጠር ለሚደራጁ ኢንተርኘራይዞች የመሬት አቅርቦት 134,284 ሄክታር መሬት ለመስጠት ታቅዶ 74,253 ሄክታር ማስተላለፍ ተችሏል ይህም በመቶኛ 55.3 ነው፤ 3,712 ሼዶች ለመስጠት ታቅዶ 2,396 ማስተላለፍ ተችሏል ይህም በመቶኛ 64.5 ነው፤ በአጠቃላይ ለ118,995 አንቃሳቃሾችና ለ5,562 ኢንተርፕራይዞች፣ ለ34,789 አንቃሳቃሾች ለማስተለላፍ ታችሏል፡፡

የብድር ስርጭትን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ 9,661,404,203 ብር፣ ለ137572 ኢንተርፕራይዞችና ለ1100576 አንቃሳቀሾች ለማሰራጨት ታቅዶ ከመደበኛ 206,847,060 ብር እና ከተዘዋዋሪ 984,547,299 ብር በአጠቃላይ 1,191,394,359ብር ለ22,599 ኢንተርፕራይዞችና ለ56,158 አንቃሳቀሾች ለማሰራጨት ታችሏል፡፡ የብድር ስርጭት አፈጻጸሙም 12.3 በመቶ ነው፡፡

ብድር መስመላስን በተመለከተ በ2013 እቅድ ውስጥ ባይኖርም ከክልሎች በአጠቃላይ 1,770,492,632 ብር የመደበኛ ብድር 1,201,772,844 ብር እና የተዘዋወሪ ብድር 568,719,788 ብር መስመላስ ተችሏል::

የኢንተርፕራይዞች የደረጀ ሽግግርን በተመለከተ በጥቃቅን ደረጀ 74,230፣ በአነስተኛ ደረጀ 7,424ና በመከካለኛ ደረጀ 743 በአጠቃላይ ለ82397 ኢንተርፕራይዞች የደረጀ ሽግግር ለማድረግ ታቅዶ በጥቃቅን ደረጀ ለ24,768፣ በአነስተኛ ደረጀ ለ5,034 እና በመከካለኛ ደረጀ ለ90 በአጠቃላይ ለ29892 ኢንተርፕራይዞች የደረጀ ሽግግር ማድረግ ታችሏል፡፡

### 3.8.2 የአካባቢና አየር ንብረት ለውጥ

ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታን ለማሳካት የሚያግዙ 4 የሀብት ማፈላለጊያ ፕሮፖዛሎችን ለማዘጋጀት ተቅዶ 4ቱም የሀብት ማፈላለግያ ፕሮፖዛሎች ተዘጋጅተዋል፡፡ በተገኘውም ገንዘብ 3 የአቅም ግንባታ ስልጠና መድረኮች እንዲዘጋጁ የተደረገ ሲሆን አፈፃፀሙ 100% ነው፡፡ ሶስት ፕሮጀክቶችን ዲዛይን ማድረግ የሚያስችሉ ርዕሶች (Titles) ተመርጠው ተቀባይነት በማግኘት በቀጣይ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡

ከPASDIP II ፕሮግራም ጋር የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መነሻ ሁኔታ እና የተጠቃሚዎች የተጋላጭነት ሀኔታ የዳሰሳ ጥናት (Base Line Assessement) ለማካሄድ ስልጠና ተሰጥቶ የመስክ ስራ ተሰርቷል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በመስክ ደረጃ የተሰበሰበውን መረጃ የማደራጀትና የመተንተን ስራ ተጠናቋል።

በሁሉም ክልሎች እየተተገበረ ያለውን የማጣጣሚያና የማስተሳሰሪያ ስራዎችን ትግበራ ለመከታተልና ለመደገፍ ታቅዶ ከሁሉም ክልሎች የተውጣጡ አመራሮችና ባላሙያዎች እና በፌደራል ደረጃ ያሉ ባለድርሻዎች በተገኙበት የእቅድ አፈፃፀም ግምገማ ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪም በመድረኩ ላይ የማጣጣሚያ እና የማስተሳሰሪያ ስራዎችን በተመለከተ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ የተሰራ ሲሆን በመድረኩ 43 አመራሮችና ባለሙያዎች (4 ሴት) ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ 4 ጊዜ በደቡብ፣ በጋምቤላ፣ ኦሮሚያና አማራ ክልሎች ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተደረገው የመስክ ድጋፍና ክትትል የፕሮጀክቶቹ ስኬትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ የተለዩ ተግዳሮቶችን የክልሉ አመራር አካላትን በማሳተፍ መፍትሄ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ለመንግስትና ለግል ግብርና ኢንቨስትመንት ልማት እና ፕሮጀክቶች የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት እንዲያረጋግጡ 1 ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች የሚገኙ በሆርቲካልቸር ለተሰማሩ ባለሃብቶች የክትትልና ድጋፍ ስራ ተሰርቷል፡፡

የአካባቢ የደህንነትና የአረንጓዴ ልማት ስራዎች በጥራት እንዲተገበሩ የአመራርና ፈጻሚ እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከትን ማሳደግ ይቻል ዘንድ ሁሉንም ክልሎች ያሳተፈ 5 መድረኮች ለማዘጋጀት ታቅዶ 4 ስልጠና መድረኮች የተዘጋጁ ሲሆን፤ አፈፃፀሙ 80% ነው፡፡ እቅዱ ሙሉ በሙሉ ያልተሳካው በኮቪድ 19 ምክንያት ነው፡፡ በመድረኮቹ የተሳተፉ ሰልጣኞች ቁጥር 121 (8 ሴት) ናቸው፡፡ ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በመተባበር በሱማሌ ክልል ሃሮሪስና ፊቅ ወረዳዎች አሳታፊ የተፋሰስና የተፈጥሮ ግጦሽ መሬት አያያዝ እና ለቆላማ አካባቢዎች የሚተገበሩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ዘዴዎች ላይ እንዲሁም ለጋምቤላ፣ አማራና ደቡብ ክልሎች ለሚገኙ የግብርና ልማት የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት ስራ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና በግብርና ኢንቨስትመንት ለተሰማሩ ባለሃብቶች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ የክህሎት ክፍተትን መሠረት በማድረግ ለ5 ባለሙያዎች ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ በእቅድ የተያዘ ሲሆን እስካሁን ድረስ ለ10 ባለሙያዎች ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በዚህም የእቅዱን 200% መፈፀም ተችሏል፡፡

ኃላፊነት የተሞላበት የግብርና ኢንቨስትመንት ዕውን ለማድረግ የሚያስችል የማህበራዊና አካባቢያዊ የስነ ምግባር ደንብ የአማርኛ ትርጉም ሰነድ በማሳተም ለ6 ክልሎች ለማሰራጨት በእቅድ ተያዘ ሲሆን አማርኛ ትርጉም የህትመት ስራው ተጠናቆ ለሲዳማ፣ ደቡብና አማራ ክልሎች የማሰራጨት ስራ ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪም ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተጣጣመ የግብርና ሥራዎችን (CSA Strategy) በማሳተም ለ10 ክልሎች ለማሰራጨት በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

### 3.8.3 የሴቶችና ወጣቶችን ተሳትፎ ማሳደግ

በፈፃሚና አስፈፃሚዎች ዙሪያ የሚስተዋሉ የአመለካከትና የክህሎት ችግሮችን ለመፍታት ያስችል ዘንድ በሥርዓተ-ፆታ ፅንሰ-ሃሳብ፣ በሴቶች ህፃናትና ወጣቶችን ማካተት፣ ሴቶችን ማብቃት፣ በምግብና ስርዓተ-

ምግብ፣ በወጣቶች ፓኬጅና ሌሎች ተያያዥ አርዕስቶች ዙሪያ ለ430 ሴቶችና ለ350 ወንዶች በድምሩ ለ780 የፌደራል፣ የክልል፣ የዞን፣ የወረዳ፣ የቀበሌ፣ ተጠሪ ተቋማት፣ የፕሮጀክት ፈፃሚዎችና ባለድርሻ አካላት ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ769 ሴቶችና ለ520 ወንዶች በድምሩ1289 ተሰጥቷል፡፡

በሚ/ር መ/ቤቱ የህፃናት ማቆያ ማዕከል (Childeren Care Center) ለማቋቋምና ወደ ተግባር ለማስገባት የሚያስችል የማስተባበር ስራ በመስራት በሚንስትር መ/ቤቱ ዉስጥ እየተገነባ ከሚገኘዉ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ጎን ለጎን የወጣዉን አዋጅ መሰረት በማድረግ ማዕከሉን ለማቋቋም በተደረገው ድጋፍ ስራው 40% እየተከናወነ ይገኛል፡፡ በተጠሪ ተቋማት 8 ለማቋቋም ታቅዶ 2 ተከናወኗል፡፡

የሚ/ር መ/ቤቱ የሴት ሠራተኞች ፎረምን የማጠናከር ስራ ተሰርቷል፤ በዚህም አጠቃላይ የአባላቱ ቁጥር 380 ሲሆን የአባላት ቁጠባ ብር 50,000 /ሃምሳ ሺህ ብር/ ማድረስ ተችሏል፡፡

በተፈጠረዉ ዓለም አቀፋዊና ሀገራዊ የኮሮና ቫይረስ ወረርሺኝ ሳቢያ በዋናነት ሴቶች፣ ህፃናት፣አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞችና ወጣቶች ተጋላጭና ተጎጂ እንደመሆናቸዉ በተቋሙ የሚገኙና የሚመለከታቸዉ አካላትን በማስተባበር ለኦሮሚያ፣ አማራና ደቡብ ክልሎች ከሁለት ሚሊየን ብር በላይ የሚያወጡ የአልባሳት ድጋፍ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ለሰዋሰዉ ገነት የአረጋዊያን፣ ሴቶችና ህፃናት የእርዳታ ድርጅት የአልባሳትና የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

በደቡብ ክልል ጉራጌ ዞን መስቃን ወረዳ በሴቶችና ወጣቶች የተገኙ ዉጤታማ ስራዎችን ለማስፋት ከተቋሙ፣ ከክልልና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን አሳታፊ ያደረገ የልምድ ልዉዉጥ መድረክ ተካሄዷል፡፡

በሴክተሩ በሚካሄዱ የልማት አቅጣጫዎች የሴቶች፣ ህፃናትና የወጣቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት በህገ-መንግስቱ የተሰጣቸዉ መብቶችና ሀገራችን ተግባራዊ ለማድረግ የተቀበለቻቸዉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ዕዉን ለማድረግ እየተከናወነ ባለው የግብርና ፖሊሲ ማሻሻያ ሂደት ተገቢውን ግብአት የመስጠት ስራ ተሰርቷል፡፡

ማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን እና የፆታዊ ጥቃት ቀን በተመለከተ የሚ/ር መ/ቤቱ የሚገኙ 34 ዳሬክቶሬቶች፣ 8 የተጠሪ ተቋማት እና 6 የክልል ፈፃሚዎችና አስፈፃሚዎችን አሳታፊ ያደረገ ሁለት የግንዛቤ ማስጨበጫና የምክክር መድረክ ተካሄዷል፡፡

የህፃናት ቀን በዓል አስመልክቶ በኦሮሚያ ክልል ለ50 ህፃናት የተለያዩ የትምህርት መርጃ ቁሳቁሶችን፣ የአልባሳት፣ ለምግብነትና ለንጽህና መስጫ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን በመግዛት ድጋፍ የተደረገ ሲሆን ለ12 ህፃናት በተቋሙ ሰራተኞች አማካይነት ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል፡፡

የክትትልና ድጋፍ ስራዎችን በተመለከተ በአምስት ክልሎች ለማድረግ ታቅዶ በ5 ክልሎች የሚገኙ የቀበሌ የሴት የልማት ቡድኖች፣ የወጣት አደረጃጀቶች፣ የኮሚቴና ሌሎች አደረጃጀቶች ላይ የክትትል፣ ድጋፍና የዳሰሳ ጥናት ስራ ተሰርቷል።

በወተት ሀብት ልማት ዙሪያ ለሴቶች ምቹ፣ ጊዜ፣ ጉልበት ቆጣቢ እና እሴት የሚጨምሩ የወተት ማለቢያና ማጣሪያ ቴክኖሎጂዎች ለአማራ፣ ኦሮሚያና ደቡብ ክልሎች ለእያንዳንዳቸዉ 70 በአጠቃላይ 280 ግብዓቶችን ድጋፍ ማድረግ ታቅዶ 210 (75%) ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፣

የሴቶችን ጊዜና ጉልበት ለመቆጠብ የሚያስችሉ 200 ግብዓቶችን ድጋፍ ማድረግ ታቅዶ 150 (75%) የጓሮ አትክልት ግብዓቶች ለኦሮሚያ፣ አማራና ደቡብ ክልሎች ድጋፍ ተደርጓል።

እንዲሁም ከዓሳ ሀብት ዳይሬክቶሬት ጋር በመቀናጀት በሀረሪ ክልልና በደቡብ ክልል አርባ ምንጭ ዙሪያ ለሚገኙ ሴቶች በዓሳ ሀብት ልማት ዙሪያ ለ80 ተሳታፊዎች ተግባር ተኮር ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ70 (88%) ታሳተፊዎች ተሰጥቷል።

በሀረሪ ክልል በዓሳ ልማት የተሰማሩ 30 የሴቶችና የወጣቶች የልማት ቡድኖች ዘመናዊ የሆነ የአሳ ማጥመጃ ቴክኖሎጂ የተሰራጨ ሲሆን በቴክኖሎጂው አጠቃቀም ከአሳ ልማት ዳይሬክቶሬት ጋር በመሆን ስልጠና ተሰጥቷል።

### 3.8.4 ምግብና ስርዓተ ምግብ

በምግብ ደህንነት፣ በተሰባጠረ አመራረት እና አመጋገብ ለስርዓተ ምግብ መሟላት ያለውን ድርሻ፣ በእሴት መጨመር (በቲማቲም እና በስራስር ሰብሎች)፣ በአይረንና ዚንክ የበለጸገ ቦሎቄ አጠቃቀም በተግባር በማስደገፍ ከመልካሳ ግብርና ምርምር ጋር በመተባበር በሚዲያ የማቅረብ ስራ ተሰርቷል፤ ኮቪድ19 በምግብ ስርዓት ላይ የሚያመጣውን ተጽእኖና የማቅለያ እርምጃዎች በተመለከተ ለሚዲያ ባለሙያዎች ገለጻ ተደርጓል፤ በሬድዮ የማስተላለፍ ስራ ተሰርቷል፤ በተጨማሪ በሄራልድ እና አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ እንዲወጣ ተደርጓል፤ እንዲሁም የኮሮና ወረርሽኝን መቋቋም እንዲቻል የማህበረሰቡ አመጋገብ ምን መሆን እንዳለበት ግንዛቤ ማስጨበጫ ፖስተሮችና ብሮሸሮች ከአላይቭ ኤንድ ትራይቭ እና ከጂአይዜድ ጋር በመተባበር አዘጋጅቶ በማሳተም ለ6 ክልሎች ተሰራጭቷል።

የአምስት አመቱን የስርዓተ-ምግብ ተኮር ግብርና ስትራቴጂ ትግበራ አፈጻጸምን አስመልክቶ በኦሮሚያ፣ ደቡብ እና አማራ ብሄራዊ ክልሎች የዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል።

የምግብ ስብጥር ዳሰሳ ጥናት በኦሮሚያ፣ አማራና ሶማሊ ክልሎች ተካሂዷል። የዳሰሳ ጥናቱን ውጤት ለማየት የትንተና ስራው በመካሄድ ላይ ይገኛል። በክልሎቹ መረጃ የማሰባሰብ ተግባር ከመካሄዱ በፊት

ከኦሮሚያ (35)፣ አማራ (20) እና ሶማሊ (6) ለተውጣጡ መረጃ ሰብሳቢ ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡ ፡

በተቋሙ በተለያዩ ክፍሎች የተዘጋጁ ፓኬጆች፣ ስትራቴጂዎችና ማኑዋሎች የስርዓተ ምግብ ተኮር ዓላማዎች እና ግቦችን አካቶ ሰነዶችን ለማዳበር ታቅዶ ሰነዶች ለማዳበር የሚረዳ የአሰራር መመሪያም የማዘጋጀት ተግባር የተከናወነ ሲሆን፤ የሆርቲካልቸር ዘርፍ የቀጣይ አስር ዓመታት ፍኖተ ካርታ ላይ የምግብና ስርዓት ምግብ ጉዳዮች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ሞዴል መንደር መፍጠር በሚል የስምንት ዓመት በሁለት ዙር የሚከናወን ፕሮጀክት ሰነድ ተዘጋጅቶ በፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር በኩል ለጃፓን መንግስት የማቅረብ ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህም መሰረት የፕሮጀክቱን ትግበራ ለማስጀመር የመጨረሻ ምዕራፍ ምክክር የተካሄደ ሲሆን ፕሮጀክቱ በሚተገርባቸው የኦሮሚያና አማራ ክልሎች ከJICA ከመጡ ባለሙያዎች ጋር በመቀናጀት የዳሰሳ ጥናት ተካሄዷል፡፡

የስርዓተ-ምግብ ተኮር ግብርና ሞዴል መንደር የመገንቢያ መስፈርት ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ፤ National Nutrition Demonstration Corners እና የስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ሞዴል መንደር (NSA-Model Village) ለመመስረት የሚያስችል ረቂቅ ማስፈፀሚያ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከግብርና አርብቶ አደር ቋሚ ከሚቴ አባላት ጋር በስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ላይ አውደ ጥናት ተካሂዷል (የተሳታፊዎች ብዛት 87)፡፡ ለተለያዩ አካላት በስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት በተደረገው ጥረት ለ62 የፌዴራልና በክልል ከፍተኛ አመራሮች በስርዓተ ምግብ ግብርና ላይ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ79 ተሳታፊዎች (6ሴቶች) ስልጠናው ተሰጥቷል፡፡

ለፌዴራልና ለክልል ከፍተኛ አመራሮች፣ የሰው ሀብት ልማት ዘርፎች፣ በተቋሙ ለሚገኙ የተለያዩ ስራ ክፍሎች እና ተጠሪ ተቋማት፣ ለህብረት ስራ ኤጀንሲና ለሚመለከታቸው የግብርናው ሴክተር ባለሙያዎች፣ ከሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ግብርና ሴክተር ለተውጣጡ ተሳታፊዎች፣ ከደቡብ እና ኦሮሚያ ክልሎች ለተውጣጡ የወረዳ ባለሙያዎች፣ በአማራ ክልል ለሚሰሩ የወረዳ የም/ስ/ም ባለሙያዎዎች፣ ለቆላማ አካባቢ የአርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር ክልሎች እና ለሚዲያ ባለሙያዎች ስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና እና የምግብ ደህንነት የስራቸው አካል ማድረግ የሚያስችል የትግበራ ሥልጠና እንዲሁም በክልል ለሚገኙ የስርዓተ ምግብ ባለሙያዎች በአድቮኬሲ እና ሎቢይንግ ላይ የክህሎት የአሰልጣኞች ሥልጠና ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በመተባበር ተሰጥቷል፤ (ተሳታፊዎች ወንድ 403 ሴት 103 ድምር 506)፡፡

ሁለተኛው ዙር ሀገራዊ የምግብ ስርዓት የምክክር መድረክ እንዲካሄድ የምግብና ስርዓተ ምግብ ማስተባበሪያ ፅ/ቤቱ እና የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው አካላት ትልቁን ድርሻ በመውሰድ የማስተባበር ተግባር ተከናውኗል፡፡ ሀገራዊ የምግብ ስርዓት ፍኖተ ካርታ የመጀመሪያ ረቂቅ ተዘጋጅቷል፡፡ በIntegrated Agricultural Development Program (IADP) ቀረፃ ላይ የምግብና ስርዓተ ምግብ ተግባራት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

ለምግብና ስርዓተ ምግብ ፖሊሲ ማስፈፀሚያ በተዘጋጀው ስትራቴጂ ውስጥ የግብርናው ዘርፍ ተግባራት ተካተው የወጪ ግምት ተሰርቶላቸዋል፡፡

በምግብ ንጥረ ነገር ይዘታቸው የበለጸጉ ምርቶች ላይ የምግብ ደህንነት ጥበቃ እና አግባባዊ እሴት ጭመራ ላይ የስልጠና ማኑዋል ተዘጋጅቷል፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የተለያዩ ስራ ክፍሎች ለሚከናወኑ ስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ተግባራት የአፈፃፀም አመላካቾች የስራ ክፍሎች ፎካሎች ባሉበት የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡

ከምግብና ስርዓተ ምግብ እና ከሆርቲካልቸር የስራ ክፍል ለተውጣጡ 24 ባለሙያዎች በE-learning እና በDigital Communication ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

የግብርና ሚኒስቴር ከሰላም ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በኦሮሚያ፣ ደቡብ፣ ሶማሊ፣ አፋር፣ ጋምቤላና ቤንሻንጉል አርብቶ እና ከፊል አርብቶ አደር ክልሎች ለሚተገብረው የLLRP ፕሮጀክት የስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና አቅም ግንባታ ስልጠና የሚሰጥበት የመጀመሪያ ረቂቅ የስልጠና ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡ የተዘጋጀውን የስልጠና ሰነድ ለማዳበር የሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲ፣ ምርምርና ክልል ግብርናና እንስሳት ሀብት ቢሮ አካላት የተገኙበት ሰነዱን የማዳበሪያ አውደ ጥናት ተካሄዷል፡፡ በተዘጋጀው የስልጠና ሰነድ ከኦሮሚያ፣ ደቡብ፣ ሶማሊ፣ አፋር፣ ጋምቤላና ቤንሻንጉል አርብቶ እና ከፊል አርብቶ አደር ክልሎች ለተውጣጡ 29 ባለሙያዎች (ሴት 7 ወንድ 22) በሰነዱ ላይ የሙከራ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በLLRP ፕሮጀክት በስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ሞዴል መንደር ለመፍጠር በአፋና ሶማሊ ክልሎች የዳሰሳ ጥናት ተካሄዷል፡፡ በዚህም መሰረት ከአፋር ክልል Kafare ቀበሌ እና ከሶማሊ ክልል Deghale ቀበሌ ሞዴል ስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና መንደር ለመፍጠር የተመረጡ ቀበሌዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም የLLRP ፕሮጀክት በሚሰራባቸው ክልሎችና ወረዳዎች የክትትልና ድጋፍ ስራ ተከናውኗል፡፡

በስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ምርጥ ተሞክሮዎችን የመለየት ተግባር በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች የተከናወነ ሲሆን ለህብረተሰቡ በሬና ቴሌቪዥን ጣቢያ መልዕክት ለማስተላለፍ ፕሮግራም ተዘጋጅቷል፡፡

ለሰቆጣ ቃል ኪዳን ትግበራ በ2012 የበጀት ክፍፍልና አጠቃቀም ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመቅረፍ እንዲቻል በ2013 በጀት ዓመት በሚኒስቴር መ/ቤቱ እቅድ ውስጥ አካቶ የማዘጋጀት ስራ ተሰርቶ

200,275,000 (ሁለት መቶ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰባ አምስት ሺህ ብር) የማስፈቀድ ስራ ተሰርቷል፡፡ ለሁለቱ የሰቆጣ ቃል ኪዳን ክልሎችም በታቀዱት ተግባራት መሰረት ለአማራ 144,198,000̃.00 እና ለትግራይ 28,038,500.00 በድምሩ 172,236,500̃.00 የተላከ ሲሆን ስለ አፈፃፀሙም ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡

በ2012 በጀት ዓመት ለአማራ እና ትግራይ ክልሎች በሰቆጣ ስምምነት ወረዳዎች ከተላከ ገንዘብ የተሰራጩ ግብአቶች (የወተት ፍየል፣ የእንቁላል ጣይ ዶሮዎች፣ የተለያዩ የጥራጥሬ ዘሮች፣ የጓሮ አትክልት ዘር) እንዲሁም የችግኝ ጣቢያ የማጠናከር፣ ግሪን ሀውስ ግንባታ፣ አነስተኛ መስኖ ግንባታ እና ሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ሰርቶ ማሳያ ማዕከል ግንባታ ስራዎች መከናወናቸውን በተካሄደ የመስክ የክትትልና ድጋፍ ስራ ወቅት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚገኙ የተለያዩ የስራ ክፍሎች በእቅዳቸው የም/ሥ/ምግብ ተግባራት እንዲያካትቱና እቅዳቸውንም እንዲያሳውቁ የክትትልና ድጋፍ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

ከህፃናት አድን ድርጅት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ለሚተገበረው "የስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና የአቅም ግንባታ ፕሮጀክት" የሰው ሀይል ለማሟላት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ፣ ሶሚሌና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልሎች የሰው ሀይል ቅጥር ተካሂዷል፡፡ የአማራ ክልል የሰው ሀይል ቅጥር በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ ከህፃናት አድን ድርጅት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን ለሚተገበረው "የስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና የአቅም ግንባታ ፕሮጀክት" በሚተገበርበት የምዕራብ አርሲ ዞን እና በዞኑ ባሉ ሁለት ወረዳዎች የክትትልና ድጋፍ ስራ ተከናውኗል፡፡

የSURE ፕሮግራም አፈፃፀም ላይ በኦሮሚያ፣ አማራና ደቡብ ክልሎች በሚገኙ 16 ወረዳዎችና 29 ቀበሌዎች የድጋፍና ክትትል ተግባር የተከናወነ ሲሆን፤ በመስክ ምልከታ ወቅት በተለዩ ውስንነቶች ላይ በየደረጃው ከቀበሌ እስከ ክልል የሚመለከታቸው ቢሮዎች የቃልና የፅሁፍ ግብረ መልስ ተሰጥቷል፡፡

በስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና እቅድ እና የእቅድ አፈጻጸም ላይ የግማሽ ዓመት የምክክርና የግምገማ አውደ ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት የፌዴራልና የክልል የስራ ሀላፊዎች| ዩኒቨርሲቲዎች እና የምርምር ተቋማት በተገኙበት የተካሄደ ሲሆን፤ ዓመታዊ የአፈፃፀም ግምገማ ለማካሄድ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡

የስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርናና ትግበራት እና ቴክኖሎጂዎች በግብርና ምርምር ማዕከላት እና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ልዩ ትኩረት አግኝተው በስፋት እንዲተዋወቁ ለማድረግ እንዲቻል በማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ በተካሄደው የግማሽ ዓመት የዕቅድ አፈጻፈም ግምገማ ላይ ዩኒቨርሲቲዎች እና የግብርና ምርምር ተቋማት ተሞክሮዋቸውን እንዲያቀርቡና ልምድ እንዲወሰድበት ተደርጓል፡፡

### 3.8.5 የኤች አይቪ ኤድስ

የተለያዩ የፀረ-ኤችአይቪ መልእክት የያዙ ጽሁፎች በኮርነር ዲስፕሌይ 4 ጊዜ ለማስተላለፍ ታቅዶ 3 ጊዜ ተላልፏል፡፡ 2215 የኤች አይቪና የአባላዘር በሽታ መልእክቶችን የያዘ ብሮሸር ለማሳተም ታቅዶ 2215 ብሮሸር ታትሞ ለተቋሙ ሰራተኞች ለተጠሪ ተቋማትና ለክልሎች ተሰራጭቷል፡፡ 1000 የኤች አይቪ መልእክቶችን የያዘ ፖስተር ለማሳተም ታቅዶ 1008 ፖስተር ታትሞ ለተጠሪ ተቋማትና ለክልሎች ተሰራጭቷል፡፡ 12 የኤች አይቪና የዘንድሮውን አለም አቀፍ የኤድስ ቀን መሪ ቃል የያዘ ባነር ታትሞ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ የአለም ኤድስ ቀን ህዳር 22 2013 ዓ.ም የተለያዩ አስተማሪ ፕሮግራሞችን በማቅረብና የህትመት ውጤቶችን በማሰራጨት 31 ሴቶችና 20 ወንድ በድምሩ 51 የተቋሙ ሰራተኞችና የህጻናቱ አሳዳጊዎች በተገኙበት በደመቀ ሁኔታ ተከብሮ ውሏል፡፡

ለግብርና ተጠሪ ለሆኑ ተቋማት፣ ለግብርና ኮሌጆች፣ ለግብርና ምርምር ማእከላትና ከትግራይ ክልል በስተቀር ከሁሉም ክልሎች ለተውጣጡ 19 የኤችአይቪ ኤድስ ፎካል ፐርሰኖች የኤች አይቪ ኤድስ ሜኒስትሪሚንግ፣ የህይወት ክህሎትና ምግብና ስርዓተ ምግብን በተመለከተ የ3 ቀን ስልጠና በሀዋሳ ከተማ ተሰጥቷል::

በተቋማችን ሠራተኞች በተቋቋመው የኤድስ ፈንድ ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸው 11 ሠራተኞች እና ወላጆቻቸውን በኤድስ ምክንያት ያጡ 7 ህጻናት በዚህ **130,800.00 ብር ከኤድስ ፈንድ** ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡ ለ7 ቱ ህጻናት በአመቱ መጀመሪያ ለእያንዳንዳቸው 1 የደብተር መያዣ ቦርሳ| አንድ ደርዘን ደብተር| 50 እስክሪፕቶ| 10 እርሳስ| 5 ላፒስ እና 5 መቅረጫ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡

5 ይበልጥ ስደተኛ ተቀባይ ክልሎችን ድጋፋዊ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ አሶሳ፣ ጋምቤላ፣ አፋር፣ አማራ እና ሶማሌ ክልል ግብርና ቢሮዎች በመገኘት በኤች አይቪ ሜኒስትሪሚንግና በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ዙሪያ ከአመራሩና ከፎካል ፐርሰኖች ጋር በጋራ በመሆን በጥንካሬዎችና በድክመቶች ላይ በመወያየትና ቀጣይ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ለተቋሙ ተጠሪ የሆኑ 9 ተቋማትን ድጋፋዊ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ ለ7 ተቋማት ኤች አይቪን ሜኒስትሪም እንዲደርጉ፣ የኮቪድ 19 ወረርሽኝን እንዲከላከሉ በተለይም ኤድስ ፈንድ እንዲያደራጁና ቫይረሱ በደማቸው ለሚገኝ ሰራተኞች ድጋፍ እንዲያደርጉ በመወያየትና ቀጣይ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መከላከያና መቆጣጠሪያ ኢንስቲቲዩት ሀላፊዎችና ሰራተኞች እንዲሁም በስሩ ለሚገኙ የማእከሉ ዳይሬክተሮች ከኢንስቲቲዩቱ ጋር በጋራ በመሆን በኤድስ ፈንድ አደረጃጀትና አላማ እና በምግብና ስርዓተ ምግብ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በመስጠት ሰራተኞች ኤድስ ፈንድ እንዲመሰርቱ ተደርጓል፡፡

ለግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ ለሆኑ 5 የግብርና ኮሌጆች ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ ለ4 ኮሌጆች (አርዳይታ፣ አላጌ፣ ሚዛን እና አጋርፋ) የኤች አይቪ ሜኒስትሪሚንግ ስራን በተመለከተ እና የኮቪድ 19 ወረረሽኝን እንዲከላከሉ በተለይም ኤድስ ፈንድ እንዲያደራጁና ቫይረሱ በደማቸው ለሚገኝ ሰራተኞች ድጋፍ እንዲያደርጉ በመወያየትና ቀጣይ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ለ9 ትልልቅ የአበባ ልማት እርሻዎች ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ ለ7 እርሻዎች የኤች አይቪ ሜኒስትሪሚንግ እና የኮቪድ 19 ወረረሽኝን እንዲከላከሉ በተለይም ኤድስ ፈንድ እንዲያደራጁና ቫይረሱ በደማቸው ለሚገኝ ሰራተኞች ድጋፍ እንዲያደርጉ በመወያየትና ቀጣይ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

## 4. የፕሮግራም በጀት

የፋይናንስ አጠቃቀም በሚመለከት በ7 ፕሮግራሞች በ2013 በጀት ዓመት በመደበኛ 1.12 ቢሊየን ብር ታቅዶ 965.56 ሚሊየን ብር (83.99%) ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን የካፒታል በጀት ደግሞ 12. ቢሊየን ብር በዕቅድ ተይዞ 19.59 ቢሊየን ብር (163.16%) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በአጠቃላይ በመደበኛና በካፒታል 13.16 ቢሊየን ብር በዕቅድ ተይዞ 20.56 ቢሊየን ብር (156.25%) ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ የበጀት አጠቃቀሙ ከዕቅድ በላይ የሆነበት ምክንያት የልማታዊ ሴፍቲኔት አጠቃቀም ከታቀደው በላይ ከዕርዳታ የበጀት ምንጭ ጥቅም ላይ ስለዋለ ነው፡፡

| ተ.ቁ | የፕሮግራሙ ስም- | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% |
|---|---|---|---|---|
| 1 | **ስራ አመራርና አስተዳደር** | **284.77** | **246.85** | **86.68** |
| | መደበኛ | 269.77 | 246.85 | 91.50 |
| | ካፒታል | 15.00 | 37.15 | 247.67 |
| 2 | **የእርሻ ልማት ፕሮግራም** | **1,468.84** | **1,957.16** | **133.25** |
| | መደበኛ | 173.62 | **196.27** | 113.05 |
| | ካፒታል | 1,295.22 | 1760.89 | 135.95 |
| 3 | **የተፈጥሮ ሃብትና ምግብ ዋስትና ልማት ፕሮግራም** | **9,080.33** | **16,452.00** | **181.18** |
| | መደበኛ | 43.96 | 33.44 | 76.07 |
| | ካፒታል | 9,036.37 | 16,418.56 | 181.69 |
| 4 | **የግ/ቴ/ሙ/ት/ስልጠና ፕሮግራም** | **519.37** | **369.42** | **71.13** |
| | መደበኛ | 496.65 | **359.28** | 72.34 |
| | ካፒታል | 22.72 | 10.14 | 44.63 |
| 5 | **የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ልማት ፕሮግራም** | **1,647.82** | **1,060.15** | **64.34** |
| | መደበኛ | 64.09 | 62.72 | 97.86 |
| | ካፒታል | 1,583.73 | 997.43 | 62.98 |
| 6 | **የእንስሳትና ዓሣ ግብዓትና ግብይት ፕሮግራም** | **12.8** | **11** | **85.94** |
| | መደበኛ | 12.8 | 11.00 | 85.94 |
| | ካፒታል | | | |
| 7 | **የእንስሳትና ዓሣ ጤና፣ ግብዓትና ምርት ጥራት ቁጥጥር ፕሮግራም** | **143.55** | **424.43** | **295.67** |
| | መደበኛ | 88.67 | 56.00 | 63.16 |
| | ካፒታል | 54.88 | 368.43 | 671.34 |
| | **አጠቃላይ አጠቃቀም** | **13,157.48** | **20,558.16** | **156.25** |
| | **መደበኛ** | **1,149.56** | **965.56** | **83.99** |
| | **ካፒታል** | **12,007.92** | **19,592.60** | **163.16** |

## 5. የኦዲት ግኝት

የተሰብሳቢ ሂሳብ ማስተካከልን በተመለከተ በ2011 በጀት አመት የመ/ቤቱ ተሰብሳቢ ሂሳቦች የተወራረዱ መሆኑ ሲጣራ ያልተወራረደና ማስተካከያ ስራ የሚያስፈልገው በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ ብር 28,030,421.65 ነው፡፡ ይህ ተሰብሳቢ ሂሳቡ ለረጅም አመታት ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ሆኖ እየተንከባለለ የመጣ ሲሆን በየጊዜው በተወሰዱ ተከታተይ እርምጃዎችና ክትትል በ2012 በጀት ዓመት ማስረጃ የቀረበላቸውና የተወራረዱ ብር 9,306,301.31 **ሲሆን** በየበጀት አመቱ ከወጪ ቀሪ ሆኖ ከሚንከባለለው ተሰብሳቢ ሂሳብ ዝርዝር የማጣራት ስራ ተሰርቶ በህግ አግባብ መታየት የሚገባቸውና ለህግ ጉዳዮች የቀረበ ብር 3,470,501.67፣ **በሂሳብ መዝገብ** መሰረዝ የሚገባቸውን በመለየት ከአስተያየት የቀረበ ብር 10,086,329.57 **ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ** ከንግድና ኢንዱስተሪ ሚኒስቴር ማስረጃ ሊቀርብለት ያልቻለ ተለይቷል.፣መስረጃ ያልተሟላለቸው፣ እንዲሁም ለተለያዩ ጉዳዮች በቅድሚያ የተከፈሉና ማስረጃ ሊቀርብባቸው የሚገቡ ሂሳቦችን አስፋላጊው ክትትል እየተደረገበት ሲሆን ሪፖርት ለማድረግ አዲስ የመጣው ሶፍትዌር (IFMIS) ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ባለመሆኑ የተደረጉ ለውጦችን ማሳየት አልተቻለም ወደፊት ሁኔታዎች ሲስተካከሉ በሪፖርታችን ውስጥ ተካቶ የሚቀርብ ይሆናል፡፡

ተከፋይ ሂሳብ ለበርካታ ዓመታት ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ሆኖ በምዝገባ በ2011 በጀት አመት ከተመለከተው በ2011 በጀት ዓመት ክፍያ የተፈፀመለትንና የሂሳብ ምዝገባ ማስተካከያ ከተሰራለት በኂላ በኦዲት ግኝት መሰረት ወደ 2012 በጀት ዓመት የዞረ **ብር** 9,776,587.34 ነው ፡፡ የተከፋይ ሂሳቡ ለረጅም አመታት ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ሆኖ እየተንከባለለ የመጣ ሲሆን በየጊዜው በተወሰዱ ተከታተይ እርምጃዎችና የማጣራት ስራ ለገቢዎች ሚንስቴር ክፍያው የተፈፀመ በገቢግብር ከተመለከተው ሚዛን ብር 556,496.83፣በተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገበው **ብር** 3,361,562.28 ፣ ከሂሳብ መዝገብ እንዲሰረዝ ብር 4,157,031.96 ለገንዘብ ሚንስቴር በደብዳቤ ተልኮ የነበረ ሲሆን የገንዘብ ሚ/ርም ከሂሳብ መደብ እንዲሰረዝ ውሳኔ ጠሰተበት በመሆኑ ለምዝገባ ላልፋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በበጀት ዓመቱ የተወራረዱ ሂሳቦች እንዳሉ የሚታወቅ ሲሆን በመ/ቤታችን የተቀናጃ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት /IFMIS/ ተግባራዊ የተደረገው በያዝነው በጀት ዓመት በመሆኑ 2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ተጠቃሎ ሲዘጋ የተደረገው ለውጥ በቀጣይ ሪፖርት የሚቀርብ ይሆናል ፡፡

## 6. ተቋማዊ ለውጥና የአገልግሎት አሰጣጥ

የሚኒስቴር መ/ቤቱን አደረጃጀት ለማሻሻል የተጀመረው የሰው ኃይል የሪፎርም ስራ ተጠናቆ የየሥራ መደቡ የሥራ መዘርዝር ተዘጋጅቷል፡፡ አደረጃጀቱ እንደጸደቀ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡ የፖሊሲ ሪፎርም የማሻሻያ ሥራ የፖሊሲ አቅጣጫዎቸ ተዘጋጅቶ ለከፍተኛ አመራ ቀርቦና በአስተያየት ዳብሮ ለማፀደቅ ለበላይ አካል ቀርቧል፡፡ በተዘጋጀው ረቂቅ መሰረትም የተለያየ ሙያ ያላቸው ግብረ ሃይሎች ተቋቁሞ ሲስተሚክ ኢንተርቬንሽን ፕላን ተዘጋጅቶ ፈፃሚ አካል ተለይቶ ወደ ተግባር ለመግበት በ2014 በጀት ዓመት መነሻ እቅድ ውስጥ ተካቶ እንዲታቀድ ተደርጓል፡፡ የስራ አካባቢን ምቹ ከማድረግ አኳያ አንድ ህንፃ የማሻሻያ ስራው ተጠናቆ ሥራ የጀመረ ሲሆን ሁለተኛው ሕንጻ በመጠናቀቅ ላይ ሲገኝ የቤተመጽሃፈት ግንባታ ከ45 በመቶ በላይ እንሁም የአዳራሽ ግንባታ ከ70 በመቶ በላይ ሲጠናቀቅ የግቢ አስፋልት ስራ ተጠናቆ ግሪኒንግ ብቻ ይቀራል፡፡

የግብርናና መረጃ ዲጂታላይዝ ከማድረግ አኳያ የግብርና አስተዳደራዊ መረጃን ለማዘመን በየክልሉ ለተመረጡ 12 የሙከራ ትግበራ ወረዳዎች ሶፍትዌር የተጫነባቸው 1,984 ታብሌቶች በመጠቀም በመረጃ አስተዳደር ስርዓቱ ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ የሙከራ ትግበራውን ለማስፋት ይቻል ዘንድ ለክልል ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና እንዲሰጥ ከተደረገ በኂላ 32,947 ታብሌቶች ለየክልሎች እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡ ለ11 የክልል ኃላፊዎች እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው 57 የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት የትውውቅ ስልጠና፣ ለ48 የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጅ እና የዕቅድ ዝግጅት ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና እና 260 የቀበሌ ልማት ጣቢያ ሰራተኞች ስልጠና እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ በትግበራ ሙከራ ወረዳዎች የተጀመረው ስልጠና እንደተጠናቀቀ የመረጃ ማስገባት ስራው የሚጀመር ይሆናል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በተበታተነ ሁኔታ የነበረውን የቃሊቲ መጋዘንን በግቢው ውስጥ ተበታትነው ሳር የበቀለባቸውን መሳሪያዎችና መኪኖች በማጽዳትና በመለየት ለተጠቃሚዎች የማሰራጨትና ለማስወገድ የማዘጋጀት ሥራ ተሰርቷል፡፡

በህግ ማዕቀፍ ማሻሻያ ላይ በፓርላማ ቋሚ ኮሚቴ በተሰጠው ግብረ-መልስ መሰረት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ  ረቂቅ ለሚ/ሮች ምክር ቤት ቀርቦ እየታየ ይገኛል፡፡ የዘር አዋጅ የማሻሻል ስራ እና የእጽዋት ዘር አዳቃዮች መብት ደንብ ተዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ተልኳል፡፡ የማዳበሪያ ማምረት፣ አያያዝ፣ ንግድና ስርጭት ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚ/ሮች ምክር ቤት ተልኮ እየታየ ይገኛል፣ የህብረት ሥራ ፖሊሲና ስትራቴጂ በኤጀንሲው የተዘጋጀ ሲሆን ከግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ ማሻሻያ ጋር ተያይዞ የሚጸድቅ ሲሆን የ15 ዓመት የህብረት ስራ ልማት ፍኖ ካርታም ከፖሊሲው መጽድቅ በኃላ የሚፀድቅ ነው፤ የግብርና ሜካናይዜሽን አገራዊ ፖሊሲ ሰነድ ተዘጅቷል፣ የሚቋቋሙ የግብርና ሜካናይዜሽን የአገልግሎት መስጫ ማእከላትን ለማስተዳደር የሚያስችል ቢዝነስ ሞዴል፣ መተዳደሪያ፣ ደንብና፣ መመሪያ በማዘጋጀት በማጸደቅ ሁለት ማእከላትን ወደ ስራ ማስገባት ተችሏል፡፡

የመ/ቤቱን የተዘበራረቀ የቢሮ አቀማመጥ የሚያመጣውን የመጓጓዝ የሀብት ብክነት ለማስቀረትና ለቀልጣፋ አገልግሎት አስጣጥ እንዲያመች ለማድረግ ለረዥም አመታት ተከማችተው የነበሩትን ንብረቶች የመለየት ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

በቃሊቲና በሳሪስ የሚገኙ ጋራዥ እና መጋዘኖች (ኮንቲነሮች) ሰፊ የሆነ የክምችት ብክነት (መለዋወጫ፣ ሰነድ፣ ግብዓቶች፣ የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶች) ፤በመለየት የማስወገድ ሥራዎች ተከናውነዋል፣ እየተከናወኑም ይገኛሉ፡፡

በዋናው መ/ቤት እና በሳሪስ መጋዘን መወገድ ያለባቸው ያረጁ ንብረቶች በማስወገድ ግቢው ሳቢ እና ምቹ እንዲሆን ከምንም ጊዜ በላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በዚሁም መሰረት ለመ/ቤቱ አገልግሎት የማይውሉትን ለረዥም አመታት ሳያገለግሉ የቆዩትን ንብረቶች እስከወረዳ ድረስ በስጦታ የማስወገድ ስራ ተሰርቷል፡፡ በግቢው ውስጥ በዘፈቀደ ያለስራ የቆሙ መኪኖች ቦታ ቆጣቢ በሆነ፣ ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ እንዲቆሙ በማድረግ የመኪኖቹን ታሪክ በተቋሙ የጋራዥ ባለሙያዎች እንዲጠኑ ተደርጓል፡፡

## 7. ልዩ ድጋፍ ክልሎች የተከናወኑ ተግባራት

በአገሪቱ ባሉ ክልሎች መሃል ያለውን ያልተመጣጠነ ልማት በአንፃራዊነት ለማቀራረብ ታዳጊ ክልሎችንና የአርብቶ አደር አካባቢዎችን የልማቱ ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግ በፌደራል መንግስት በኩል ላለፉት በርካታ ዓመታት ድጋፍ ሲደረግ መቆየቱ ይታወሳል፡፡

በዚሁ መሰረት ውሃን መሰረት ያደረገና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የመንደር ማሰባሰብን አቅጣጫ የተከተለ ልዩ ድጋፍ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ የዚህ ድጋፍ ዋና ትኩረት የክልሎችን የመፈፀምና ማስፈፀም አቅም ማጎልበት ሆኖ በየዘርፉ ተከታታይና ቋሚ ድጋፍ ሲሰጥ ቆይቷል፡፡

ይሁንና እስካሁን በርካታ ውጤት የተመዘገበ ቢሆንም ችግሩን በማቃለል ተመጣጣኝ ልማት ለማምጣት ባለመቻሉ አሁንም ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅ ሆኖ ይገኛል፡፡ በዚህ በያዝነው ዓመትም የአንበጣ ወረርሽኝና የኮሮና ቫይረስ ስርጭት ተጨምሮ የስራ እንቅስቃሴውን አዳጋች ቢያደርገውም በተቻለ መጠን በመንቀሳቀስ በያዝነው 2013 ዓ.ም የተደረገውን ድጋፍ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎች ማስተባበሪያ የተከናወኑ ተግባራት፡-** የአራቱን ታዳጊ ክልሎችና የኦሮሚያና የደቡብ አርብቶ አደሮች አካባቢን በግብርና ልማቱ ላይ ያላቸውን የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ለማጎልበት ባለሙያ በክልሎቹ በመመደብ ሦሥት ዙር ድጋፍ ለመስጠት ታቅዶ የነበረ ቢሆንም የወቅቱ ችግር በሆነው የኮቪድ 19 ቫይረስ ስርጭት እና በአንዳንድ አካባቢዎች ባለው የጸጥታ ችግር የተነሳ ለሁለት ዙር ድጋፍ (67%) መስጠት ተችሏል፡፡

በፌደራል የልዩ ድጋፍ ቦርድ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት የ4ቱ ልዩ ድጋፍ ክልሎችና የኦሮሚያና ደቡብ አርብቶ አደር አካባቢዎች እንዲሁም በአማራ ክልል ዋግህምራ ብሄረሰብ ዞን የ3 ዓመት /2014-2017/ የመ/ቤታችን የድጋፍ እቅድ ከክልሎቹ ጋር በመግባባት የመጀመሪያ ድራፍት ተዘጋጅቶ ለሰላም ሚኒስቴር ተልኳል፡፡

በፌደራል የልዩ ድጋፍ ቴክኒክ ኮሚቴ የልዩ ድጋፍ ስራ አፈፃጸም በመስክ በመገኘት የተቀናጀ ድጋፋዊ ሱፐርቪዥን ስራ አንድ ጊዜ ተከናውኗል፡፡ በመስሪያ ቤታችን ፈፃሚ ዳይሬክቶሬቶች የሚሰጠውን የልዩ ድጋፍ ስራ ከዕቅድ ዝግጅት ጀምሮ እስከ አፈፃፀም ሂደት የማስተባበርና የመከታተል ስራ ተከናውኗል፡፡
በሰላም ሚኒስቴር በሚመራው የቆላማ አካባቢዎች የኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት (LLRP) በኩል በግብርና ሴክተር የሚካሄደውን የድጋፍ ስራ በማቀድና የሚያስፈልገውን በጀት በማስመደብ እንቅስቃሴው ተጀምሯል፡፡ በዚሁ መሰረት 41 ሚሊየን ብር የተመደበ ሲሆን የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛል፡፡

## 8. ለክልሎች የተሰጠ አቅም ግንባታ

የግብርናን ሴክተር የ10 ዓመት መሪ እቅድ በተሳካ ሁኔታ ለመተግበር በበጀት ዓመቱ የክልሎችን የክትትልና ግምገማ አቅም ለመሳደግ ከልማት አጋሮች በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በእቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ እንዲሁም በፕሮጀክት አስተዳደር ለ80 ባለሙያዎች ሥልጠና ለማስጠት ታቅዶ ለ111 ባለሙያዎች (12% ሴቶች) የ10 ቀን ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ በተለያዩ የትኩረት መስኮች በተለዩ ክፍተቶች የቴክኒክ ስልጠናዎች የአሰልጣኞች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ የግብርና አስተዳደራዊ መረጃ ለማዘመን 34931 ታብለቶች ለክልሎች ተደልድሎ በመሰረጨት ላይ ሲገኝ ወደ ተግባርም ለማስገባት ለ60 ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ሥልጠና እና ለ260 የዞን የፓይለት ወረዳና  የልማት ጣቢያ ሰራተኞች  ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
በበጀት ዓመቱ የተከሰተውን የበረሃ አንበጣ ለመከላከል በተከሰተባቸው ክልሎች ባለሙያ በማሰማራት የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ክልሎች ኮቪድ 19 የሚያሳደርውን ተጽእኖ ለመቋቋም እንዲችሉ ከፕሮጀክቶች በጀት በማስመደብ ለሁሉም ክልሎች የሳኒተይዝርና የማስክ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ክልሎችን በፋይናንስ ከመደገፍ አኳያ ለአረንጓዴ አሻራ የችግኝ ተከላ ሥራ ማሳለጪያ 170,000,000 ብር ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለሁሉም ክልሎች ተፈቅዶ 160,000,000 ብር ቀርቧል፡፡ ከዚህ ዉስጥ 149,265,101.36 ብር ለክልሎች ተልኮ ለተላከለት ዓላማ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ሥር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ላለባቸው ክልሎች፣ የአነስተኛ አርሶ አደሮች መስኖ ልማት ለሚካሄድባቸው ክልሎች እንዲሁም ለተፋሰስ ልማት ሥራ፣ በፕሮጀክቶች በታቀደው መሰረት ፋይናንስ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

## 9. የዋና ዋና ፕሮጀክቶች አፈፃፀም

### 9.1 የግብርና እድገት ፕሮግራም

የግብርና እድገት ፕሮግራም በግብርናዉ ክፍለ ኢኮኖሚ የሚታየዉን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ለመቅረፍና ምርታማነትን ለማሳደግ እና ገበያ ተኮር ለማድረግ ታስቦ ከዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር ተሳስሮ የተዘጋጀና ይህንንም ግብ ለማሳካት በሚያስችል መልኩ የተቀረፀ መንግስታዊ ፕሮግራም ነዉ፡፡ ፕሮግራሙ በስምንት ክልሎች እና በአንድ የከተማ አስተዳደር (ማለትም፤ በኦሮሚያ፤ በአማራ፣ በደቡብ ፤በትግራይ፣ በሲዳማ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላ እና በሀረሪ ክልሎች እንዲሁም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር) በሚገኙና በተመረጡ 181 ወረዳዎች እና 4,181 ቀበሌዎች ዉስጥ የሚንቀሳቀስ ነዉ፡፡ በፕሮግራሙ ዘመን በድምሩ 3.7 ሚሊዮን አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ የሚጠበቅ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1.6 ሚሊዮን የሚሆኑ አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶአደሮች የፕሮግራሙ ቀጥተኛ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

በበጀት ዓመቱ በግብርና እድገት ፕሮግራም ከተከናወኑ ተግባራት መካከል ዋና ዋናዎቹ ከዚህ እንደሚከተለዉ በየስራ ክፍሎች በአጭሩ ቀርቧል፡፡

**የኤክስቴንሽን አገልግሎትን ተደራሽነት ለማሳደግ** 12 የአርሶ አደር ማሰልጠና ማዕከላትን ለማጠናከር ታቅዶ (83%) የአርሶአደር ማሰልጠኛ ጣቢያዎችን የማጠናከር የ4,125 ሰርቶ ማሳያዎችን የመደገፍ ፤ አንድ የንግስት ንብ ማራቢያ ና ማሰልጠኛ ማእከል ግንባታን የመደገፍ፤ አንድ የአሳ ጫጩት ማስፈልፈያ ማዕከልን በቁሳቁስ የማጠናከር፤ 12(67%) የአትክልትና ፍራፍሬ ችግኝ ጣቢያዎችን የማጠናከር፤ 4 የአፈር ለምነት ምርመራ ተቋሞችን በቁሳቁስ የማጠናከር ስራን መደገፍ ተችሏል፡፡

**ቴክኖሎጅ ማፍለቅና ማላመድ ተግባራትን** በተመለከተ 10 ከምርምር የወጡ የሰብል ቴክኖሎጂዎችን የማላመድ ስራንና 9 አዳዲስ የእንስሳት ቴክኖሎጂዎችን (100%) በድምሩ 19 ቴክኖሎጂዎችን (100%) የማላመድና ማፍለቅ እንዲሁም 1,754 ኩ/ል የሰብል ቅድመ መስራች ዘር የማባዛት ስራ ለመደገፍ ተችሎአል፡፡

**የአነስተኛ መስኖ ልማት ግንባታና አስተዳደርን** በተመለከተ የአነስተኛ መስኖ ልማት ግንባታና አስተዳደርን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ ዝርዝር ዲዛይንና ጥናት ዝግጅታቸዉ ቀደም ሲል

የተጠናቀቀ፤ 71 ቀደም ሲል የተገነቡ (84%) እና 2,431 ሄ/ር(86%) የማልማትና 1,724 አባወራዎችን (430 ሴቶች) ተጠቃሚ የሚያደርጉ መስኖ ተቋም ግንባታ፤18 የጥቃቅንና የቤተሰብ መስኖ ተቋም 123 ሄ/ር የሚያለማ እንዲሁም 13 የአዲስ (67%) መስኖ ተቋም 11,903 ሄ/ር የሚያለማና 14,659 አባወራዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ አነስተኛ የመስኖ ተቋማት ግንባታቸዉ ተጠናቆ በአሁኑ ወቅት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ የ84 መስኖ አዉታሮች በመዘርጋት 4,457 ሄ/ር የማልማት አቅም ያላቸዉንና 18,301 አባወራዎችን (3,642 ሴቶች) ተጠቃሚ የሚያደርጉ የመስኖ አዉታሮችን ግንባታ በማጠናቀቅና ወደስራ እንዲገቡ በማድረግ አርሶ አደሮችን ከዝናብ ጥገኝነት በማላቀቅ የግብርና ምርትና ምርታማነትን በዘላቂነት ለማሳደግ የሚያስችል አቅም ለመፍጠር ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል 51 የተለያዩ ዉኃ ቆጣቢ የዘመናዊ መስኖ ልማት ቴክኖሎጂዎችን የማስተዋወቅና የመስኖ ተቋማት ዘላቂ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ የማስተዳደር፤ የአጠቃቀምና ጥገና ስራ የሚያከናዉኑ 24 ህጋዊ ሰዉነት (75%) ያላቸዉ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚ ማሕበራትን የማጠናከር ተግባር በመከናወኑ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

አ/አደሩን ከገበያ ጋር በማስተሳሰር ላመረተዉ ምርት የተሻለ ገበያ የሚያገኝበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የሚያስችሉ 14 (87.5%) የመዳረሻ ገበያ ማእከላት (7 የሰብል የመጀመሪያ ደረጃ ገበያ፤ 4 የእንስሳት የመጀመሪያ ደረጃ ገበያ እና 2 የማር ምርት ማቀነባበሪያ እና 1 የመንገድ ዳር ገበያ) ግንባታ ስራ ተከናዉኗል፡፡ በተጨማሪም የአ/አደሩን ምርት ለገበያ ተደራሽ ለማድረግ ያስችል ዘንድ ለ11(69%) መጋዘኖች (ለ9 የመጀመሪያ ህብረት ስራ ማህበራት መጋዘኖች እና ለ2 ዩኒየኖች) ግንባታ እና ለ4 የአነስተኛ ድልድይ (80%) ግንባታዎች ድጋፍ ተደርጓል፡፡

### 9.2 ዘላቂ የመሬት አጠቃቀም ፕሮግራም

ውጤታማ ሆነው የተገኙ የዘላቂ መሬት አያያዝ ዘዴዎችን በስፋትና በጥራት እንዲተገበሩ ማድረግ ቁልፍ የሆነው መፍትሄ ሲሆን ይህም የአሳታፊ ተፋሰስ ልማት አሰራርን በመጠቀም በተመረጡ ተፋሰሶች ላይ በመተግበር ላይ ነው፡፡ ማእቀፋን መሰረት በማድረግ ከልማት አጋሮች በተገኘ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ በስድስት ክልሎች ማለትም፤ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣ በደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ እና በጋምቤላ ክልሎች በሚገኙ 250 ተፋሰሶች ዉስጥ ዘላቂ መሬት አያያዝ ፕሮጀክቶች ተቀርጸዉ በመተግበር ላይ ይገኛሉ፡፡ በእነዚህ

ተፋሰሶች ውስጥ 645,000 ቤተሰቦች (በግምት 3.2 ሚሊዮን ሰው) ከፕሮጀክቱ አገልግሎት ያገኛሉ፡

በበጀት አመቱ 4634 ሄክታር የወልና 3728 ሄክታር የእርሻ ማሳ ላይ የተለያዩ የስነ-አካላዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን ጨምሮ በአጠቃላይ እስከአሁን 21703 ሄክታር የወልና 26703 ሄክታር የእርሻ ማሳ ላይ በድምሩ 47906 ሄክታር መሬት ላይ የተለያዩ የስነ-አካላዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራው ተከናውኗል፡፡

በበጀት አመቱ በአጠቃላይ በ442 ችግኝ ጣቢያዎች 60 939 579 ችግኖች የተፈሉ ሲሆን በሰፊው የችግኝ ማፍላት ስራወ ተጠናክሮ እየቀጠለ ይገኛል፡፡ ይህም ያለውን ሀገራዊ የአረንጓዴ ልማት ንቅናቄ በሚደግፍ መልኩ ታቅዶ እየተሰራ ሲሆን ይህን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ማህበረሰቡን የበለጠ ተሳታፊ ለማድረግ ታቅዷል፡፡

የተለያዩ ምርታማነት የሚያሻሽሉ ዘዴዎችን በመጠቀም 22,376 ሄ/ር ለማልማት ታቅዶ 11,089 ሄ/ር (50 በመቶ) በአርሶ አደር ማሣ ላይ የዕቀባ እርሻና በሰብል ቅሪት በመሻፈን የተከናወነ ነው፡፡ ዓላማውም የአፈርን የዕርጥበት ደረጃ ከፍ ለማድረግ ነው፡፡ በተመሣሣይ የአፈር ለምነትን ለማሻሻል የሚረዱ ቴክኖሎጂዎችን (በኮምፖስት፣ በኖራ የማከም እና በመሬት ላይ የጥምር ደን እርሻ) 22,540 ሄ/ር ለማካሄድ ታቅዶ 15,373 ሄ/ር (68.2 በመቶ) ተተግብሯል፡፡ በተጨማሪም በተያዘው ሩብ አመት 50,678 ኩል የተለያዩ የከብቶች መኖ የሚያገለግሉ የተለያዩ የሳር ዝርያዎች የማምረት ስራ ተከናውናል፡፡ በዚህም ከ12,000 በላይ የሚሆኑ አርሶ አደር ቤተሰቦች ተጠቃሚ ማድረግ ተችላል፡፡

## 9.3 ተሳትፏዊ የአነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮግራም

አነስተኛ መስኖ ልመት ፕረሮግራም የመስኖ አውታሮችን በመገንባት 18,400 ሄክታር በመስኖ እርሻ በማልማት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ የተፈጥሮ ሃብት መራቆትን በመቀነስ፣ የግበዓትና ግብይት ስርዓት እንዲሻሻል በማድረግ አነስተኛ የኑሮ ደረጃ ያላቸውን 108,750 አባ/እማ ወራዎችን በምግብ እና በስርዓተ ምግብ ዋስትና ማረጋገጥና የገቢ አቅማቸው እንዲጎለብት ማስቻል ነው፡፡ በመሆኑ የተሳትፎአዊ አነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮግራም ሶስት ዋና ዋና ክፍሎች (Components) አሉት እነሱም የአነስተኛ መስኖ መሰረት ልማት ኢንቨስትመንት፣

አቅም ግንባታ ለዘላቂ ግብርና ኢንቨስትመንት እና ፕሮግራም ማነጅመንት፣ ክትትልና ግምገማ እና ዕውቀት አስተዳደር ናቸው።

ፕሮግራሙ ከጀመረበት ከየካቲት 2009 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ አሁን አጠቃላይ የተጠናቀቁና በግንባታ ሂደት ላይ ያሉ የመስኖ ተቋማት 116 ናቸው። እነዚህ ተቋማት በሙሉ ሲጠናቀቁ 17,100 ሄክታር በማልማት 40,008 (7,579 ሴት) አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ የማድረግ አቅም

በዚህ ዓመት የተሰራው የግንባታ ሥራ በመጨመር አጠቃላይ የመስኖ አውታር ግንባታ ሲታይ ከ116 የመስኖ አውታሮች ውስጥ 70 የመስኖ አውታሮች ግንባታቸው ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ 62 ወደ ግብርና ልማት ገብተዋል ቀሪ 8ቱ ደግሞ የርክክብ ስራ የሚከናወን ይሆናል።

በግንባታ ላይ ካሉት 45 የመስኖ ተቋማት አጠቃላይ የመስኖ ተቋማት ግንባታ በአማካይ 51.51% ላይ ነው። በሌላ መልኩ 25 የመስኖ ተቋማት ይደረግላቸው የነበረው ሁለገብ የሁለት ዓመት ድጋፍ ያጠናቀቁ በመሆኑ መደበኛ የመስኖ ልማት እንቅስቃሴያቸውን ቀጥለዋል። የቀሩት 45 ተቋማት በፕሮጀክቱ ሁለገብ ድጋፍ እየተደረገላቸው በመስኖ ልማት ላይ ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪ ግንባታቸው ሳይጠናቀቅ በከፊል ማልማት የጀመሩ 6 የመስኖ ተቋማት አሉ።

## 9.4 የባለአነስተኛ ይዞታ መስኖ ልማት ፕሮጀክት

በግብርናው ዘርፍ ሁለንተናዊ ዕድገት ዕውን ለማድረግ ከተቀመጡት ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች መካከል የተፈጥሮ ሀብትን በመጠበቅ፣የውኃ ሀብት አያያዝንና አጠቃቀምን በማሻሻል፣ የባለአነስተኛ ይዞታ አርሶ-አደሮች እና ከፊል አርብቶ አደሮች ቢያንስ አንድ የውሃ አማራጭን ለመስኖ ልማት በመጠቀም፤ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮችን በተደራጀ አግባብ ተጠቅመው ዘላቂ የመስኖ ልማትን እንዲያስፋፉ በልዩ ትኩረት ማከናወን ሲሆን ይህም በቤተሰብ ደረጃ የውሃን ተደራሽነት ከማረጋገጥ ባሻገር ተያያዥ ለሆኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች መጎልበት የራሱን አስተዋኦ ያደርጋል።

ስለሆነም አርሶ እና ከፊል አርብቶ አደሮችን ከአካባቢ ስነ-ምህዳር ስፔሻላይዜሽን ጋር በማስተሳሰርና የገበያና የመሠረተ ልማት መስፋፋት ጋር በማያያዝ ደረጃ በደረጃ ተፈፃሚና ተደራሽ ለማድረግ ከሚያስችል ሂደቶች አንዱ የባለአነስተኛ ይዞታ መስኖ ልማት ፕሮጀክት አምስት ኮምፖነንቶችን አካቶ እየተተገበር ያለ ፕሮጀክት ነው።

ፕሮጀክቱ በዋናነት የሚተገብራቸው ስራዎችም 1ኛ የውሀ ሀብት አማራጭ ጥናትና አነስተኛ መስኖ አውታሮች ግንባታ ማካሄድ፣ 2ኛ) ሃይል ቆጣቢ የሆኑ የአነስተኛ መስኖ ልማት ቴክኖሎጅዎችን በመለየት ጥቅም ላይ ማዋል 3ኛ) ተቋማዊ አደረጃጀት/ዓቅምን ማጠናከር እና 4ኛ) ፕሮጀክት ማስተባበርና ማስተዳደር ችሎታን ማሳደግ ናቸው፡፡

በዚህ መነሻነት በዘንድሮ በጀት ዓመት ከ2012 ዓ.ም ከተሸጋገሩ በቁጥር 52 አውታሮች ውስጥ 1,388.22 ሄ/ር ማልማት የሚችሉ እና 3,512 አ/አደሮችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ በቁጥር 25 የመስኖ አውታሮች የተጠናቀቁ ሲሆን ሌሎቹ ያልተጠናቀቁት 27 የመስኖ አውታች አማካይ የፊዚካል አፈፃጸም 58.0% ደርሷል፡፡ እንዲሁም በ2013 በጀት ዓመት አዲስ ውል ከተያዘላቸው 44 የመስኖ አውታሮች ወደ ግንባታ የገቡት 22 ሲሆኑ ከእነዚህ ውስጥ 406.35 ሄ/ር ማልማት የሚችሉ እና 1,535 አ/አደሮችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ በቁጥር 4 የመስኖ አውታሮች ሲጠናቀቁ የቀሪዎቹ 18 ፕሮጀክቶች አማካይ ፊዚካል አፈፃፀማቸው 56% ደርሷል፡፡ ሌሎቹ 22 ፕሮጀክቶች ውልና ቅድመ ክፍያ የተከናወነው በቅርብ ጊዜ (ዝናብ ከጀመረ በኋላ) በመሆኑ ግንባታ ያልጀመሩ ናቸው፡፡ በጥቅሉ በዚህ በጀት ዓመት 1,794.57 ሄ/ር ሊያለሙ የሚችሉና 5,017 አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 29 የአነስተኛ መስኖ አውታሮች ተጠናቀዋል፡፡

ቴክኖሎጂዎችን ከማቅረብ አኳያ በ2012 በጀት ዓመት 3,700.23 ሄ/ር ማልማት የሚችሉ በቁጥር 400 የመስኖ ሞተር ፓምፖችን ለክልሎች የተከፋፈለ ሲሆን በዚህ በጀት ዓመትም 99.6 ሄ/ር ማልማት የሚችሉ በፀሐይ ኃይል የሚሰሩ 120 ፓምፖች ግዥ ተከናውኗል፡፡

የአቅም ግንባታ ስልጠና ከመስጠት አኳያ የፓምፖች አያያዝ፣ አጠቃቀምና ጥገና እና የመስኖ ውሃ አጠቃቀም በተመለከተ ለ552 (ሴት 34) የክልል ባለሙያዎች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በኦሮሚያ ክልልም በኮንትራት አስተዳደር ዙርያ ለ54 (2 ሴት) የዞንና ወረዳ ባለሙያዎች ስልጠና ተሰቷል፡፡ በተጨማሪም በኦሮሚያ ክልል ለ162 (15 ሴት) የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማሕበር አባላት ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በአማራ ክልልም በውሃ አያያዝና አጠቃቀም ዙርያ ለ143 (5 ሴት) የወረዳና ዞን ባለሙያዎች ስልጠና ተሰቷል፡፡ ባጠቃላይ **ለ911 (56 ሴት)** ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

ከመስኖ ልማቱ ጎን ለጎን የወጣቶችን ስራ ዕድል ለመፍጠር በተደረገው ጥረት **1,800** ጊዜያዊና **195** በግንባታ ተቋራጭነት ላይ የተሰማሩ ወጣቶች ተሳትፎ አድርገው ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

ባጠቃላይ ፕሮጀክቱ ከጀመረበት ከ2012 በጀት ዓመት ጀምሮ **3,068.97 ሄ/ር** መሬት ማልማት የሚችሉና **8,199 አ/አደሮችን** ተጠቃሚ የሚያደርጉ በቁጥር **51 የመስኖ አውታሮችን** ለልማት ዝግጁ አድርጓል፡፡

የክልሎች የፕሮጀክቱ አፈፃፀም ከክልል ክልል አቅም ውስንነት፣ ለፕሮጀክቶቹ ትኩረት ከመስጠትና የኮንትራት አስተዳደር ክፍተት አንፃር ሲታይ የአፈጻጸም ልዩነት አላቸው፡፡ይህንንም የፊዚካል የክንውን ደረጃ እንደሚከተለው ቀርቧሯል፡፡

### 9.5 የስደተኞች ተፅዕኖ ምላሽ የልማት ፕሮጀክት

በበጀት ዓመቱ 136 አዲስ እና 9 በ2012 ዓ.ም ተጀምረው ያልተጠናቀቁ የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የመሰረተ ልማት አገልግሎቶችን የሚሰጡ ን/ፕሮጀክቶች በእቅድ ተይዞ እንቅስቃሴ ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት ካለፈው በጀት ዓመት ሳይጠናቀቁ ወደ 2013 ከተሸጋገሩ 9 ን/ፕሮጀክቶች ውስጥ 6 የተጠናቀቁ ሲሆን ቀሪዎቹ 3 እነዚህም 2 በትግራይ እና 1 በአፋር የሚገኙ ሲሆን የአፋር ፕሮጀክት የማጠናቀቅ ሥራ እየተሰራ ሲሆን የትግራይ አልተጀመረም፡፡ የአፋር ንዑስ ፕሮጀክት እስካሁን ሳይጠናቀቅ የቆየበት ምክንያት ቀደም ሲል ግንባታው በሚገኝበት አካባቢ በነበረው የውሃ ሙላትና ጎርፍ ምክንያት እንዲሁም የወረዳው ክትትልና ድጋፍ አነስተኛ በመሆኑ ነው፡፡ የዚህ ን/ፕሮጀክት አፈፃፀም 68% ላይ ይገኛል፡፡ አዳዲስ ፕሮጀክቶች የሚገነቡበት የቦታ መረጣ ስራ፣ ዲዛይን፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት ግምገማ እና ማህበረሰቡን ለ2.5% የጥሬ ገንዘብ እንዲሁም ለ5% የዓይነትና በጉልበት ተሳትፎ ለማሰባሰብ የመቀስቀስና ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚሁ መሰረት የትግራይ ክልልን ጨምሮ 136 አዳዲስ ንዑሳን ፕሮጀክቶች ቦታ መረጣ ስራ የተሰራ ሲሆን 1 ንዑስ ፕሮጀክት በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት ተፅዕኖ ልየታ ግምገማ ወቅት ብቁ ስላልሆነ እንዲሁም 1 ንዑስ ፕሮጀክት የተጠየቀዉ በጀት ከፕሮጀክቱ ወሰን በላይ ስለሆነ ከእቅዱ እንዲወጡ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ከትግራይ ክልል በስተቀር የአራቱም ክልሎች 112 ንዑሳን ፕሮጀክቶች የዲዛይን እና ስፔስፊኬሽን የማዘጋጀት ሥራ ተጠናቆ ጨረታ ወጥቶ ሁሉም ወደ ግንባታ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ከዚህም ውስጥ 98 ንዑሳን ፕሮጀክቶች ግንባታቸው ተጠናቅቋል፡፡ ቀሪዎቹ 14 ንዑሳን ፕሮጀክቶች በተለያዩ የግንባታ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡

የማህበረሰብ መዋጮ ማሰባሰብን በተመለከተ ከትግራይ ክልል ውጭ በአራቱም የፕሮጀክት ክልሎች የ2.5% የገንዘብ ማዋጮ ማሰባሰብ ስራ ሙሉ በሙሉ ተጠናቅቋል፡፡ በበጀት ዓመቱ

9,243,241 ብር በገንዘብ የን/ፕሮጀክት ጠቅላላ ወጪ 2.5% ለማሰባሰብ በታቀደው መሰረት ብር 8,334,334.87(90.16%) የማሰባሰብ ስራ ተሰርቷል፡፡ በሌላ በኩል 18,484,483 ብር በጉልበት/በዓይነት የን/ፕሮጀክት ጠቅላላ ወጪ 5% ከማህበረሰቡ ለማሰባሰብ በታቀደው መሰረት ብር 12,145,686 (65.7%) ለማሰባሰብ ተችሏል፡፡

## 9.6 የድርቅ መቋቋም እና አርብቶ አደር ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም

በበጀት ዓመቱ 17 የውሀ ተቋማት ግንባታ ለማካሄድ በዕቅድ ተይዞ  አስር አነስተኛ የውሀ ተቋማት ግንባታ ተጠናቋል፡፡

በበጀት ዓመቱ  7 ጥልቅ የውሀ ጉድጓዶች ቁፋሮ ለማጠናቀቅ በዕቅድ ተይዞ  የዕቅዱን 100% ለማከናወን ተችሏል፡፡  እንድሁም እስከ 2013 በጀት ዓመት መጨረሻ 59 ጥልቅ የውሀ ጉድጓዶች ቁፋሮ ተጠናቋል፡፡

በበጀት ዓመቱ ቁፋሮቻቸው ከተጠናቀቁ ጥልቅ የውሀ ጉድጓዶች የመስመር ዝርጋታ በማከናወን ጥቅም ላይ ለማዋል 46 ዕቅድ የተያዘ ሲሆን አስራ ስድስት የመስመር ዝርጋታ የተጠናቀቀ ሲሆን አምስት የተጠናቀቁ የውሀ ጉድጓዶች የመስመር ዝርጋታ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

24 የገበያ ማዕከላት ሙሉ በሙሉ ወደ ስራ እንዲገቡ እየተደረገ ይገኛል፡፡ እስካሁን ድረስ 10 የገበያ ማዕከላት ማለትም 1 በሶማሌ ክልል፣ 4 በኦሮሚያ ክልል 4 በደ/ብ/ብ/ህ/ ክልል እና 1 በሶማሌ ክልል አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል፡፡ በደ/ብ/ብ/ህ/ ክልል ዳሰነች ወረዳ የእንስሳት ገበያ ማእከል ግንባታ ስራ 100 በመቶ ተጠናቋል፡፡ ርክክብ እንደተደረገም ወደ አገልግሎት መስጠት ስራ እንዲገባ ይደረጋል፡፡

### 9.6.1 የተፈጥሮ ግጦሽ መሬት ማልማት እና ማኔጅመንት

የቁጥቋጦ እና ወራሪ አረሞችን የማስወገድ ስራ በበጀት ዓመቱ በዕቅድ ከተያዘው 450 ሄ/ር ውስጥ በኦሮሚያ ክልል 187 ሄ/ር እና በደቡብ 148 ሄ/ር በድምሩ 335 ሄ/ር መሬት ላይ በማከናወን የዕቅዱን 74% ለማከናወን ተችሏል፡፡ በፕሮጀከክት ዘመን እስከ 2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ በኦሮሚያ ክልል 14,968 ሄ/ር እና በደቡብ ክልል 3,410 ሄ/ር በድምሩ 18,378 ሄ/ር መሬት ከቁጥቋጦና ከወራሪ አረም እንዲጸዳ ተደርጓል፡፡

በበጀት ዓመቱ በ700 ሄ/ር መሬት ላይ የአፈር እና ውሀ ጥበቃ ስራዎችን በማከናወን የግጦሽ መሬትን እንዲያገግም ለማድረግ በዕቅድ ተይዞ በኦሮሚያ ክልል 148 ሄ/ር እና በደቡብ ክልል 337 ሄ/ር በድምሩ 485 ሄ/ር መሬት ላይ በማከናወን የዕቅዱን 69% ለማከናወን ተችሏል፡፡ ፕሮጀክቱ ስራ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በኦሮሚያ ክልል 6,256 ሄ/ር እና በደቡብ 2,300 ሄ/ር በድምሩ 8,556 ሄ/ር መሬት ከሰው እና ከእንስሳት በመከለል አፈርና ውሀ ጥበቃ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

### 9.6.2 የእንስሳት መሰረተ ልማት ማስፋፋት

በበጀት ዓመቱ በኦሮሚያ ክልል 2.54 ኪ.ሜ እና በደቡብ ክልል 8 ኪ.ሜ በድምሩ 10.54 ኪ.ሜ መጋቢ ግንባታ ለማካሄድ ታቅዶ ግንባታው ሙሉ ለሙሉ የተጠናቀቀ ሲሆን በፕሮጀክት ዘመን በአጠቃላይ በኦሮሚያ ክልል 45 ኪ.ሜ እና በደቡብ ክልል 22.5 ኪ.ሜ በድምሩ 67.5 ኪ.ሜ የመጋቢ መንገድ ግንባታ 100% ግንባታው ለማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

በዕቅድ ዘመኑ 12 ወራት በኦሮሚያ አምስት የገበያ ማዕከል ግንባታ ለማጠናቀቅ በዕቅድ ተይዞ 100% የተከናወነ ሲሆን ፕሮጀክቱ ስራ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከዚህ በጀት ዓመት 12ወር ድረስ በኦሮሚያ ክልል አንድ የነባር የእንስሳ ገበያ ማዕከል ጥገና እና ስድስት አዳዲስ የእንስሳት ገበያ ማዕከላት ግንባታ እንዲሁም በደቡብ ክልል አራት አዳዲስ የገበያ ማዕከላት ግንባታ በድምሩ አንድ የእንስሳት ገበያ ማዕከል ጥገናና አስር አዳዲስ የእንስሳት ገበያ ማዕከላት ግንባታ 100% ተጠናቋል፡፡ የተቀሩት የገበያ ማዕከላት የግንባታ እየተከናወነ ሲሆን በኦሮሚያ ሁለት አዳዲስ የገበያ ማዕከላት ግንባታ በአማካይ 85% እና በደቡብ ሁለት የገበያ ማዕከላት ግንባታ በአማካይ 70% ደርሷል፡፡

በደቡብ ክልል ጂንካ ከተማ በጥገና ላይ ያለ አንድ የእንስሳት ላቦራቶሪ ለማጠናቀቅ በዕቅድ ተይዞ የነበረ ሲሆን የጥገና ስራው 85% የደረሰ ቢሆንም ከኮንትራክተሩ በተለያዩ ምክንያቶች መቀጠል ባለመቻሉ ከኮንትራክተሩ ጋር የነበረው ውል የተቋረጠ ሲሆን ጥገናውን ለማጠናቀቅ እንዲቻል በድጋሚ ጨረታ ወጥቷል፡፡ ሚዛን ከተማ ላይ አንድ የእንስሳት ላቦራቶሪ ጥገና 100% ተጠናቋል፡፡

## 9.7 የክፍለ አህጉራዊ የድርቅ መቋቋሚያና የአርብቶ አደር ኑሮ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ፕሮግራም

በበጀት ዓመቱ 17 የውሃ ተቋማት ለማከናወን ታቅደው 5ቱ የተጠናቀቁ፣ 10 በግንባታ ላይ ሲሆኑ 2 በጨረታ ሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጅ እስካሁን ድረስ 130 የውሃ ተቋማት መገንባት ተችለዋል ፡፡ በባንጋቶም ወረዳ ደ/ብ/ብ/ህ ክልል ውስጥ በአንድ ሲስተም 3 ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶች ቁፋሮ ይገኛል፡፡ አንድ በ250 ሜትር ጥልቀት የተጠናቀቀ ሲሆን 2ኛ ጉድጓድ ቁፋሮ ስራ ተጀምሯል፡፡ አፈጻመሙም 65 በመቶ ነው፡፡

24 የገበያ ማዕከላት ሙሉ በሙሉ ወደ ስራ እንዲገቡ እየተደረገ ይገኛል፡፡ እስካሁን ድረስ 10 የገበያ ማዕከላት ማለትም 1 በሶማሌ ክልል፣ 4 በኦረሚያ ክልል 4 በደ/ብ/ብ/ህ/ ክልል እና 1 በሶማሌ ክልል አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል፡፡

## 9.8 የእንስሳት እና የአሳ ዘርፍ ልማት ፕሮጀክት

የእንሰሳትን ዝርያ ለማሻሻል ፕሮጀክቱ 150 ሆለስታይን ፍሪዥያን ጊደሮች እና 75 የጀርሲ ዝርያዎችን በድምሩ 225 ዝርያዎችን ለመግዛት አቅዶ ግዢው የእቅዱ 88.9% ተከናዉነዋል ፡፡ የሚገዙት ዝርያዎች ከውጪ እንደመጡ ተለይተው የሚቀመጡበት ቦታ በሆልታ እየተገነባ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጅ ግንባታው ባለመጠናቀቁ ምክንያት በአዳበርጋ ምርምር ማዕከል 200 የሃገር ውስጥ ዝርያዎችን ማስገባት ተችሉዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ 10000 ሴመን ለመግዛት ታቅዶ የእቅዱ 100% ተጠናቋል፡፡

በፕሮጀክት ወረዳ ውስጥ የሚገኙ የእንስሳት ጤና ኬላ እና ክሊኒክ በቁሳቁስ ማጠናከር፣(አስፈላጊ የሆኑ የመስክ እቃዎች በወረዳ እና በቀበሌ) ገዝቶ በማቅረብ ህብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ የሚገዙ እቃዎች ተለይተው አየር ላይ ውሏል፡፡

## 10. በአፈፃፀም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

### ዋና ዋና ተግዳሮቶች

- በዓለም አቀፍ ደረጃ ብሎም በሀገራችን የተከሰተው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በእቅድ የተያዙ ስራዎች እንዳይፈጸሙ ማድረጉ፣
- በአንዳንድ አካባቢዎች የተከሰተው የጸጥታ ችግር ባለሀብቶች የተላለፈላቸውን መሬት በተገባው ሊዝ ውል መሰረት ወደ ልማት መግባት እንዳይችሉ ማድረጉ፣
- የተዛማች ተባዮችን ስጋትና አደጋ ለመቀነስ የሚያስችል የሰው ሀይልና ሎጀስቲክ አቅምና አደረጃጀት አለመገንባት፣
- በሀገር አቀፍ ደረጃ በቆዳና ሌጦ ዋጋ መውደቅ የተነሳ ምርቱን በበቂ ሁኔታ ለማሰባሰብ አዳጋች እየሆነ መምጣቱ፣
- የተገነቡ የመስኖ አውታሮች በፍጥነት ወደ ልማት ማሸጋገር ላይ ጉድለቶች መኖር፡፡
- በየደረጃው ያለው መዋቅራዊ አደረጃጀት ወጥነት አለመኖር በተግባራት አፈፃፀምና መረጃ ልውውጥ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረ መሆኑ፣
- የአለም አቀፍ የቡና ዋጋ ከሀገር ውስጥ ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ መሆን የዘርፉን ተዋንያን የሚያበረታታ አለመሆኑ ናቸው፡፡

### የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

- የኮሮና ቫይረስ ተጽዕኖ ለመቋቋም በውስን ባለሙያዎች ስራዎችን ለማከናወን ተሞክሯል፡፡
- የተዛማች ተባዮችን ስጋትና አደጋ ለመከላከልና የጉዳት መጠኑን ለመቀነስ የሰው ሀይልና ሎጀስቲክ አቅምና አደረጃጀት ለመገንባት ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

### ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

- የተዘጋጁ የህግ ማዕቀፎች በቶሎ ፀድቀው እንዲተገበሩ ማድረግ፤
- የአደረጃጀት ችግሮችን ዝርዝር ጥናት በማድረግና ከክልሎቹ ጋር በመነጋገር በቀጣይ የሚፈታበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- የቆዳና ሌጦ ዋጋ  የሚስተካከልበትን መንገድ በመፈለግ ለኤክስፖርት ያለውን ጠቀሜታ ማሳደግ ናቸው፡፡

## 11. ማጠቃለያ

በሀገራችን ኢኮኖሚያዊ እድገት ላይ ከፍተኛ ድርሻ የሚኖረውና መዋቅራዊ ሽግግርን የሚያረጋግጥ የግብርና ዘርፍ ለመፍጠር የሚያስችሉ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተዘጋጅተው ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ የ2013 በጀት ዓመት የተሻሻለውን የግብርና ፖሊሲና የዘርፉን የ10 ዓመት እቅድ መተግበር የምንጀምርበት ዓመት እንደመሆኑ የተለያዩ የመደላድል ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ ከእነዚህም ዋና ዋናዎቹ ዘርፉን ለማጠናከር መሰራት ያለባቸውን የፖሊሲና የሰው ሃይል አስተዳደር ሪፎርሞች፤ እንዲሁም ከፌደራል እስከ ወረዳ ድረስ ያለውን የመረጃ ልውውጥ የሚያቀላጥፉ የዲጂታይዜሽን ስራዎች ይገኙበታል፡፡ በዚህም መሰረት የግብርና ዘርፍ ፖሊሲ ሪፎርም አጀንዳዎች ተለይተው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ የግብርና መረጃ አስተዳደር ስርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ በ12 ክልሎች በተመረጡ 12 ወረዳና በ249 ቀበሌዎች ላይ የሙከራ ትግበራ ለማካሄድ 360 የወረዳና የቀበሌ ባለሙያዎችን በማሰልጠን ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

በተጨማሪም በሀገር ደረጃ ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው ሲሰሩ የቆዩ የልማት ስራዎችን አፈፃፀም በመገምገም በ2013 በጀት ዓመት በላቀ ሁኔታ ግባቸውን እንዲመቱ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህም የአረንጓዴ አሻራን፣ የመኸር እርሻ፣ የአንበጣ መከላከል፣ የቆላ ስንዴ ልማት ዝግጅት፣ የአነስተኛ መስኖ ፕሮጀክትን እንዲሁም የኩታ-ገጠም እርሻ ስራዎችን በልዩ ሁኔታ በመገምገም የማሻሻያ አቅጣጫዎች ተቀምጠው እንዲፈፀሙ ተደርጓል፡፡

የግብርና ዘርፍ በ2012 በጀት ዓመት መጠነ ሰፊ ተግዳሮቶች ሲገጥሙት ቆይተዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል የበረሃ አንበጣ፣ ኮቪድ-19 ወረርሽኝ እንዲሁም ከመጠን ያለፈ ዝናብን ተከትለው የተከሰቱ የጎርፍ አደጋዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ለእነዚህ ተግዳሮቶች ተገቢውን ምላሽ ከመስጠት አኳያ በፌደራልና በክልል መንግስታት ተገቢውን መዋቅሮች በመገንባትና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጡ አሰራሮችን በማስቀመጥ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ ለስራዎቹ የሚያስፈልጉ ድጋፎችን ከመንግስትና ከልማት አጋሮች አቀናጅቶ በመጠቀም አደጋዎቹ ሊያስከትሉት የሚችሉትን ጉዳት በሰፊው መቀነስ ተችሏል፡፡ በትግበራ ሂደት ገተገኘውም ልምድ በተለይም ወረርሽኝን ለመከላከል ተቋማዊ አቅም ለመገንባት ከፍተኛ ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ በዘርፉ ውስጥ የሚሰሩት ስራዎች ጥራትና ቀጣይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ የሃብት ማሰባሰብ፣ ተቋማትን የማጠናከር፣ የአሰራር ስርዓቶችን የማሻሻልና ከአጋሮች ጋር ያለውን ግንኙነት የማጠናከር ስራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡

የተቋማዊ ለውጥን በተመለከተ በሰው ኃይል፣ በፖሊሲ፣ ግብርናን በቴክኖሎጅ በመደገፍና ምቹ የስራ አካባቢ እንዲኖር በማድረግ ከፍተኛ ውጤት የታየበት ተግባር ተከናውኗል፡፡

## 12. የግርጌ ማስታወሻ

### የሪፖርት ጥንቅር  መረጃዎች ፤ክፍትቶችና ጠቃሚ መፍትሄዎች

- ቀደም ሲል በ2013 በጀት ዓመት የሰብልና ሆርቲከልቸር እቅድ ሲታቀድ በኮቪድ የተነሳ በ2012 በጀት ዓመት የተደረሰበት በላይ መፈጸም አዳጋች እንደሚሆን በግምት ውስጥ በማስገባት የእቅድ ማሻሻያ የተደረገ ቢሆንም በ10 ዓመትና በ5 ዓመት የልማት እቅድ ላይ የተቀመጠውን ከመካከለኛ ጊዜ ግምገማ ወዲህ መሻሻ ስለማይቻል ዓመታ እቅዱ ዒላማ ቀደም ሲል በ10 እና 5 ዓመት ላይ የተቀመጠው ተወስዶ ትንተናው በዚሁ መሰረት ተሰርቷል፡፡

- ይህን ሪፖርት ለማጠናከቀር ከየዘርፉ እና ተጠሪ ተቋማት የቀረቡ ረቂቅ ሪፖርቶች ሥራ ላይ ውሏል፡፡

- ለሰብልና ሆርቲካልቸር፣ለእንስሳት ዘርፍ ሪፖርቶች የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ የናሙና ጥናት መረጃዎች በሥራ ላይ ውሏል፡፡ በተፈጥሮ ሀብት ፤በምግብ ዋትና፤ በስራ እድልፈጠር፣በምርምር፣ እንዲሁም በዘርፈ ብዙ ጉዳዮች የአስተዳደራዊ መረጃ በጥቅም ላይ ውሏል፡፡

- በ10 ዓመቱ እቅድ  የተወሰኑ የስኬት (Outcome) አመልካቾች ዓመታዊ ዒላማ ተቀመጠላቸው ቢሆንም ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ሆነ ከግብርና አስተዳደራዊ የመረጃ ምንጭ መረጃ ባለመገኘቱ አፈጻጸም ማስቀመጥ አልተቻለም (ለምሳሌ ለገበያ የቀረበ ምርት መጠን፤ ለእንስሳት ሞት መጠን በእንስሳት ምረት ዓይነት …ወዘተ ፡፡ ስለሆነም በቀጣይ ዓመታት የመረጃ ምነጭ በመለየትና ባለቤት በመስጠት መረጃ የሚሰበሰብበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

- በ10 ዓመቱ እቅድ ውሰጥ ያልታዩ ነገር ግን በዓምራቹ ውሳኔ (የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደርና በላሀብት እርሻ) የለሙ ሰብሎች እቅድ ባይኖራቸውም አፈጻጸማቸው እንዲታይ ተደርጓል (ለምሳሌ የአነስተኛ ይዞታ አርሶአደር በልግ ምርት በሰብል ዓይነት፡፡

- በ10 ዓመቱ እቅድ ውስጥ በረጅምና በመካከለኛ ጊዜ የሚለኩ ዓመልካቾች በዓመታዊ ሪፖርት ውስጥ እንዲካተቱ አልተደረገም (ለምሳሌ የአፈር ክህለት መቀነስ፤ የባዮማስ መጠን መጨመር …. ወዘተ በጥናት መረጃቸው የሚመነጭ ስለሆነ፡፡

- በፕሮግራም ውጤት ደረጃ በሪፖርቱ የተካተተ አፈጻጸሞች በመሪ እቅዱ በዝርዝር የታቀዱ ባይሆንም ለስኬቶች ያላቸው አስተዋጽኦ ሊየሳይ በሚችል ደረጃ እንዲካተት ተደርጓል (ምሳሌ ዝርያ ማሻሻል፤ የተፋሰስ ልማት፣አፈር ለምነትና ጤንነት፤ መኖ ልማት….ወዘተ) ፡፡

## 13. አባሪ 1፡ የግብርና ዘርፍ የቁልፍ አመልካቾች የ2013 ዓመታዊ አፈጻጸም

| የአፈጻጸም አመልካቾች | መነሻ ዓመት 2012 | የ2013 ግብ | የዓመቱ አፈፃፀም | አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 1. የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግ | | | | |
| **ጠቅላላ የሰብል ምርት በሚሊዮን ኩንታል** | 543.0 | 571.0 | 640.3 | 112.1 |
| **የዋና ዋና የምግብ ሰብሎች ምርት በሚሊዮን ኩንታል (ጠቅላላ)** | 404.9 | 425.6 | 380.7 | 89.5 |
| **የብርዕ ሰብሎች ምርት በሚሊዮን ኩንታል (ጠቅላላ)** | 153.0 | 161.1 | 159.7 | 99.1 |
| *የጤፍ ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል* | 60.5 | 63.1 | 55.7 | 88.4 |
| *የገብስ ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል* | 29.0 | 29.8 | 23.7 | 79.8 |
| *የስንዴ ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል* | 61.2 | 65.1 | 64.9 | 99.7 |
| *የአጃ ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል* | 0.5 | 0.5 | 0.3 | 70.9 |
| *የሩዝ ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል* | 1.9 | 2.6 | 2.8 | 104.6 |
| *የዳጉሳ ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል* | 0.00 | 0.00 | 12.16 | |
| *ሌሎች የብርዕ ሰብሎች ምርት በሚሊዮን ኩንታል* | | | | |
| **የአገዳ ሰብሎች ምርት በሚሊዮን ኩንታል (ጠቅላላ)** | 208.2 | 218.7 | 176.7 | 80.8 |
| የበቆሎ ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 139.50 | 149.45 | 128.55 | 86.0 |
| የማሽላ ምርት መጠን በሚሊዮን ኩንታል | 57.67 | 57.57 | 48.14 | 83.6 |
| የዘንጋዳ ማሽላ ምርት መጠን በሚሊዮን ኩንታል | 11.0 | 11.7 | 0.0 | 0.0 |
| **የጥራጥሬ ሰብል ምርት ሚሊዮን ኩንታል (ጠቅላላ)** | 33.1 | 34.2 | 34.1 | 99.8 |
| *የባቄላ ምርት መጠን በሚሊዮን ኩንታል* | 10.08 | 10.44 | 10.79 | 103.4 |
| *የአተር ምርት መጠን በሚሊዮን ኩንታል* | 3.90 | 4.06 | 3.77 | 92.8 |
| *የሽምብራ ምርት መጠን በሚሊዮን ኩንታል* | 5.39 | 5.28 | 4.82 | 91.4 |
| *የምስር ምርት መጠን በሚሊዮን ኩንታል* | 1.19 | 1.25 | 1.37 | 109.9 |
| *የጓያ ምርት መጠን በሚሊዮን ኩንታል* | 3.13 | 3.20 | 3.01 | 93.9 |
| *የአኩሪ* አተር ምርት መጠን በሚሊዮን ኩንታል | 2.42 | 2.95 | 2.71 | 91.8 |
| *የግብጦ ምርት መጠን በሚሊዮን ኩንታል* | 0.35 | 0.37 | 0.29 | 80.3 |
| የማሾ ምርት መጠን በሚሊዮን ኩንታል | 0.96 | 0.77 | 0.79 | 102.0 |

| የአፈጻጸም አመልካቾች | መነሻ ዓመት 2012 | የ2013 ግብ | የዓመቱ አፈፃፀም | አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| የነጭ ቦሎቄ ምርት መጠን በሚሊዮን ኩንታል | 2.13 | 2.20 | 2.15 | 97.7 |
| የቀይ ቦሎቄ ምርት መጠን በሚሊዮን ኩንታል | 3.12 | 3.29 | 3.85 | 117.0 |
| የአብሽ ምርት መጠን በሚሊዮን ኩንታል | 0.380 | 0.384 | 0.564 | 146.8 |
| ሌሎች ጥራጥሬ ሰብሎች ምርት መጠን በሚሊዮን ኩንታል | | | | |
| **የቅባት ሰብል ምርት በሚሊዮን ኩንታል (ጠቅላላ)** | 10.73 | 11.57 | 10.23 | 88.4 |
| የሰሊጥ ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 4.85 | 5.34 | 4.95 | 92.7 |
| የኑግ ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 2.91 | 3.08 | 2.15 | 69.8 |
| የለውዝ ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 1.51 | 1.63 | 2.07 | 127.1 |
| የተልባ ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 0.80 | 0.85 | 0.81 | 95.9 |
| የጎመን ዘር ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 0.556 | 0.538 | 0.194 | 36.0 |
| የሱፍ ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 0.10 | 0.14 | 0.05 | 36.8 |
| የሌሎች የቅባት እህሎች ምርት ሚሊዮን ኩንታል | | | | |
| **የአትክልት ምርት በሚሊዮን ኩንታል (ጠቅላላ)** | 31.33 | 32.45 | 20.62 | 63.5 |
| ቲማቲም ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 7.63 | 7.87 | 6.08 | 77.2 |
| የሰላጣ ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 0.45 | 0.38 | 0.22 | 56.2 |
| የጥቅል ጎመን ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 7.79 | 8.19 | 4.21 | 51.4 |
| የሀበሻ ጎመን ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 10.30 | 10.57 | 5.59 | 52.9 |
| የቃሪያ ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 5.16 | 5.44 | 4.44 | 81.6 |
| ፎሶሊያ ምርት መጠን በሚሊዮን ኩንታል | 0 | 0 | 0.047 | |
| የቆስጣ ምርት መጠን በሚሊዮን ኩንታል | 0.000 | 0.000 | 0.045 | |
| **የስራስር ሰብሎች ምርት በሚሊዮን ኩንታል (ጠቅላላ)** | 77.85 | 81.76 | 112.10 | 137.1 |
| የቀይ ስር ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 5.60 | 5.72 | 7.67 | 133.9 |
| የካሮት ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 1.48 | 1.60 | 0.63 | 39.5 |
| የድንች ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 31.75 | 33.26 | 32.52 | 97.8 |
| የሸንኩርት ምርት መጠን በሚልዮን | 25.71 | 27.20 | 26.89 | 98.8 |

| የአፈጻጸም አመልካቾች | መነሻ ዓመት 2012 | የ2013 ግብ | የዓመቱ አፈፃፀም | አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| ኩንታል | | | | |
| የነጭ ሸንኩርት ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 5.77 | 5.94 | 4.88 | 82.1 |
| የጎዴሬ ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 7.41 | 7.88 | 23.28 | 295.5 |
| የስኳር ድንች ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 0.14 | 0.16 | 16.23 | 100.0 |
| የያም ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 0 | 0 | 0.0037 | |
| የካሳባ ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 0 | 0 | 0.0028 | |
| የዱባ ምርት በሚሊዮን ኩንታል | 0 | 0 | 0.0015 | |
| **የፍራፍሬ ምርት በሚሊዮን ኩንታል (ጠቅላላ)** | 10.66 | 11.80 | 15.71 | 133.1 |
| የዘይቱን ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 0.07 | 0.08 | 0.04 | 44.0 |
| የሎሚ ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 0.17 | 0.18 | 0.07 | 41.0 |
| የብርቱካን ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 1.00 | 0.83 | 0.85 | 101.9 |
| የፓፓያ ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 1.52 | 1.36 | 1.06 | 77.9 |
| የአናናስ ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 0.02 | 0.03 | 0.03 | 82.8 |
| የአቮካዶ ምርት መጠን በሚልዮን ኩንታል | 1.06 | 1.30 | 2.59 | 198.7 |
